
# ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! 3ኛ መፅሐፍ
# My Bride I am on My way get ready - Book 3 - Amharic



# መግቢያ

ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ በሚል ርዕስ በሶስት መፅሐፍ የቀረቡ እነዚህ መልዕክቶች ከኢየሱስ የተላኩ የፍቅር ደብዳቤዎች በሚል ርዕስ በሲስተር ክሌር ዴቡስ ከቀረቡ መልዕክቶች ተመርጠው የተተረጎሙ ናቸው፡፡ ይህንንም ርዕስ የመረጥንበት ምክንያት በእርግጥም ሙሽራው ሊመጣ በደጅ ስለሆነና ሙሽሪት ይህንን በመገንዘብ መዘጋጀት እንዳለባት አፅንዎት ለመስጠት ነው፡፡ ሲስተር ክሌር ዴቡስ የ74 ዓመት አሜሪካዊት ነቢይት ስትሆን ከጌታ መልዕክቶችን እየተቀበለች እ.አ.አ. ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ አይነት መንገድ ለአለም እያስተላለፈች ትገኛለች፡፡ በሦስቱም መፅሐፍ ተርጉመን ያቀረብንላችሁ መልዕክቶች ከአንዳንዶች በስተቀር ከሲስተር ክሌር የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህም የእርሷ ያልሆኑ መልዕክቶች በ1ኛው መፅሐፍ የካሮል ጄንጊዝ አንድ መልእክት፣ በሁለተኛው መፅሐፍ የኸርት ድዌለርሷ የናና አንድ መልእክት እንዲሁም በሦስተኛው መፅሐፍ ውስጥ በሲስተር ክሌር መፅሐፍ ውስጥ ቀርቦ የነበረ የማይክ ፐራልታ አንድ መልዕክት ናቸው፡፡ የሲስተር ክሌር መልእክቶች እጅግ ብዙ በመሆናቸው ለእናንተ ለአንባቢዮቻችን የበለጠ ይጠቅማል ብለን የመረጥነውን ብቻ ተርጉመን በመፅሐፍ መልክ በማጠናቀር አቅርበናል፡፡

ዘ ኤንድ ዴይስ ሚኒስትሪስ/ The End Days ministries / ዋና ዓላማው በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና ህዝባችን ሊሰማቸው የሚገቡ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች በመተርጎም ለህዝባችን ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ እነዚህንና ሌሎች መልዕክቶችን በንባብ መልክ በድምፅ ተቀርፆ በዩ ቱዩብ ቻናላችን ላይ ታገኙታላችሁ፡፡

በሲስተር ክሌር የሚተላለፉ መልዕክቶች አጠቃላይ ይዘታቸውን ስንመለከት ሙሽራው በቅርብ ሊመጣ እንደሆነ፣ ሙሽሪት ከጌታዋ ጋር ለመሄድ /ለንጥቀት/ መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዲሁም የማይነጠቁ ሰዎች በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ታላቁ መከራ ተብሎ የተጠቀሰውን ዘመናት በምድር እንደሚያልፉና በዚህም የመከራ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክቱ ወሳኝ መልዕክቶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ጠቅላላውን መልዕክት በሚከተሉት ቻናሎችና ዌብሳቶች ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡

(1) በአማረኛ የተተረጎሙ መልዕክቶችን ለማግኘት/ translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) በአማረኛ ዘ ኤንድ ዴይስ የተተረጎሙ ትንቢታዊ መልዕክቶችንና መፅሐፎችን ለማግኘት - heartdwellers.org – Book በሚለው ውስጥ ገብታችሁ እነዚህን ርዕሶች ታገኛላችሁ;-

- The Rapture was real Book Amharic pdf - ንጥቀቱ እውን ነበር በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- Tethered Book Amharic pdf - ቴተርድ በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- My Bride get ready Book one – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ አንድ
- My Bride get ready Book two – Amharic pdf / ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሁለት
- My Bride get ready Book three – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሦስት
- Events after the rapture Amharic pdf/ በቅርብ ስለሚሆኑ ክስተቶችና ስለ ታላቁ የመከራ ዘመን

(3) በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ መልዕክቶቹን ለማግኘት/ Messages in Engilish

- heartdwellers.org
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## ጌታ ዘመናችሁን ይባርክ

# Introduction

The title of this book, in Amharic "ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! " translated to Engilish "My bride get ready I am on my way ", was given to show that the Groom is truly on His way and to alert the bride. All the messages in the three books (book 1, book 2 and book 3) except same messages were taken and translated from Sister Clare, The other Messages are Calor jenngs message in the first book, Nana's Messagen in the second book and Mike Peralta message (taken from Love letter book- new) in the third book. Sister Clare is a 74 years old American prophetess who hears and transmites messages from God to the world through different Medias since 2014. Her messages are so many and we have tried to translate very few of them.

We are doing this since one of our ministries goals is to acceses prophetice messages spoken in Engilish and which are relevant to our people. For this purpose we have translated and recorded same messages and uploaded them on you tube.

When we look to the content of Sister Clars' messages, they talk about the coming of Jesus sooner than expected, intiate brides to be ready for the rapture and explaine how to be ready. In addition, they reveal what is to come after the rapture, what will the left behind face in the period called great tribulation, which is written in the Bible, and the messages also give same hints how to persevere in the tribulation. Therfore if you want to get the whole messages in English and the translated messages in Amharic you can find them as follows:-

(1) Translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) Translated messages compiled in book pdf - go to - heartdwellers.org to Book folder then search for these titles;-

- The Rapture was real Book Amharic pdf
- Tethered Book Amharic pdf
- My Bride get ready Book one – Amharic pdf
- My Bride get ready Book two – Amharic pdf
- My Bride get ready Book three – Amharic pdf
- Events after the rapture Amharic pdf

(3) The whole Messages in Engilish

- heartdwellers.org
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## God bless you

| ተራ ቁ. | የመልዕክቱ ዝርዝር ርዕሶች | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | ቤተሰባዊ ግንኙነቶችና ጠላት የሚደግሰው የማታለያ ድግስ / Don't Take the Bait & Rapture Preparation, | 5 |
| 2 | ታይቶ የማይታወቅ ጊዜ ከፊታችን እየመጣ ነው / The Time We are Entering shall be like no other | 7 |
| 3 | የደከሚችሁና የዛላችሁ ሁላችሁ ወደ እኔ ኑና አሳርፋችኋለሁ / Come Unto Me All Who Are Weary | 10 |
| 4 | የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያ -የራስ ቁር / The Armor of God- Helmet | 13 |
| 5 | የሚሊኒየሙ የወንድማማቾች ፍቅር / Shoulder to Shoulder Unity | 16 |
| 6 | የወደቁ መላዕክቶች ወደ ምድር መምጣትና መደረግ ያለበት ጥንቃቄ / The Name of Jesus Routes Demons | 19 |
| 7 | የእግዚአብሔር ቁጣ ዘግይቶ የምህረት ጊዜ ተጨምሯል/ A Love Letter to You | 23 |
| 8 | የመዳናችሁ ቀን ከምንግዜውም ይልቅ ቀርቧል / Your Redemption Draws Near | 29 |
| 9 | ትልቁ መነቃቃት( ዘ ግሬት አዋክኒንግ) ምንድነው / What is the great awakning | 31 |
| 10 | የወደቁ መላዕክት/*Aliens*/ መጓጓዣዎች አየሩን ሁሉ ይሞሉታል / Alien Vehicles Will Fill the Skies | 37 |
| 11 | እናንተ የወንድማችሁ ጠባቂዎች ናችሁ / You are your brother's keepers | 44 |
| 12 | በጀርባ እየተካሄዱ ያሉ ክስተቶችና የኮሮና ቫይረስ ክትባት ሚስጥር / America Behind the Scene | 49 |
| 13 | የጌታ ኢየሱስ ጥሪ ለተናቁትና ለማይፈለጉት / Rapture update & My call to the unwanted, April 22nd, 2021 | 53 |
| 14 | መንግስተ ሰማያት መግባቴን ንዴት እርግጠኛ ልሆን እችላለሁ? የተጋጀው በማይክ ፐራልታ / The Gospel Simply Explained, Mike Peralta | 55 |

**"ቤተሰባዊ ግንኙነቶችና ጠላት የሚደግሰው የማታለያ ድግስ" ጄንዋሪ 4 ቀን 2021 ዓ.ም**

**Don't Take the Bait & Rapture Preparation, January 4, 2021**

(ክሌር)፡- ሰይጣን በጣም የሚወደው አንድ ነገር ቤተሰብ ሲሰበሰብ ጥሩ ጊዜ እንዳያሳልፉ ሁኔታዎችን ማበላሸት ነው፡፡ በቅርቡ የጌታን ልደት ለማክበር ማህበረሰቡ በአንድ ላይ ተሰብስቦ በጣም ቆንጆ የሆነ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ነበር፡፡ በአሉን እያከበርን እያለን ወደ ተራራው መግቢያ የሆነው በር እንደተቆለፈ ወሬ ሰማን፡፡ ይህም በመሆኑ ከውጪው አለም ጋር መገናኘት አንችልም፡፡ ከተራራው መውረድም ሆነ ወደ ተራራው መውጣትም አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት በታኦስ የሚገኙት አባላቶቻችን እንኳን ለእሁድ ስብሰባ ወደ እኛ መምጣት አይችሉም ማለት ነው፡፡

ይህ ደግሞ እኔን አዝቅት ውስጥ አስገባኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ማድረግ የቻልኩት ከስብሰባው ወጥቼ ማልቀስ ነበር፡፡ ይህ የሆነው እንግዲህ ሁላችንም ተሰብስበን ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን ባለንበት ወቅት ላይ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ከተወሰደው ተሞክሮ የተነሳ ለበአሉ ተብሎ ጉዳዩን እኔ እንዳልሰማ ተደርጎ ነበር፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ለጌታ ልደት ዋዜማ አንዱ ወንድማችን እንዲሁ የሚያሳዝን ነገር ገጥሞት ነበር፡፡ ይህ ወንድማችን በሚቺጋን የሚገኘውን ልጁን ለበአሉ ለማየት ትኬት ቆርጦ ለመሄድ ሲያስብ የቀድሞ ሚስቱ በኮሮና ምክንያት ልጁን ማየት እንደማይችል ነገረችው፡፡ ይህም እርሱን ከሚገባው በላይ ሐዘን ውስጥ ከትቶት ነበር፡፡ በኋላ ግን ነገሩን በውይይት በመፍታት ልጁን ለማግኘት ሄዷል፡፡

ሰይጣን ሊያርድ፣ ሊሰርቅና ሊያጠፉ እንደገና መጣ! እርሱ ደግሞ የሚመጣው በእኛ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያመጣ ነገር ላይ ነው፡፡ ስለዚህም በጣም ደስ ተሰኝታችሁ እያሳለፉችሁ ባላችሁበት ወቅት ላይ እንደዚህ አይነት ድንገተኛ ኃዘን ሲከሰትባችሁ ያ ውሸት የማይቆይ መሆኑን ወይም እናንተ በማታውቁት መንገድ እግዚአብሔር መውጫ እንዳዘጋጀ እወቁና ተዘጋጁ፡፡ በእውነቱ ከሆነ እንዲህ አይነቱ ስቃይ  ለፀሎቶቻችሁ እንደ ፆም ስጦታ ሆኖ ለጌታ የሚቀርብ ነው፡፡ ምክንያቱም የልባችሁ ስቃይ እጅግ ከባድ ስለሆነ ነው፡፡ እናም እንዲህ አይነቱ ነገር ሁኔታዎችን ወደ በረከት ይለውጣል፡፡

*እግዚአብሔር ሆይ  ህዝቅኤል ወደ ተራራው የመግቢያ በር አንድ ብቻ መሆኑን እያወቀ በሩ ቢዘጋም እንኳን ፍፁም ሰላም ስለሆን አመሰግንሃለሁ፡፡ እናም በእርሱ ምክንያት ጉዳዩ በአንተ ቁጥጥር ስር እንደሆነ እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡*
*እነዚህን ነገሮች የምነግራችሁ በጣም የሚጎዱ ስለሆኑና በበአል ወቅት ደግሞ ጠላት የሚፈልገው በቤተሰቦች ወይም በቤተ ዘመዳሞች መካከል ጥል መፍጠርን፣ ያለመስማመትን፣ ያለመግባባትን፣ ደም ማፍላትን በመፍጠር የሚችለውን ሁሉ በማድረግ በመልካም ለማሳለፍ ያሰባችሁትን ጊዜያችሁን ማበላሸት ነው፡፡ ይህ በእናንተ መካከል እንዲሆን አትፍቀዱ፡፡ እነዚህን ነገሮች እንዳይፈጠሩ በመጠበቅ የምታደርጉትን ቀጥሉ፡፡ ሁሉ ነገር በጌታ ቁጥጥሩ ሥር ነው፡፡*
*ጌታ? ብዬ ገና ስጣራ ወዲያው መለሰልኝ፡፡*

*ጌታም . . . " የኔ ውዶች የሰይጣን መንግስት መልዕክተኞች ይህንን እቅድ የሚያወጡትና ሴራን የሚጠነስሱት በቤተሰብ ደስታ መካከል ሐዘንን በማምጣት ዝቅ ሊያደርጓችሁ ነው፡፡ ታዲያ እናንተ ይህ እቅዳቸው እንዲፈፀም ተባባሪ መሆን*

የለባችሁም፡፡ ጠላት ምን ለማድረግ እንዳሰበ ከገባችሁና በልባችሁ ነገሩን ካስቀመጣችሁ ከተዘጋጀው ወጥመድ በማምለጥ ቤተሰብ ሊደርስበት ያለውን የግንኙነት መበላሸት ታስቆማላችሁ፡፡

"እንደነዚህ አይነት ክብረ በአላትን ስታከብሩ፣ ጠላት መከፋፈልን ለመፍጠር፣ ስሜትን ለመጉዳትና መራራቅን ለመፍጠር አጀንዳንና መዝገብን ይዞ ይቀሳቀሳል፡፡ የእያንዳንዳችሁን ደካማ ጎን ስለሚያውቅ በእያንዳንዳችሁን ደካማ ጎን ይጠቀማል፡፡ ይህንን ለማስወገድ ከፈለጋችሁ አጀንዳችሁ ወንድማችሁን መውደድ ብቻ ይሁን፡፡ ለእምነቱ ጥላቻ እንዳላቸው የምታውቁ ከሆነ እነዚህን በዓላት ለስብከት አትጠቀሙባቸው፡፡ በሚያጋግሉ ርዕሶች ላይ ውይይት አታድርጉ፡፡ ዳክዬዎች ውኃ በጀርባቸው ላይ እየተከባለለ እንደሚወርድ ስድቦችም በእናንተ ላይ እንዲሁ ይንከባለሉ፡፡ መጋጋልን ሊፍጥሩ የሚችሉ ርዕሶች ላይ አትሳተፉ፡፡ ቦታውን ልቀቁ ወይም ርዕስ ቀይሩ፡፡ ሁሉንም ነገር በአሉታዊ መንገድ አከናውኑ፡፡ አንድ በሚያደርጋችሁና ሁላችሁንም ሊያሳትፍ በሚችል ነገር ላይ ተነጋገሩ፡፡ እንደተከበሩና እንደተወደዱ እንዲሰማቸው አድርጉ፡፡ በተለይም በእናንተ ላይ ግንባራቸውን የሚያኮሳትሩ ከሆነ ይህንን አድርጉ፡፡ ምክንያቱም ፍቅር ሁሉንም ልብ ያለሰልሳል፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን እንደሚገባው መጠን ሥራ ላይ አልዋለም፡፡ ነገር ግን ይህንን ከልብ ባልሆነ መንገድ አታድርጉት፡፡ ልባችሁን በፍቅር እንድሞላው ሁልጊዜ ጠይቁኝ፡፡ ያንን የሰጧችሁን ፍቅር ደግሞ ከውስጥ ልባችሁ በማውጣት ተለማመዱት፡፡

"ማስታወስ ያለባችሁ የብዙዎች ጉዳት የሚጀምረው ከህፃንነት በመሆኑ የእናንተ ጥፋት ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ወንድሞቻችሁ አሁን እየደረሰባቸው ያለውን ፈተና በማሰብ ለማፅናናትና ለማበረታታት እናንተ ምንጮች ሁኑ፡፡ ሁልጊዜም ሊገባችሁ የሚያስፈልገው እንደ እውነቱ ከሆነ እናንተን የሚዋጋ የሚመስላችሁ ነገር የሚመጣው ከተለያየ ምንጭ ነው፡፡ የጎዳችሁ ሰው እንኳን እንደጎዳችሁ ላያስተውል ይችላል፡፡ ነገር ግን ኢጋንንት እርሱን በመጠቀም በጣም ደካማ የሆነውን ማንነታችሁን እንዲነካ ያደርጋል፡፡

"ምን እየተካሄደ እንዳለ ከገባችሁ ያንን ግንኙነት እንዲበላሽ ከማድረግ ይልቅ ለማስተካከል ትችላላችሁ፡፡ ነገሮች ለመጋጋል ዕድል ያላቸው ከመሰላችሁ ወደ አንድ ቦታ ሄዳችሁ ፀልዩ፡፡ በአይምሮአችሁና በልሳኖቻችሁ ፀልዩ፡፡ ምክንያቱም ውጊያችሁ ከሥጋና ከደም ጋር አይደለምና ነው፡፡ ስሜታችሁን የጎዳውን ማንንም ይቅርታ አድርጉ፡፡ እናንተም ይቅርታ መጠየቅ ካለባችሁ ይቅርታ ጠይቁ፡፡

"ከቤተሰብ ጋር አንድ ላይ ስትሰባሰቡ የእኔ ትልቁ ምኞት መልካም የሆኑ ግንኙነቶችን እንድታጠናክሩና የተሰበሩትን እንድትጠግኑ ነው፡፡ በዘመዶቻችሁ ደስ እንድትሰኙ እፈልጋለሁ፡፡ ከእነሱ እንድትርቁ አልፈልግም፡፡ እናንተን ከዘመዶቻችሁ ማራቅ ደግሞ የጠላት አጀንዳ ነው፡፡ ቤተሰብ እርስ በእርስ በጋራ ተሳስሮ ትንሹ የህብረተሰብ ክፍል በመሆን በችግር ጊዜ አንዱ ለአንዱ እንዲገኝ ተብሎ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡ ጠላት ግን የሚፈልገው ይህንን በመስረቅ ሁላችሁም ለየብቻችሁ እንድትሆኑና እርሱ በፈለገ ጊዜ ነጥሎ በቀላሉ ሊወስዳችሁ እንዲችል ነው፡፡

"አሁን ግን ይህንን ነግሬያችኋለሁ፡፡ የሚያስፈልጋችሁ ይህንን በሥራ ላይ ለማዋል መለማመድ ነው፡፡ በዚህም የእኔ ሰላም መልዕክተኞች ትሆናላችሁ፡፡ በችግሮቻችሁ መሃከል እኔን ጥሩኝ፡፡ እኔም ልረዳችሁ ፈጥኜ እገኝላችኋለሁ፡፡ እጅግ እወዳችኋለሁ እናንተም ሄዳችሁ ሌሎችን እንዲሁ ውደዱ፡፡ ይህም ሊወደድ የማይችለውን እንኳን በተመሳሳይ መንገድ ውደዱ፡፡ ክርስቲያን መሆናችሁን በፍቅራችሁ ያውቃሉ፡፡ እናም በዚህ ሰዎችን ሁሉ ወደ እኔ እስባለሁ፡፡"

## ታይቶ የማይታወቅ ጊዜ ከፊታችን እየመጣ ነው - ጀርዋሪ 13 ቀን 2021 ዓ.ም

**The time we are entering shall be like no other, January 13th, 2021**

ኸርት ዱዌለርስ ጌታ ሰላሙን፣ እንዲሁም በእነዚህ ቀናት እጆቹ እየተቀሳቀሱ እንደሆነ እንድታምኑትና በእርሱ ላይ ለመደገፍ እንድትችሉ ችሎታ ይስጣችሁ፡፡ ጌታ ይባርካችሁ፡፡

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ጌታን፣ ግርማዊነቱንና ሉአላዊነቱን ሁልጊዜ ከፊታችን እናስቀድም፡፡ ምንም ነገር እየሆነ ቢሆንም ሰላማችንን ለመጠበቅና በእርሱ ፍፁም ፈቃድ ውስጥ ለመቆየት እርሱ ለሁሉም መልስና መልካም መንገድ እንዳለው እርግጠኞች መሆን አለብን፡፡

ጌታ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ነገር እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ይህም ቢሆን ግን መልካም መሆንህን ስለማውቅ፣ በስተመጨረሻም ከእነዚህ ነገሮች መልካም ነገር እንደምታወጣ በማወቄ ሰላሜን የማገኘውና ደህንነት የሚሰማኝ ራሴን በአንተ ልብ ላይ በማሳረፌ ብቻ ነው፡፡ እዚህጋ አንድ ተጨማሪ የምናገረው ነገር ቢኖር ምን ማመን እንዳለባችሁ ግራ ለተጋባችሁ ሰዎች ከዚህ መልዕክት መጨረሻ ላይ የታመኑና የተረጋገጡ ምንጮችን ትቸተላችኋለሁንና እነርሱን መመልከት ትችላላችሁ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ምን ልትለን ትፈልጋለህ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ኃይለኛ ጫጫታ በበዛበት ወቅት በተለይም አይናችሁን ከእኔ ላይ ካነሳችሁ እናንተን መምራት ቀላል አይሆንም፡፡ እነዚህ ወቅቶች የብጥብጥና የማንፃት ጊዜያቶች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ፍፁም ቀላል የሆነ ጉዳይ አይደለም፡፡ በጥንቃቄ እንድታስቡ የምፈልገው በቅርቡ ሊሆን ላለው ንጥቀት ሰዎችን ሁሉ ወደእኔ ለመሳብ የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ ነው፡፡ በግራ መጋባት ወቅት እናንተ ብርሃንና የማትነቃነቁ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም መንገጫቀጮችና ታስበው የሚደረጉ የውሸት ክስተቶች ሰዉን ለበለጠ ግራ መጋባት በማጋለጥ ሰውን ሁሉ ከእውነት እያራቁት ይሄዳሉ፡፡

"ፕሬዜዳንት ትራንፕ እስካሁን የኔ ምርጫ እንደሆነ መቼም አውቃችኋል፡፡ ነገር ግን እርሱ እየተጋፈጠ ያለው ለመቶ አመታት ሲካሄድ ከነበረ ብልሽት ጋር ነው፡፡ በተለይም ለክፍለ ዘመን ሲካሄድ የነበረው የመንግስታችሁ ብልሽት እርሱ የፕሬዚዳንትነቱን ቢሮ ሲረከብ በቢሮው ውስጥ የጠበቀው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም አሜሪካን መልሶ ለመገንባት የራሱንና የልጆችን ህይወት አድጋ ላይ ጥሏል፡፡ የእናንተ ፀሎት ነው ህይወቱ እንዲጠበቅና ሥራውንም እንዲያስኬድ የረዳው፡፡ በአሁን ሰአት ከህብረተሰባችሁ ብዙ ዕረከን ያላቸው ተውኔቶች ናቸው እየተወገዱ ያሉት፡፡ እየጠለቅን በሄድን ቁጥር ፍፁም የሆነው የሰይጣን የጨለማ ሥራ እየተገለጡ ይሄዳሉ፡፡

"ለዚህ ነው አንድ የተበላሸ ነገር ሲገጥማችሁ ወደታችኛው መሰረት በመሄድ ማፅዳት መጀመር ያለባችሁ፡፡ አሁን እያያችሁ ያላችሁት የዛን ምልክት ነው፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ እየተጋፈጠ ያለው እጅግ ከበረታ ክፉ ጋር ስለሆነ ከምንግዜውም በበለጠ የእናንተ ፀሎት ያስፈልገዋል፡፡ በአሁን ጊዜ ሁለት ነገሮችን ነው እያያችሁ ያላችሁት ፡፡ አንዱ የተበላሸ መንግስት ሲሆን ሌላው ደግሞ ሊካድ የማይቻለው ከቻይና ጋር የሚገጥማችሁ የኑክላር ጦርነት ስጋት ነው፡፡

ሊገባችሁ የሚያስፈልገው ይህ በአንድ ሌሊት የመጣ ጉዳይ አይደለም፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ  እያደረገ ያለው ፈቀቅ ብሎ በመቆም ጠላት ራሱን እንዲያጋልጥ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም ትክክለኛው አጋጣሚ ሲመጣ እርምጃ መውሰድ ይጀምራል፡፡ እስከዛው ግን የእናንተ ትዕግስትና ድጋፍ ፍፁም አስፈላጊ ነው፡፡

"ክሌር  ቻይና አገራችሁን እንደምትወር ብዙ ራዕይና ህልም ሰጥቼሽ ነበር፡፡"

(ክሌር):- ጌታ ይህ እውነት ነው ነገር ግን እንዲህ ቅርብ አልመሰለኝም ነበር፡፡ አንዳንዱን አስታውሳለሁ፡፡ ለምሳሌ በባህሩ ዳርቻ በኩል ፍሎሪዳን ሲወሩ እንዲሁም ደግሞ የደፈጣ ተዋጊዎች በደቡብ ምስራቅ ጫካ ውስጥ ተደብቀው ማየቴን አስታውሳለሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." ክሌር ቻይናዎቹ አዳጋች ኃይሎች ናቸው፡፡ እነርሱ አገራችሁን ለመውሰድ ለብዙ አመታት ሲያቀዱና ሲጋጁ ነበር፡፡ በተጨማሪም እንዲህ ልበላችሁ እነርሱ በመጥፎ  ሁኔታ ውጤታማ ሊሆኑ ደርሰዋል፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ ከውስጥና ከውጪ ብዙ ግርግሮች ገጥመውታል፡፡ ነገር ግን እርሱ ጎበዝና በፊት የሰራውን ኃጢያት ሁሉ የተናዘዘ፣ በሚያስፈልገው ነገር ምክር ለመቀበል በእኔ ላይ የተደገፈ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ ለእርሱ የምታደርጉለት ነገር ቢኖር በአጠገቡ ያሉ ሰዎች ምንም ይበሉ ምንም እርሱ ግን የእኔን ድምፅና ፈቃድ ጥርት ባለ መልኩ መለየት እንዲችል እንድትፀልዩለት ነው፡፡ አብረውት ካሉ ከሁሉም ሰዎች በበለጠ ይህ ችሎታ ለእርሱ ያስፈልገዋል፡፡ እርሱ የፅድቅ ምንነት ይገባዋል ነገር ግን የሌሎቹ ጋጋታ ድምፅ አንዳንዴ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን በውስጡ ያለው የመለየት ችሎታ ጥሩ ነው፡፡

"እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ በመከራ እያሳለፈ ያለው ወቅት በምድር የወደደው ነገር ነው፡፡ በአጠገቡ ምን ያህል ከዳተኞች እንደሚያጋጥመው አልተገነዘበም ነበር፡፡ ይህ አጋጣሚ የሰው ልጆችን የውስጥ ፍላጎት የገለጠ እጅግ የሚያም ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እርሱ ሰው ብቻ ስለሆነ አንዳንድ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች በጥብጠውታል፡፡ ስለዚህም በልቡ ውስጥ ያለው ቁስልም እንዲፈወስ ፀልዩለት፡፡ እንዲሁም በልቡ መራራ ተክል እንዲበቅል ፈቃዱን እንዳይሰጥ ፀልዩለት፡፡ እውነተኛ ክርስቲያን ስትሆኑ ብዙ የምትማሩት ነገር አለ፡፡ ነገሩ አንቺና ህዝቄኤል "ህፃናት በአሸዋ ሳጥን ውስጥ ከሆኑ እናቶች ጉዳት የለባቸውም፡፡" እንደምትሉት ነው፡፡ ይቅር ያለማለት ከሁሉም ህመሞች ይልቅ ለማሸንፍ የሚያስቸግር ነው፡፡ በእኔ ፀጋ ግን ማሸነፍ ይችላል፡፡ የጥንት አባባል እንደሚል "ይቅር ያለማለት ለጠላትህ ያዘጋጀኸውን አንድ ኩባያ መርዝ አንተ ራስህ ጠጥተህ እርሱ ሳይጎዳ ነፃ ሆኖ ሲሄድ እንደማለት ነው፡፡"

"ይህንን አስታውሱ እርሱ እንደ ክርስቲያን፣ እንደ ፕሬዜዳንትና እንደ ፖለቲካኛ ሰው ገና እያደገ ነው፡፡ እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች ሁሉ ለእርሱ ገና አዲስ ናቸው፡፡ የተጎዳ ነፍስ የሚለው አመለካከት እንኳን ለእርሱ አዲስ ሐሳብ ነው፡፡ አንቺ በዚህ ዙሪያ ብዙ አስተምረሻል፡፡ በአለም ላሉት ግን ድካምና ህመም ፍርድ የሚሰጥበትና እንደ ቅጣት ተደርጎ የሚቆጠር እንጂ የበለጠ ፀጋን እንደሚያመጣ እንደ ፆም ስጦታ ተደርጎ አይቆጠርም፡፡

"ሁላችሁም እንድትረዱ የምፈልገው በግልም ይሁን በአለም የሚደንቅ ጥርመሳ እየመጣ ነው፡፡ ነገር ግን ሁላችሁንም ውድ ዋጋ ያስከፍላችኋል፡፡ መስዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ደም እስካሁንም የቤተ ክርስቲያን ዘር እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ እናም ቻይና ብዙዎች እስኪሞቱና ፍፁም እስከትሸነፍ ድረስ  ወደኋላ አትመለስም፡፡ በራሳችሁ ምድር ደም ይፈሳል፡፡ ነገር ግን

ደግሞ ይህንን አስታውሱ እኔ መጥቼ በምድር ላይ ከመግዛቴ በፊት በራዕይ የተፃፈው ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡ ይህ ነው አስቀያሚው የማንፃት ሂደት፡፡ ነገሩን የሚያስፈፅሙ ተዋንያን ሁሉ በመድረክ ላይ ናቸው፡፡ ንጥቀት ሲካሄድ ወዲያው ይጀምራል፡፡ እስከዚያው ግን መጨረስ ያለባችሁን ለመጨረስ የምትችሉትን ያህል እንድትሰሩ እፈልጋለሁ፡፡ መልዕክቶቼን ችላ አትበይ፡፡ ህዝቤ በየቀኑ ድምፄን መስማት ያስፈልገዋል፡፡

"የኔ ውዶች እንዲገባችሁ የሚያስፈልገው መልካም አጋጣሚ የሚኖረው በችግርና በመከራ ወቅት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ደግሞ በጣም የሚያም ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ አሮጌ ልማዶችና መንገዶች ሞተው አዲስና ትኩስ የሆነው የወይን ጠጅ መጠጫ መምጣት አለበት፡፡ ብዙ የሞቱ ሰዎች ከሙታን ሲነሱ የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ ማግኘቱና ትልቁ የማንፃት ጊዜ እንደሆነ ምስክር ይሆናሉ፡፡ ይህም ምስክርነት የተነጠቁ ሰዎች ተጠልፈው የተወሰዱት በኤሊየንስ ሳይሆን ስለ ንጥቀት የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ መሆኑን የሚገልፅ ስለሚሆን ነው፡፡ ብዙዎችም እንደ ሰማይ ከዋክብት ይደምቃሉ፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ለራሳቸው ህይወት ዋጋ ሳይሰጡ ለእኔ ምስክር ለመሆን ብቻ ስለሚኖሩ ነው፡፡ እንዲሁም ልጆች እንደ ታላቅ የእምነት ተዋጊዎች ይነሳሉ፡፡ ለማገልገል ዕድሉን በመጠባበቅ ላይ ያሉም ተቀብተው አገልግሎት ይጀምራሉ፡፡

"በጥልቀት መልኩ መከናወን ከምትጓጉት መካከል አብዛኛዎቻችሁ ጠርምሳችሁ ትወጣላችሁ፡፡ ይህንን አለምና ያላችሁን የክብር ሥፍራ ዋጋ ሰጥታችሁ የነበራችሁ አብዛኛዎቻችሁ ደግሞ ይህንን ሐሳብ ትታችሁ የኔን ምህረት፣ ክብር በማወጅና የግል ጥያቄያችሁን በመተው፣ ለእኔና ለፈቃዴ ብቻ በመኖር የነፃ ህይወት መኖር ትጀምራላችሁ፡፡ ሌሎች ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አለምን ፈልገው ወደኋላ በመመለስ ስም አልባ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ከእኔ ይልቅ አለምን መርጠዋልና ከእኔ እየራቁ እየራቁ ይሄዳሉ፡፡ ልጆቻችሁ ከእነዚህ ውስጥ እንዳይሆኑ ፀልዩ፡፡

"ደማቅ ቀይ ሰማይ ባያችሁ ጊዜ ነፃ የምትወጡበት ወቅት መሆኑንና ልወስዳችሁ እየመጣሁ እንደሆነ ያን ጊዜ ታውቃላችሁ፡፡"

*(ክሌር)፡- ጌታ በኒው ሜክሲኮ ፀሐይ ስትጠልቅ ብዙ ጊዜ በጣም ደማቅ ቀይ ነው፡፡*

ጌታም . . . " እያልኩ ያለሁት እንደ ደም የቀላ ማለቴ ነው፡፡ እንደ ደም የቀላ ሰማይ ሆኖ አንዳንድ ቦታ ላይ የጠቆረ ነው፡፡ እንዳውም የደረቀ ጥቁር ደም የሚመስልና ወፍራም ቀይ ሰማይ ነው፡፡ ይህም እስካሁን ካያችኋቸው የፀሐይ መጥለቆች በጣም የተለየ ነው፡፡ ይህንን ባያችሁ ጊዜ እኔ በበሩ ላይ እንደሆንኩና ጥሼ ልመጣ እንደተዘጋጀሁ እወቁ፡፡ አትፍሩ ነገር ግን እኔን ለመቀበልና ወደ ቤት ለመሄድ ራሳችሁንና ልባችሁን ቀና በማድረግ ደስ ይበላችሁ፡፡ ይህ አባባል ለእናንተ የማይመች ቢሆንም ተፈፅሞ ታዩታላችሁ፡፡

"ክሌር አምነሺኝ እየፃፍሽ ስለሆነ አመሰግንሻለሁ፡፡ ልጄ እባክሽ ጠንካራ እምነት ይኑርሽ ብዙ የምነግርሽ ነገር አለ፡፡ እባክሽ እምነትሽን አጠንክሪ፡፡ እናም የኔን ባህርይ አስታውሺ፡፡ ሙሽራዬ ዳቦ ስትጠይቀኝ ድንጋይ እሰጣታለሁን? እምነትሽን አጠንክሪና ብዙ ሚስጥራትን እገልጥልሻለሁ፡፡"

*(ክሌር)፡- ጌታ ይህንን እንዴት ማድረግ እችላለሁ?*

"መለስ ብለሽ የነበርሽበትን ህይወት ተመልከቺ፡፡ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ደርሰሽ የነበረበትን ጊዜና እኔ ደግሞ እንዴት እንደደረስኩልሽ አስቢ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሁልጊዜ ያንን እያስታወሱ ይኖራሉ፡፡ እና አንቺም እንደነርሱ መሆን ትፈልጊያለሽ፡፡ ስለዚህ እባክሽ ልብሽን ክፈቺና የመዳንን ብርሃንና የታማኝነቴን እውነት ተቀበዪ፡፡ በዚህ መልዕክት ላይ በማረፍ በክንዴ ላይ ለመደገፍ ተጠጊ፡፡ የልቤ ምት ያጠንክርሺ ደግሞም በረከቶቼ ያቁሙሽ፡፡ እንዲሁም ለሁላችሁ መልእክቱ ቃሌ የተሞላው የማይቻለውን በማድረግ የታሪክ ክንውኖች እንደሆነ በማስታወስ ለማይቻለው ነገር ልባችሁን ክፈቱ፡፡ እናም እየገባችሁበት ያለ ይህ ወቅት እስከዛሬ ታይቶ የማይታወቅና የማይቻል የሚባለውን ነገር በማከናወን በየዕለቱ የምትለማመዱበት ወቅት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው እኔን በብቸኝነት ለሚፈልጉና ልባቸውን ላዘጋጁ ነው፡፡

"በአለም ዙሪያ መቅሰፍቶች እየተከሰቱ ባለበት በዚህ ጊዜ፣ በህይወት ኖራችሁ የእኔ የፍቅርና የተስፋ መልዕክተኞች በመሆናችሁ በብዙ ብርታትና እምነት ወደፊት ቀጥሉ፡፡ ይህም ተስፋ ክፉ የሌለበትና ብልሽት አልባ የሆነው መንግስተ ሰማይና የዘላለም ህይወት ነው፡፡

*የጌታ መልዕክት በእዚህ ላይ ያበቃል፡፡ እየፀለያችሁልን ስለሆነ፣ ደግሞም ደብዳቤ ስለምትፅፉልንና ና ኢሜል ስለምታደርጉልን አመሰግናችኋለሁ፡፡ መልዕክቶቻችሁን ሁሉ ማንበብ ባለመቻሌ ግን ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ በተጨማሪም ስለምታደርጉልን ድጋፍ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡ ጌታ በሰላሙ ይባርካችሁ፡፡ ከዚህ በታች የፃፍኩላችሁን የታመኑ ምንጮች ማየት አትርሱ፡፡ ከእነዚህ ምንጮች ጥሩ ግንዛቤን መጨበጥ ትችላላችሁ፡፡*

**የደከሟችሁና ሁላችሁ ወደ እኔ ኑና አሳርፋችኋለሁ - ጄንዋሪ 31 ቀን 2021 ዓ.ም**

**Come Unto Me All Who Are Weary, January 31st, 2021**

ቤተሰቦቼ ከማያልቅ ከዚህ አለም የድራማ ህይወት ጌታ ወደ ዕረፍቱ ይሳባችሁ፡፡ አሜን፡፡

ውድ ቤተሰቦች በሃምሳዎቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ክብር እንደነበረውና ይህንንም የሚያደርጉ እንዴት ታማኝና መልካም ሰዎች እንደነበሩ እንዲሁም ቄሶችና መነኩሲቶች እንዴት ትልቅ ተደርገው እንደሚታሰቡ አስታውሳለሁ፡፡ እናም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ይፀልዩ የነበሩ ሰዎች የህብረተሰቡ የጀርባ አጥንት ነበሩ፡፡

ከሰላሳ ዓመታት በኋላ ግን በኢየሱስ ፍቅር በመነደፍ ለእርሱ ብቻ ለመኖር ወስኜ፣ በፋሽኑ አለም መጠመዱንና የብልፅግናውን ጎራ ጥዬ፣ ልማዴን ብቻ ይዤ ከአለም ተነጥዬ ስወጣ ሰዎች አይምሮዋ ትክክል አይደለም፣ ተታላለች፣ አይምሮዋ ታሟል ብለው ከሰሱኝ፡፡

ዛሬ ጠዋት የፕሬዚዳንቱ ጠበቃ የነበረው ሰው በቴሌግራም ላይ ያስተላለፈውን ለመመልከት ችዬ ነበር፡፡ ይህ ሰው አንድ ጊዜ ንግግር ሲያደርግ ሰምቼው ንግግሩ የጠበቃ ንግግር ሳይሆን የበለጠ የሰባኪ ዓይነት ስለነበር ደንቆኝ ነበር፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ እየጠቀሰ ሲናገር እንዲሁም በንግግሩ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ሲገልጥ ነበር፡፡ ይህ ሰው በሥራው ምንም እንከን ሳይገኝበት ለ35 አመታት በጆርጂያ የጥብቅና ሥራውን እየሰራ ያለ ሰው ነው፡፡ አሁን ግን የጆርጂያ ባር አሶሴሽን ወደ ሆስፒታል ሄዶ አይምሮውን እንዲመረመር፣ ካልተመረመረ ግን ህግ ላይ እንዲሰራ

የተሰጠውን የሥራ ፈቃድ እንደሚሰርዙበት እያስፈራሩት ነው፡፡ እግዚአብሔርን እጅግ ስለወደደ ብቻ ይህ ይደረጋል ብላችሁ ታምናላችሁ ???

ደግሞም ልጃችሁ በተፈጥሮ ያገኘውን ፆታ መጠበቅ ክፉ ነገር ሲሆን በትምህርት ቤቶች የፈለጉትን ፆታ እንዲመርጡ ማበረታታት ግን መልካም ነው!!! ይህንን ልታስቡት ወይም ልትረዱት እንኳን ትችላላችሁን? እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን ያለነው በመጨረሻው ዘመን ጫፍ ላይ ነው፡፡ በየትኛውም ዘመን ቢሆን የአለም ሞራል እንዲህ ከላይ ወደ ታች፣ ከውስጥ ወደ ውጪ ተገልብጦ አያውቅም፡፡ ደግሞ የምናወራው ስለ ትንሽ ቡድኖች አይደለም፡፡ በዚህ ዘመን እያየን ያለነው የቤተሰብ መበላሸት፣ ሱሰኝነት፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንደ መዝናኛ ማፅደቅ፣ እግዚአብሔር የለም የሚል የምሁራን አመለካከት እና የሞራል ዝቅጠት መቼም ታይቶ በማይታወቅ መጠን እየተስፋፋ መምጣቱን ነው፡፡ እነዚህ አመለካከቶች ባለፉት መቶ አመታት በጥንቃቄ ወደ ህዝቡ በጥቂት በጥቂቱ እየተለቀቁ ነበር፡፡ ይህም ጉሉኮስ በደም ስር በጠብታ እንደሚሰጥ አይነት መርዛቸውን ወደ ህዝባችን ልብ እንዲሁ እያስገቡ ነበር፡፡ ይህም የጀመረው በትምህርት ቤቶች መዋቅር፣ በውበት ኢንዱስትሪው ውስጥ ዱካውን በመጣል፣ በፋሽን ተንቀሳቃሽ ምስሎች አማካኝነት ነው፡፡ በእንዲህ አይነት መልኩ በጥንቃቄና በታቀደ መጠን እየተለቀቀ ነበር፡፡ ይህም የተደረገው እኛን በእብደት አፋፍ ላይ ለማውጣት፣ እንዲሁም የተፈጠሩበት ማንነታቸው የጠፋባቸውን፣ እንዲሁም እንዴት መኖር እንዳለባቸው ግራ የገባቸውን ቁጥር ለመጨመር ነው፡፡

የሚገርመው ነገር በተፈጥሮ ህግ መሰረት መኖር የምንፈልገውንና እግዚአብሔርን የምናመልከውን እንደ ጉድ ነው የሚመለከቱን፡፡ በእውነት ከልቤ ነው የምላችሁ በአለም ያሉት እኛን የሚመለከቱን የተታለልን ጎዶች አድርገው ነው፡፡ ፕሬዜዳንታችንም እየሰራ ያለው በዕድሜ ክልል ከ18 እስከ 50 አመት ያለውን የህብረተሰብ ክፍል የተጣመመ ነገርን ተቀብሎ የማድነቅን አመለካከት ለመቀየር ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ንፁህና መልካም ህይወት ለሚኖሩት ትዕግስት የሌላቸው ሰዎች ናቸው፡፡
ጌታ ለኸርት ድዌለርስ የምትላቸው ነገር አለ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . ."የደከማችሁና የዛላችሁ ሁላችሁ ወደ እኔ ኑና አሳርፋችኋለሁ፡፡ ህዝቦቼ በምድር ከሚኖሩት ውስጥ በእርግጥም አነስተኞች ናችሁ፡፡ ይህ ማለት ግን ወደ ምድር ለመላክ ያሰብኩት የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ክፉን በተቃራኒው መንገድ ሊቀለብሰው አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ለእግዚአብሔር የማይቻል ነገር የለም፡፡ እርግጥ ነው እየተቋቋምኩ ያለሁት ከተጣመመና ከተቆለመመ ትውልድ ጋር ነው፡፡ ቢሆንም ከእናንተ ውስጥ ደግሞ እውነትንና ፅድቅን የተራባችሁ አላችሁ፡፡ ስለዚህ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡

"አያችሁ በትክክለኛው ወቅት በአንድ ጀንበር ብዙ ለውጥ ሊመጣ ይችላል፡፡ እኔም እያቀድኩ ያለሁት በአለም ላይ ፍፁም የሆነ የእሴቶች ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ አይን ያላችሁ የምታዩ፣ ጆሮ ያላችሁ የምትሰሙ፤ ፅድቅን የተራባችሁና የተጠማችሁ፤ የጠፋችሁና እኔን የምትፈልጉ ለእናንተ ሁሉ በእርግጥም ተስፋ አለ፡፡

"እናንተ ህዝቦቼ ግን ለሌሎች ህዝቦች ብርሃን መሆን አለባችሁ፡፡ ፍቅሬ በእናንተ ውስጥ አንፀባርቆ መታየት ይኖርበታል፡፡ በዚህም ሌሎች ህዝቦች ለማየት የሚፈልጉትን በእናንተ ውስጥ ማየት ይችላሉ፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ወደ እኔ መገኘት ሊያስገቡአችሁ በሚችሉ መዝሙሮች ወደ ጠለቀ ፀሎት በመግባት ተለማመዱ፡፡ እነዚህም መዝሙሮች

እኔ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር፣ እናንተ ደግሞ ለእኔ ያላችሁን ፍቅር፤ እኔ እንዴት እንደምጠነቀቅላችሁ፣ እንዲሁም እኔን ምን ያህል እንደተራባችሁ የሚገልፁ መዝሙሮች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስለዚህም እኔንና እናንተን ሊያቀራርቡ የሚችሉ መዝሙሮችን ምረጡ፡፡ መዝሙሮች እየተዘመሩ እያሉ በእርግጥም እጎበኛችኋለሁ፡፡ ለመሆኑ ከእኔ ጋር ስንት ሰዓት ነው የምታሳልፉት? የኔን መገኘት ምን ያህል ትፈልጉታላችሁ? አንድ ሰአት? 2 ሰአት? 3 ሰአት? 12 ሰአት? ወይስ ቀናቶች?

"የተወደዳችሁ ይህ የእናንተ ምርጫ ነው፡፡ እኔ ግን የእናንተን አብሮነት እፈልገዋለሁ፡፡ ስለዚህም እናንተ የምትሰጡኝን አከብራለሁ፡፡ ከእኔ ጋር ያልተገናኛችሁ መስሎ ከታያችሁ የሬማ ካርድ ከሬማ ሳጥናችሁ ውስጥ ምረጡ፣ ወይም ልባችሁን ከሚነካው አንድ የመፅሐፍ ክፍል አንብቡ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልባችሁን መዝጋት ትታችሁ ለእኔ ለመክፈት የሚያስፈልገው ይኸውም ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ልቦች እንደ ነሐስ ግድግዳ የጠነከሩና ወደ ውስጥ ለመግባት የማይቻሉ ናቸው፡፡ ይህም የሆነው እኔ ለዚህ የማልገባ ነኝ ከሚል አስተሳሰብ ከመጣ የሃፍረት ስሜት ነው፡፡ ከእውነት ሊርቅ የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡ እኔን የምትናፍቁ ከሆነ እኔም እናንተን ለመንካት እናፍቃለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምን ያህል እንደምትፈልጉኝ የማጣራበት መንገድ እኔ እስከመጣ ምን ያህል እንደምትጠብቁኝ በማየት ነው፡፡

"አምላካችሁን በመዳፈርና እርሱን በማየትና በመስማት ያለውን ልዩ ሙብት በመረዳት መካከል ሚዛን አለ፡፡ ነገር ግን እንድትረዱ የምፈልገው ከእኔ ጋር በመቀራረብ በምታሳልፉት ጊዜ የሚገጥማችሁ ደስታ፣ አብረን የምናሳልፈው ጣፋጭ ጊዜ፣ እርጋታውና ክብሩን መሞላታችሁ ነው የፍቅሬ አምባሳደር ለመሆን የሚያስፈልጋችሁ፡፡ ሰው ማንን ይመስላል ብትሉ አብሮት የሚያሳልፈውን ሰው ነው የሚመስለው፡፡ በኢንተርኔት ላይ ብዙ ጊዜያችሁን እንዳታጠፉ የምፈልገውም አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ እንድትመስሉ የምፈልገው እኔን እንጂ በአለም ያሉትን አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜያችሁን መፅሐፍ ቅዱስ በማንበብና በመስማት፣ መዝሙር በማዳመጥ፣ እንዲሁም ቅዱሳን መፅሐፍቶችን በማንበብ ለምሳሌ የቅዱሳንን የህይወት ታሪክ በማንበብ ጊዜያችሁን ባሳለፋችሁ ቁጥር የበለጠ እኔን እየመሰላችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ ይህም ሆኖ ግን የእኔን እውነተኛ መገኘት የሚተካ ነገር የለም፡፡

"በሥጋ ወደሙ እኔን ስትቀበሉ የተጨበጠ መገኘቴንና ለቀኑ የሚያስፈልጋችሁን ቅባት ላካፍላችሁ እንደምናፍቅ ልትገነዘቡ ይገባል፡፡ ይህ ጊዜ ደግሞ ለእናንተ የምገኝበት፣ ምናልባትም ድምፄን ልትሰሙና ፊቴን ልታዩ የምትችሉበት፣ እንዲሁም ለእናንተ ያለኝን ፍቅር ልትገነዘቡ የምትችሉበት ጊዜ ነው፡፡ በቀደመው ዘመናችሁ ፍቅር ይዟችሁ በነበረ ጊዜ፣ የምትፈልጉት አንድ ነገር ቢኖር አንዳችሁ ለአንዳችሁ መገኘታችሁ ብቻ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ የወደዳችሁትን ሰው ድምፅ ለመስማት፣ አይኑን ለማየትና ቅርብ ለመሆን ትፈልጉ ነበር፡፡ በስልክ ማውራቱም ለሰአታት የሚቆይ ነበር፡፡ እንዲሁም ከምትወዱት ሰው ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ሲኖራችሁ በተቻላችሁ መጠን ራሳችሁን በማስዋብ ትቀርቡ ነበር፡፡ አብራችሁ የምታሳልፉት ጊዜ ሰላማዊና አስደሳች፣ የሚመችና ጥሩ እንዲሆን የተቻላችሁን ሁሉ ለማድረግ ትጥሩ ነበር፡፡

"የኔ ውዶች ይህ እኔና እናንተ ተለያይተን ያለንበት፣ እናንተም እኔን በመጠባበቅ ላይ ያላችሁት ይህ ህይወት እጅግ የሚያምና አሰቃቂ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ በፍቅሬ ላጥለቀልቃችሁ እንደምጠባበቅና በክንዴ ላቅፋችሁ እንደምናፍቅ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ ይህ አለም እኔ ካዘጋጀሁላችሁ ሥፍራ ጋር ሲወዳደር የዘቀጠና መጥፎ ሥፍራ ነው፡፡ ስለዚህም ወደ ራሴ ልወስዳችሁ እናፍቃለሁ፡፡

"ይህም ሆኖ ግን በአባቴ የወይን አትክልት ሥፍራ ደግሞ ተባባሪ ሰራተኞች እንደሆንን አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም ለዘላለም ከእኔ ጋር እንድትኖሩ ከመውሰዴ በፊት ለእኔ ህመም ቢሆንም እንኳን መጠበቅ አለብኝ፡፡ በተለይም

እየተጓዛችሁበት ስላለውና ወደፊትም ስለሚጠብቃችሁ ፈተና ስመለከት ቶሎ እንዲያበቃ ምኞቴ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ሊመጣ ያለውን ያንን ቀን መጠበቅ ለእኔ ራስን የመካድ ትልቅ ሥራ ነው፡፡ ቀኑ ዛሬ ይሆን ብዬ በመጓጓት በእያንዳንዱ ቀን የአባቴን ምልክቶችና አስተያየቱን አጤናለሁ፡፡ "ቀኑ ዛሬ ነው? የሚለውን ጥያቄዬን ለአባቴ አቀርብና መልሱ "ልጄ ገና ነው" የሚል እንደሆነ ስረዳ ልቤ ዝቅ ይልብኝና በትልቁ እተነፍሳለሁ፡፡ እውነቴን ነው የምላችሁ ከእኔ ጋር እንድትሆኑ በጣም ነው የምፈልገው፡፡ ይህንን አይነት መናፈቅ ሊኖረው የሚችለው ፈጣሪያችሁ ብቻ ነው፡፡

"በዚህም ምክንያት በየቀኑ ለእኔ ጊዜ እንዲኖራችሁ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ለእኔም ስቃይ ስለሆነ መለያየትን አስወግዱ፡፡ ፍቅር በተሞላበት ቃላችሁና በአምልኮ ልቤን አፅናኑ፡፡ ትራስ ይዛችሁ ወደ ልባችሁ በማቅረብ ፍቅሬንና መገኘቴን አሰላስሉ፡፡ እኔ ወደምኖርበት ሚስጥራዊ ወደሆነው ወደ ልባችሁ የአትክልት ሥፍራ ግቡ፡፡ በዛም በእኔ መገኘት ምክንያት የሚወጣውን መልካም መንፈሳዊ ሽታ ውሰዱ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ለማንም ሳይሆን ለእኔ ብቻ ብላችሁ ይህንን ስላደረጋችሁ ትክክል መሆናችሁን ማረጋገጫ ለመስጠትና ደስታዬን ለመግለፅ ፍቅሬን በላያችሁና በዙሪያችሁ አፈሳለሁ፡፡ የኔ ውዶች እመኑኝ ይህንን የፍቅር ቃል እመኑ፡፡ ይህንን ቃል የማፈስላችሁ ከሚናፍቀው ልቤ ውስጥ ነው፡፡ ቀኑ ደርሶ ለዘላለም አብረን አንድ ላይ እስከንሆን ድረስ እነዚህ የእኔ የፍቅር ደብዳቤዎች ናቸው፡፡"

### የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያ - የራስ ቁር - ፌብርዋሪ 4 ቀን 2021 ዓ.ም
### The Armor of God-Helmet, February 4th, 2021

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." መንግስታት የተሳሳተ መረጃን በመጠቀም ተቃዋሚዎቻቸውን እንዴት እንደሚያሳስቱበት ተመልክተሻል ፡፡ የሰይጣን አገልጋዮችም ሰው ሊገምተው ከሚችለው በላይ ይህንን ዘዴ የሚጠቀሙና በዚህም የሰለጠኑ ናቸው፡፡ ዋናው ዓላማቸው አንድን ሰው በማሳት የወደፊቱን የዕጣ ፈንታ አቅጣጫውን እንዲቀይር ማድረግ ነው፡፡ በቀላሉ የምታምኚና ለማወቅ ያለሽንም ጉጉት በመጠቀም በቀላሉ ተጫውተውብሻል፡፡ ይህንንም ሲናገር "ከባዱን መንገድ ያልተጠቀሙት አስፈላጊ ስላልሆነ ነው" ብዬ አሰብኩ፡፡

ጌታም "አሁን የራስ ቁር አስፈላጊ መሆኑን እያገናዘብሽ መጥተሻል፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥ የሚያስፈልግ ነገር ነው፡፡ ይህንንም መመሪያ የምሰጠው ደግሞ ግንባር ቀደም ለሆኑትና ለመሪዎቻቸው ነው፡፡ ነገር ግን ሰነፎችና የምታምኑት በግማሽ ልብ ከሆነ ልትጠቀሙበት አትችሉም፡፡ ክሌር የራስ ቁሩን ተጠቀሚ፡፡ አሁን የራስ ቁሩን መጠቀም ጥበብና በእውነትም አስፈላጊ መሆኑን በመረዳትሽ ፈተና ሲያጋጥምሽ ጠንካራ እንድትሆኚ ተጨማሪ መመሪያ እሰጥሻለሁ፡፡

የመዳን ራስ ቁር ወደ ጭንቅላታሽ ጥልቅ በመግባት ከዚህ አለም እንዳዳንኩሽና አዲስ ፍጥረት እንደሆንሽ የሚያመለክት ነው፡፡ የምድራዊ ነገሮች ሁሉ፣ የምትሳቢባቸው ነገሮች ሁሉ፣ ፍላጎቶችሽ፣ ስህተቶችሽ ፣ አመፃዎችሽ ወዘተ ሁሉ በደሜ ተሸፍነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ቀይ የራስ ቁር ስታዪ በደሜ እንደተሸፈንሽ ያስታውስሻል፡፡

ብዙ ነገሮች በአንቺ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉት ከአስተሳሰብሽ የተነሳ ስለሆነ ድክመትሽን ማወቅ አለብሽ፡፡ እነዚህም ስለራስሽ በአሉታዊ ሁኔታ እንድታስቢ የሚያደርጉሽ አመለካከቶች ናቸው፡፡ "በአሉታዊ ሁኔታ " ስል ለማለት የፈለግሁት ከአለም ይዘሽ የመጣሻቸው የግል ፀባዮች፣ አመለካከቶችና ሁኔታዎች ሲሆኑ እነዚህም ማማረር፣ መበሳጨት፣ ስህተትን መፈለግ፣ መፍረድ፣ የፈለጉትን ያለገደብ ማድረግ፣ ነፃ አመለካከት፣ ከሚያስፈልገው በላይ

ያለገደብ መመርመር፣ መርዝ ሊሆን የሚችል ነገርን ያለገደብ የማወቅ ፍቅር ፣ ለራስ ማዘን፣ የማልረባ ነኝ ብሎ በማመን ራስን ዝቅ በማድረግ ሳያቋርጡ ራስን በሐሳብ መቀጥቀጥ ወይም መጉዳት እንደ ምሳሌ የሚወሰዱ ናቸው።"

(ክሌር)፡- በነገራችን ላይ ነገሮች እኔ እንዳሰብኩት ሳይሆን ሲቀር አሉታዊ አባባሎችን ላለመጠቀም ወይም ለመቀልበስ ዘዴ አግኝቻለሁ። ለምሳሌ ውኃ ማሞቂያው ተበላሸ እንበል . . . ለነገሩ በዚህ በምንኖርበት ተራራማ ቦታ እንኳን ሙቅ ውኃ የቧንቧ ውኃ እንኳን ኖሮን አያውቅም ነበር። ነገር ግን ከመካከላችን ለሚገኝ አንድ ሰው ምስጋና ይግባውና ልምዱ ስለነበረው ሰርቶልን አሁን አለን። እናም 'ይህ ደደብ የውኃ ማሞቂያ' ብዬ ከማማረር ራሴን ቆጠብ በማድረግ ወዲያው ንስሐ እገባና "ጌታ የቧንቧ ውኃ ስላለን አመሰግንሃለሁ" እላለሁ። ይህንን ስል ደግሞ ከልቤ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በፊት ጊዜ የሚያስፈልገንን ውኃ ለማግኘት ትልቅ ጀሪካን ተሸክመን ወደ ተራራው እንዴት እናመጣ እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለዚህም ለእያንዳንዱ ነገር ማማረር ከአንደበቴ እንዳይወጣ ይህንን ህግ እጠቀማለሁ። ይህ ደግሞ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ይመስለኛል። ከዚህ ሁሉ ደግሞ እነዚህ ጥቃቅን የማይመቹ ነገሮች ፀሎቶቻችን የሚደግፉ እንደ ፆም ስጦታ ተደርገው ለጌታ ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው።

*ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." ጠላት በእነዚህ አይነት አስተሳሰቦች እጅግ የተካነ ነው። እርሱ ወላጆችሽ በእነዚህ ፀባዮች እንዴት እየመሩ ቀርፀው እንዳሳደጉሽ አይቷል።*

*(ክሌር)፡ - እንደ እውነቱ ከሆነ አባት ስለሌለኝ በአንድ ወላጅ ነበር ያደግሁት።*

ኢየሱስም . . . " ለዚህ ነው ትውልድ የሚሰነካከለው። በህፃናቱ ውስጥ አንዴ አሉታዊ አመለካከት ከተመሰረተ የሚለውጥ ትልቅ ነገር በህይወታቸው ተከስቶ ጎትቶ ካላወጣቸው በስተቀር እድሜ ልካቸውን እንዲህ ሆነው ነው የሚቀሩት። ነገር ግን ልብ በሉ እነዚህን አሉታዊ አመለካከቶችን ያሸነፈ አንድ ነፍስ በማንኛውም ጊዜ በህይወቱ መሰናክል ይገጥመዋል። ለምሳሌ እንደ ህመም፣ ሥራ ማጣት፣ ፕሮጀክቶችን ያለማጠናቀቅ፣ ትዳር መፍታት ወይም አደጋ የመሳሰሉ ስቃዮችን ያስተናግዳል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ወደነበሩበት አሉታዊ ሁኔታ ሊመለሱና ራሳቸውን ከአለም ጋር እያወዳደሩ ለምንም ነገር በቂ አይደለሁም ብለው ራሳቸውን ይቆጥራሉ። ይህ ደግሞ ተስፋ ስለሚያስቆርጣቸው ሁሉን ነገር ለመተው ወይም ራሳቸውን ለመግደል ይፈልጋሉ። ይህ ሁኔታ ለብዙ ጊዜ ከቀጠለ እስካሁን እጅግ ታግለው ያሸነፉት ነገር ሊያጡና ቀላሉን ህይወት በቂ ነው በማለት የአሸናፊነት ህይወት ራዕይ የነበራቸውን በመተው ራሳቸውን አደላድለው ሊቀመጡ ይችላሉ።

"ሰውነት የተጎዱትን እነዚያን ክፍሎች እንዲጠግን ተደርጎ የተሰራ ነው።። ስለዚህም በቀደሙት ጊዜያት እነዚህን ነገሮች አሸንፋችኋቸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንቺና ባለቤትሽ እንደገጠማችሁ አይነት በሚያሰቃይ ህመም ስትጠቁ ሰውነት አውንታዊ የሆኑ አመለካከት ኬሚካሎችን ከጭንቅላታችሁ ህመም ወዳለበት ሥፍራ በማጓጓዝ ከጭንቅላት ክፍል ሐሳብንና አውንታዊ ሽፋን እንዲያካሂድ የሚያደርገውን ሥራ ላይ እንዲውል ያደርገዋል። እናንተ ደግሞ ከዚያ በኋላ ድፐርት ውስጥ በመግባት ወጣት ሆናችሁ ወዳሸነፋችሁት አሉታዊ አመለካከት ትመለሳላችሁ። የኔ ፍቅር አንቺ በእነዚህ ነገሮች ህይወትሽን ሁሉ እንደ ሚዛን አንዴ ወዲህ አንዴ ወዲያ ስትዪ በትግል ነው ያሳለፍሽው። እኔና አንቺ አሁን እዚህ ተቀምጠን የምናወራው ያለፈውን ህይወትሽን በማሸነፍ እንድትቀጥይ ለማድረግና ከዚያም ባለፈ ከአንቺ በኋላ ለሚመጡትና በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚጠቁት የሚያስፈልግውን ላካፍልሽ ነው።"

(ክሌር)፡- እንደ እውነቱ ከሆነ ጌታ ስለዚህ ነገር እያወራ እያለ መጥፎ ስሜት እየተሰማኝ ነው ያለው፡፡ ለምን እንደዚህ እየተሰማኝ እንደሆነ እንኳን አላውቅም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ቀጠለ፡፡

"በፍፁም በዛ መንገድ አትሂጂ፡፡ እኔ እዚህ ያለሁት ፍፁም አዲስ በሆነ መንገድ ልመራሽ ነው፡፡ በህይወትሽ የነበረውን ክንድ ለምሳሌ ህይወትሽን እንዴት መምራት እንዳለብሽ የነበረው የቤተሰቦችሽ በጎም ይሁን መጥፎ  ተፅዕኖ መሸነፍን ሊያመጣና ለራስሽ እንድታዝኚ ወይም መራራ እንድትሆኚ ሊያደርግሽ ይችላል፡፡ ነገር ግን እኔ እዚህ ያለሁት ይህንን ፍፁም ልቀይረው እንደምችልና ተስፋ እንዳለ ልነግርሽ ነው፡፡ በዛን ጊዜ በህይወቷ ራሷን ተሸናፊ አድርጋ እንደቆጠረችው ኮረዳ አይነት አሁን መሆን የለብሽም፡፡"

(ክሌር)፡ - ጌታ እኔ ራሴን እንደዛ የምመለከትበት፣ ደግሞ ያ በጣም አስቀያሚ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡
ኢየሱስም . . . "የዚህ አስተሳሰብ ግማሹ የእድሜ ጉዳይ ሲሆን ግማሹ ደግሞ ኢጋንንቶች ውድቀትሽን ስለሚያስታውሱሽ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ፀጋ የሚመጣው፡፡ በተለይም ከሙሉ የጦር እቃ ልብስና ከራስ ቁር ጋር የሚመጣ ፀጋ ነው፡፡ ሌሎቹ ፀጋዎች የሚመጡት በትክክለኛው አመለካከትና ክብር በማምለክና ሥጋና ደሜን በመውሰድ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ማተኮር የምፈልገው የራስ ቁር ላይ ነው፡፡

"ህዝቤ እያንዳንዳችሁ የሚጎድላችሁ ነገር በአንድም ይሁን በሌላ የተለያየ ነው፡፡ እዚህጋ ነው ነገሩን በማወቅ የጦር መሳሪያችሁን ለማጠንከር መወሰን ያለባችሁ፡፡ ይህም "ካልሺየምና ማግኒዚየም ለአጥንቶቼ  ያስፈልጋቸዋል" በማለት በእውቀት እንደምትወስኑት አይነት ውሳኔ ማለት ነው፡፡ በየትኛው ነገር ራሳችሁን ማጠንከር እንዳለባችሁ ለመወሰን ነፃነት አላችሁ፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ አታስቡም፡፡ ለዚህ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት እየሰጠሁ ያለሁት፡፡ ስለዚህም በዚህ መንገድ ማሰብ አለባችሁ፡፡ መርዛማ በሆነ አመለካከት የተጎዳችሁ ሁላችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት ሳልወስዳችሁ እዚሁ እያላችሁ እነዚህን አመለካከቶች እንድታሸንፏቸው እፈልጋለሁ፡፡ በመንግስተ ሰማያት በተፈጥሯችሁ ውስጥ የቀረውን ማንኛውንም ነገር በህይወት ወንዝ ዳር የበቀሉ ዛፎች ቅጠል ይፈውሷችኋል፡፡

"ሌሎች ሰዎች ሳይመቻችሁ ሲቀሩ በአንዴ ተቀብላችሁ በአሉታዊ አመለካከት ታዮአቸዋላችሁ? ይህንን ልታስወግዱ የምትችሉት በምስጋና መንፈስ የራስ ቁር ውስጡን በመሸፈን ነው፡፡ ይህንንም የምታደርጉት  እግዚአብሔርን ስለእነዛ ሰዎች በማመስገንና ሰዎቹ በህይወታችሁ ያላቸውን ሥፍራ በማጤን ነው፡፡ አብዛኞቹ በእድሜ የገፉ ሰዎች ለብቻቸው እንደሆኑና ከፊልምና ከሌሎች መዝናኛዎች ውጪ እናንተም ብቻችሁን ልትሆኑ ትችሉ ነበር፡፡ አሉታዊው ሁኔታ እንዲቀጥል ካደረጋችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስና አምልኮ ደካማ እንዲሆን ታደርጋላችሁ፡፡ እንዲሁም አካል የለበስ፣ መንፈስ ያለው መደበቂያ ብቻ ትሆናላችሁ፡፡

"በዚህም ምክንያት የራስ ቁር የውጪ ክፍል በደም የተሸፈነ እንዲሆን ሦስት ኢንች ውፍረት ያለው ቀይ ብረት፣ እንዲሁም በውስጥ በኩል በንፁህ ወርቅ ዙሪያውን የተሰራ በማስታወሻ ፎም የተለበደና በእርከኖች ወይም በደረጃዎች የተከፋፈለ እንዲሆን አድርጌያለሁ፡፡ አሁን ስትመለከቱ የምታገኙት ብርሃን የሚያስተላልፍ የሚያበራ አይምሮ በራስ ቁር ውስጥ የሆነ ምስል ነው፡፡ ይህ ደግሞ በእኔ አይምሮ የተሞላው የእኔ ጭንቅላት ነው፡፡ ስለዚህም የራስ ቁሩን ራሳችሁ ላይ ስታደርጉት የእኔ አይምሮ በእናንተ ውስጥ በመግባት ፍፁም ተስማማሚ ይሆናል፡፡ እየሰጠኋችሁ ያለሁት ሙሉ

ለሙሉ በብረት የተሸፈነውን መሳሪያ ፣ በእኔ ማዳንና ቅድስና የተሸፈነውን፣ በወርቅ የተለበደውንና ማጥለያ የሆነውን፣ ለእያንዳንዱ እንደሚያስፈልጋችሁ የሚሰጠውን የክርስቶስን አይምሮ ነው፡፡

"አሁን ስለ ማጥለያዎች ልናገር፡፡ እነዚህን ማጥለያዎች በየቀኑ እንደሚገጥማችሁ የትግል ህይወት መጠን ያህል ሊኖራችሁ ይችላል፡፡ ክሌር ለአንቺ የሚያስፈልገው በመጀመሪያው እርከን በጭንቅላትሽ ቅርበት በኩል ንፁህ የሆነ፣ ያልተቀላቀለና በደስታ የሚቀርብ ምስጋና፣ በሁለተኛው እርከን ደግሞ ምክንያት የሌለው ፍቅርና ቸርነት፣ በመጨረሻም በውጪው የእርከን ክፍል በፅናት የተያያዘ አልሸነፍም የሚል ብርታት ነው፡፡ ይህ እጅግ እውነት የሆነ የራስ ቁር ነው፡፡ ይህንን ለአንቺ የፈጠርኩት ነው፡፡ በውስጥ በኩል የኔ የአይምሮ ሥራዎች ከአንቺ የህይወት ተሞክሮዎች ጋር በተመለከተ፣ ምክንያቱም አይምሮሽ በደንብ የታጠቀ ነው፡፡(ክሌርም - የማስበውን ሁሉ ይመለከተዋል) ኢሱስም . . .

"አዎ የብረቱ ክፍል ሊሆን የሚችል አንድ ዕርከን እርሱም የትዕግስት እርከን ልትጨምሪበት ትችያለሽ፡፡ በዚህም በልምድ የጠነከረው ነገር የብረቱ አካል በመሆኑ ብረቱ በእሳቱ ሲቀልጥ ትዕግስትን ይፈጥራል፡፡

አሁን ይህንን አንድ ላይ በማድረግ እንዲህ ብለሽ መፀለይ ትችያለሽ "በደሙ የተሸፈነ የክርስቶስ ልብ አለኝ፡፡ ለማወቅ የሚስፈልገኝን ነገር ሁሉ፣ ዓላማዬን ለመፈፀም የሚያነሳሳኝና የሚቀሰቅሰኝ ነገር ሁሉ ያለው አሁን አንተ ጌታዬ ከምትሰጠኝ ከዚህ የራስ ቁር ውስጥ ነው፡፡"

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." ይህንን በየቀኑ ስታደርጊ ከባዱን ነገር ለመሥራት ፈቃደኛ እየሆንሽ ትሄጃለሽ፡፡ ሌሎችንም የጦር መሳሪያዎች ደግሞ እንዲሁ እነግርሻለሁ፡፡

"የተወደዳችሁ ሁላችሁ፣ ለእናንተ ማለት የምፈልገው ባለ ጥንካሪያችሁ ሁሉ እኔን አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ አይናችሁን ከእኔ ላይ አታንሱ፣ ወይም እንዲያድኗችሁ ጓደኞቻችሁን፣ መንግስትን ቢሆን፣ ማንንም አትመልከቱ፡፡ ገንዘብንም ቢሆን አትመልከቱ፡፡ እናንተን ማዳን የኔ ሥራ ነው፡፡ እናንተን ማዳንና መጠበቅ የኔ የልቤ ፍላጎት ነው፡፡ ነገር ግን አስቀያሚውን የአለም አመለካከት በእናንተ ላይ ምልክቱን ሲተውና ወደታች ሲያደርጋችሁ ለእኔ ከባድ ታደርጉብኛላችሁ፡፡ ስለዚህም በቀናችሁ ውስጥ ብዙዎች ለማየት የሚጓጉለትን፣ ነገር ግን እናንተ ብቻ ልታዩት የተዘጋጀ አንድ ትልቅ ነገር እንደምሰራ በማመንና በመጠባበቅ በአውንታዊ አመለካከት ፀንታችሁ ቁሙ፡፡"

**የሚሊኒየሙ የወንድማማቾች አንድነት - ፌብራዋሪ 8 ቀን 2021 ዓ.ም**

**Shoulder to Shoulder Unity, Feb 8, 2021**

ቤተሰቦቼ ከንፁህ ህሊናና ልብ የሚመጣ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡ ጌታ ስለ አካሉ አንድነት እንዲህ በማለት ተናግሮኛል፡፡

"በአካሌ ውስጥ ያለውን አንድነት ኮትኩታችሁ እንድታሳድጉት እፈልጋለሁ፡፡ በመካከላችሁ በሚገኝ የእምነት ልዩነት(doctrine) ምክንያት መለያየት እንዲኖር አትፍቀዱ፡፡ በዚህ ሚሊኒየም ከምንግዜም በበለጠ እጅ ለእጅ በመያያዝ አንድ ሆናችሁ እንድትጓዙ የምፈልግበት ጊዜ ነው፡፡ ጠላት እናንተን በመከፋፈል ለማለያየት የተቻለውን ሁሉ

ይጥራል፡፡ ይህም ህብረት እንዳታደርጉ፣ አብራችሁ እንዳትፀልዩና መልካም ምክር እንዳይኖር ነው፡፡ ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የትኞቹ ጉዳዮች ሳይንቀሳቀሱ እዛው ባለበት እንደቀረ ታውቃላችሁ፡፡ ነገር ግን ማስታወስ ያለባችሁ እናንተም ህይወታቸውን በሙሉ በልዩ ሁኔታ ያሳለፉት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆናችሁን ነው፡፡ በፊቴ ስትቆሙ ለመንግስተ ሰማያት ወይም ለሹመት የሚያበቃችሁ እውቀታችሁ ወይም ችሎታችሁ ሳይሆን አስቸጋሪ የሆነውን ሰው እንኳን ይቅር ማለት መቻላችሁና ማፍቀራችሁ እንዲሁም ቁስሎቻችሁን ይቅር በማለት በእኔ ዕይታ ማየት ስትችሉ ነው፡፡

"በአካሌ ውስጥ ገደብ የሌለው መውደድ ተረስቷል፡፡ እነርሱ ከሚያምኑት አንድ የእምነት ክፍል የተለየ ከሆነ ህፃኑን ከገንዳው ውስጥ አውጥተው ይወረውሩታል፡፡ ብዙዎች ከእምነቱ የተወሰነውን ክፍል ሌሎች ያልተረዱት እነርሱ ግን የተረዱት ነገር አለ፡፡ ነገር ግን ከፍርድ፣ ከኩራትና ከሃይማኖት መንፈስ የተነሳ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎ ያለውን እነርሱ ከተረዱት የተለየ መረዳት ያለውን ማንም ሰው ብቁ አይደለም ብሎ ለመፈረጅ ፈጣኖች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስድስት ውስጥ ሥጋዬና ደሜ እውነተኛ መብልና መጠጥ እንደሆነ ሰባት ጊዜ የተናገርኩትን እውነታ ችላ ይሉታል፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ክፍል በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ስለ አንድ ጉዳይ ሰባት ጊዜ የተናገርኩበት ቦታ የለም፡፡

"ይህ ተራ ዳቦና ወይን እንዴት ተቀይሮ የኔ ሥጋና ደም ሊሆን ይችላል? ይህ ሊሆን የሚችለው የተሾመው አገልጋይ "አባት ሆይ ይህንን የቀረበውን ዳቦና ወይን የልጅህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ስጦታ አድርገህ እንድትሰጠን መንፈስህን ላክልን" ብሎ ሲፀልይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይህ ይሆናል፡፡

"ይህ ከላይ የተገለፀው እያንዳንዱ ቃል ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ይህንን የሚያደርጉትን አገልጋዮች አስማትን ይፈፅማሉ በማለት ብዙዎች ይከሷቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ደግሞ የሰይጣን ነው ማለት የሚያስከትለውን ነገር ነግሬያችኋለሁ፡፡ ነገር ግን እናንተ እውነቱን ለማወቅ በእርግጥ ፈልገው ካልጠየቋችሁ በስተቀር በዚህ ነጥብ ላይ መከራከር የለባችሁም፡፡ ከዚህ በላይ መሄድ አያስፈልግም አንድ ቀን እውነቱን ሊረዱ ይችላሉ፡፡ አሁን የምፈልገው አካሌ ሙሉ ለሙሉ ታጥቀው ሳይከፋፈሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደፊት እንዲሄዱ ነው፡፡

"የወንድማማች ፍቅርና ትህትና ሳይኖር እንዲሁም ቅን በሆነ መንገድ ራሳችሁን ማወቅ ካልቻላችሁ በስተቀር ይህም ምንም ያህል የቲዎሎጂ ዲግሪ ቢኖራችሁ፣ ወይም ምንም ያህል ታምራት በእጃችሁ ብፈፅም፣ በልባችሁ ግን ገና ያላወቃችሁት ነገር እንዳለ ወይም ሙሉ ለሙሉ ያልገባችሁ ነገር እንዳለ ካላመናችሁ በስተቀር ዋጋ የለውም፡፡ ይህንን አይነት ትህትና ከሌላችሁ በስተቀር ቤተ ክርስቲያኔን ከመጥቀም ይልቅ የበለጠ ጉዳት ታስከትላላችሁ እንጂ አንድነትን በማበረታታት እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ ከፉን አትቃወሙም፡፡ ይህ ደግሞ እኔ ብቻ ትክክል ነኝ የሚለውን ለማሳየት መከፋፈልን የሚያመጣውን የሃይማኖት መንፈስ በመለማመድ ሥራ ይበዛባችኋል፡፡

"አንድነት ምን ማለት እንደሆነ የምትረዱበት ጊዜ በፊታችሁ እየመጣ ነው፡፡ ይህም በጦርነት ውስጥ ላሉትና ለታናናሽ ነፍሶች የመከላከል ተግባርን ለሚፈፅሙ ይህ ማለት ህይወት ወይም ሞት ነው፡፡ ህዝቤ ፍቅር የእግዚአብሔር ስለሆነ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ በመንግስተ ሰማያት ለአባቴ ክብርን ሲያመጡ የወንድማማች

ፍቅርን በመጉዳት ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ደግሞ በእምነቱ ላይ ውርደትን ያመጣሉ፡፡ በእኔ ምክንያት ያሟችሁን ይቅር በማለት ፀልዩላቸውና ነገሩን ተዉት፡፡ በልባችሁ መርዝን አታኑሩ፡፡ ልባችሁ መራራ ተክልን ለማብቀል የሚያመቺ መሬት እንዲሆን አትፍቀዱ፡፡

"በዚህ ጊዜ ለህዝቤ ለመልቀቅ የምፈልገው ብዙ ፀጋዎች አሉ፡፡ እነዚህን ፀጋዎች በንፅህናና በጥሩ ልብ ለመሸከም ግን ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ ሁሉ የሚቀድመው ግን ጠላቶቻችሁን መውደድና እርስ በእርሳችሁ መዋደድ ነው፡፡

"ምንም እንዳልሆኑ ራሳቸውን የሚቆጥሩና ሁሉ ነገራቸው እኔ እንደሆንኩ  የሚያስቡ ነፍሶች ናቸው የመንግስቱን ኃብት ፀጋ አድርገው በመቀበል የሚታጠቁና ራሳቸውን የፍቅር አምባሳደር የሚያደርጉ፡፡ እነዚህን ነፍሶች ነው አምኜ የሚበልጥ ስጦታዎችን የምሰጣቸው፡፡ እነዚህ በሚመጣው ታላቅ የመከር ወቅት ትልቁን መከር የሚሰበስቡ ናቸው፡፡

"ጠላት በዚህ አገር ውስጥ ራሱን በአንድ ላይ በማጠናከር መልካምና ትክክል የሆነውን ሁሉ ለማጥፋት እንዴት እንደተቀሳቀሰ ተመልክታችኋል፡፡ ከተለያየ ቦታና ባህል የመጡ ሰዎች አንድ ላይ በመሆን መልካምን እንዴት እንደተቃወሙ አይታችኋል፡፡ ይህንን ስታዩ የተለያየ አመለካከትና ልምምድ ካላቸው ጋር አንድ በመሆን መልካምና ትክክል ለሆነው ለመቆምና መልካሙን ገድል ለመጋደል፣  እንዲሁም የተለየ አመለካከት ያላቸውን ባለማቋረጥ ለመወደድ ወስናችሁ ከእነርሱ ጋር እጅ ለእጅ ለመያያዝ በልባችሁ አላሰባችሁም? ነገር ግን ደግሞ እኔን ስለምትወዱ ይህንን ለእኔ ስትሉ አታደርጉትምን?

"የሚወዱና ይቅር የሚሉ ከእግዚአብሔር እንደሆኑ ይህንን እነግራችኋለሁ፡፡ መራራነትንና ክስን በልባችሁ የሚይዙ የሚኖሩት ለእኔ ሳይሆን ለራሳቸው ነው፡፡ ስለዚህ የምጠይቃችሁ ከፍ ባለው በእኔ መስታወት በልባችሁ ውስጥ ክፉ መንገድ እንዳለ እንድትፈትሹ ነው፡፡ የአምልኮ መንገዳቸው የተለየ በመሆኑ ፍርድን በማስተላለፍ ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖችን ወደ ጎን ገፍታችኋል? እንዲህ ካደረጋችሁ  ንስሐ እንድትገቡና ከሁሉ ጥሪያችሁ በላይ በእኔ ፍቅር እንድትኖሩ እንድረዳችሁ እኔን እንድትጠይቁ እለምናችኋለሁ፡፡

"በመካከላችሁ ያለው ልዩነት ንፁህና መፅሐፍ ቅዱሳዊ እስከሆነ ድረስ አክብሩት፡፡ ገና በመጀመሪያው እናንተን ትክክል፣ ወንድማችሁን ግን ተቃራኒ እንደሆነ ለማድረግ እጃችሁን በመጫን አትክሰሱ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ስርዓት ያለቸውን በደንብ ሳይገባቸው የሚያወግዙ የቀደሙ ብዙ አባባሎች እንከን ያለባቸው ቃላቶችን ሻል ባለ መልኩ በመጠቀም መርዝ እንዳለው ቀስት የሌላውን ክርስትና ዋጋ የሌለው ለማድረግ የተደረገ ነው፡፡

"የተለያዩ የቤተ እምነት ፓስተሮች ሌሎች የተመሰረቱበትን የመፅሐፍ ቅዱስ የእምነት ክፍል ሳይረዱ ብዙ ስህተቶችን አስተላልፈዋል፡፡ በደንብ ሳይገባቸው ቀድሞ የነበረውን ትችት በማቅረብ ወዲያው ወደትችት ለመግባት እጅግ ቀላሉ መንገድ ሆኖላቸዋል፡፡ እኔ ግን የምፈልገው የባህልና የልምምድ ልዩነቶቻችሁን እንድታከብሯቸውና ሌሎች ክርስቲያኖች ለእኔ ያላቸውን ትልቅ ፍቅር እንድትገነዝቡ ነው፡፡  ለምሳሌ ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች ካልተለመደ ባህል የመጡ ቢሆኑም ለእኔ ሲሉ አንገታቸውን የሚቀሉ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ከሞት ጋር የተጋፈጡና እኔን እንዲክዱ የተጠየቁ ነገር ግን ይህንን ለማድረግ እንቢ ስላሉ የተፈረደባቸው ባል፣ ሚስትና ልጆች ናቸው፡፡

"የተለመደው አይነት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ባለመሆናቸው ብቻ እኔን አይወዱኝም ማለት አይደለም፡፡ እኔን እንደሚወዱኝ ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው በመስጠት አረጋግጠዋል፡፡ ከእነዚህ ነፍሶች ብዙ ልትማሩ ትችላላችሁ፡፡ አንድነታችሁ መሆን ያለበት የጋራ በሆነ መሰረተ ሐሳብ ላይ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ለእናንተ እጅግ መደበኛ መስሎ የታያችሁን ባህላቸውን ማክበር አለባችሁ፡፡ በአምልኳቸው ላይ  መላዕክቶቼ እንዲነበኗቸው በማድረግ አምልኳቸውን እንዴት እንደማከብር ብታዩ እጅግ ትደነግጡ ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ ባልተለመደ ሁኔታ ተራ ሰዎች ሲሆኑ ለእኔ ግን ልብ ያላቸው ናቸው፡፡ እምነታቸውን ከሚክዱ ቢሞቱ ይመርጣሉ፡፡

"የተወደዳችሁ ህዝቦቼ ስለዚህ የምጠይቃችሁ ነገር ልዩነታችሁን ትታችሁ ከእናንተ ልዩ ባህል ያላቸውን በትልቅ አክብሮት በማየት የጎረቤቶቻችሁን እጆች ይዛችሁ እኔን በመንፈስና በእውነት አምልኩኝ፡፡ ስለዚህም ከአሁን ወዲያ በስርአት የሚተዳደሩትን ቤተ ክርስቲያናት የሞተች ናት የሚለውን መስማት አልፈልግም፡፡ አዎን የሞቱ ቤተ ክርስቲያናት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እናንተ በማይገባችሁ መንገድ ከእነርሱ ሙሉ ህይወት ያላቸው ደግሞ አሉ፡፡ በማይገባችሁ ነገር ፍርድን የምትሰጡ እናንተ ማን ናችሁ?

"አሁን ይህንን እየገርኳችሁ ያለሁት አለም ሁሉ ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ራሱን እያዘጋጀ ስለሆነ ነው፡፡ እናም ለእናንተ የምመኘው እኔ በብፅዕና እንዲኖሩ በጠራኋቸው መሰረት እየኖሩ ያሉትን ነገር ግን ከከራዝማቲክ ምዕራባውያን ልዩ የሆኑትንና እናንተን የማይመስሉትን ክርስቲያኖች እንድታከብሯቸው ነው፡፡ በዚህ አለም ላይ የጎርፉን በር ልከፍተው ነው፡፡ እናም በእኔ በኩል እንድትሆኑና እናንተን ከማይመስሉ ሌሎች ክርስቲያኖች ጋር እጅ ለእጅ እንድትያያዙ እፈልጋለሁ፡፡

"ይህ አሁን ሊመጣ ያለው ፀጋ ምክንያታዊ ያልሆነ ፍቅር፣ ትህትናና ለሌሎች ክብር መስጠትን የሚፈልግ ፀጋ ነው፡፡ ይህም ገና መለወጥ ያስፈልጋቸዋል ከሚል ድፍረት ይልቅ ትልቅ ጥቅም እንዳላቸው ማየትን ይጠይቃል፡፡ ጊዜ እየጨመረ በሄደ ቁጥር እየሆነ ያለውን የብዙ መሪዎች ዕብሪት ማየት ብትችሉ በመሸማቀቅ ይቅርታ ትጠይቁ ነበር፡፡ አሁን ኑና ከፍ ወዳለ አዲስ ባህርይ እንውጣ፡፡ ይህም በሰዎች ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ለማክበር የሚያስችልና ከመንግስተ ሰማይ የሚመጣውን ማር ለመቀበል የሚያዘጋጃችሁ ነው፡፡ ይህም ሰዎች ሁሉ ወደእኔ እንዲሮጡ የሚያደርግ ነው፡፡"

**የወደቁ መላዕክቶች ወደ ምድር መምጣትና መደረግ ያለበት ጥንቃቄ - ፌብርዋሪ 9 ቀን 2021 ዓ.ም**

**The Name of Jesus Routes Demons, Feb 9, 2021**

*ጌታ ኢየሱስ እባክህ ፍርሃታችንን አሸንፈን የሚያስፈልገውን መረጃ ለልጆቻችን ትተን እንድንሄድ አበርታን፡፡ አሜን፡፡*
ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ ጌታ በተደጋጋሚ ስለ ንጥቀት እንድናስብ እያደረገን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጥያቄዎችን የሚያመጣ ነው፡፡ አሁን ግን እየተማርኩ ያለሁት ይህንን ሐሳብ በመተው በእርሱ ላይ ማረፍን ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው ቀላል አይደለም፡፡ ነገር ግን እየተካሄደ ያለው የጌታ ጥበቃ ነው፡፡ እናም አሁን እርሱ እየጠየቀን ያለው በእርሱ ላይ እንድናርፍ ነው፡፡ ነገር ግን የንጥቀቱን ሂደት እያሰብኩ እንዲሁም ንጥቀቱ በቅርቡ የሚያስከትለውን በማሰብ ገና ብዙ መሰራት  ያለበት ነገር እንዳለ በመገንዘብ፣ ብዙ መስራት እፈልጋለሁ፡፡ ጌታ ተጨማሪ ጊዜ ቢሰጠን ለሚቀሩት የሚያስፈልግ ብዙ ነገሮችን ትቼ ለመሄድ ራሴን ለሥራው አሳልፌ ለመስጠት ዝግጁ

ነኝ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ጌታ ወደኋላ ለሚቀሩት ነፍሶች፣ እንዲሁም ያልዳኑ ነፍሶች በአጥፊው እሳት ወይም በአስቀያሚው ጦርነቱ እንዳይያዙ እንዲፀልሉ ለህዝቄኤል ነግሮታል፡፡

ከሁሉ የሚበልጠው ግን በአሁኑ ጊዜ በአገራችን እየተካሄደ ያለው ነገር ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ስር እንደሆነ እየነገረንና ሰላሙን እየሰጠን ነው፡፡ እርሱ ጌታ ነው፣ እርሱ የአሜሪካም ጌታ ነው ደግሞም የአለም ሁሉ ጌታ ነው፡፡ ብዙ መልካምን ለውጥ ካመጣው አስተዳደር ጋር እርሱ አብሮ ነው፡፡

(ክሌር)፡- በቅርቡ ከሌላ ፕላኔቶችና ከምድር ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጡራን ወደ ምድራችን መጥተው በማረፍ ጥፋት ያስከትላሉ የሚል ወሬ ሰምቼ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥም ቆም ብዬ እንዳስብና ትንሽ እንድፈራ አድርጎኛል፡፡ በዚህም ኢየሱስ ራሴን ወደ ልቡ ጠጋ አድርጎ አጥብቆ ያዘኝ፡፡ እኔም በእርሱ ላይ ጥብቅ አልኩ፡፡ በቅርቡ ፍፁም ክፉ የሆኑ ፍጥረታት እነዚህም የወደቁ መላእክቶች (demone alien) መጥተው ምድራችን በመውረር ሽብርን እንደሚያመጡ እንዳስታውስ ተደርጌ ነበር፡፡ እነዚህ ደግሞ ሰውን የሚበሉ ፍጥረታት ናቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ በእርግጠኝነት ሰውን እንደሚበሉ አውቃለሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." ይህንን ርዕስ ከአንቺ ጋር ለመነጋገር በፍፁም አልፈልግም ነበር፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ይህ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ ድርጊት በከፍተኛ ሁኔታ በሚፈፀምበት ወቅት በአለም ላይ መደነቅንና ፍርሃትን በማምጣት አለምን ሽባ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም የአንዳንዶችን ልብ ቀጥ የሚያደርግ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ኢየሱስ ይህ ከገሃነም በቀር ማሰብ ከምችለው ከማንኛውም ነገር በላይ አስፈሪ ነው፡፡
ኢየሱስም . . ."አዎ ይህ በምድር ላይ ትንሹ ገሃነም ነው፡፡

"ብዙ የምነግርሽ ነገር አለ፡፡ ነገር ግን ጊዜ ልትሰጪኝ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ልትሰጪኝ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጅማሬው ነው፡፡ ክሌር ከአንቺ ጋር ብዙ ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ነው ስለ እነዚህ ነገሮች እንድነግርሽና በዚህ ውስጥ የሚያልፉትን ልብ እንድታዘጋጂ በማሰብ ከአለም ጉዳዮች እንድትለዪ የምፈልገው፡፡ ከሁሉም በበለጠ ግን ታምራዊ በሆነ መንገድ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ እነዚህ ጊዜያቶች ለታምራቶችና ጊዜው እንዲያጥር ለማድረግ ብዙ ጩኸትን ይጠይቃል፡፡ ይህም ሰዎች ከሞት እንዲተርፉ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህም ታምራቶች እጅግ የሚታዩ ከመሆናቸው የተነሳና እንዲሁም ይህ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ህልም ስለሆነ በመንግስተ ሰማይ ያሉ እንኳን በዚህ ውስጥ ባለመሳተፋቸው ቅር ይላቸዋል፡፡

"አዎ የሚያስፈራ ጊዜ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ዋናው ነጥብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማሸነፍ መቻሉ ነው፡፡ ማንም ሰው ያለ እርዳታ አይሆንም፡፡ ነገር ግን እኔ ማን እንደሆንኩ አይኖቻቸው ተከፍቶ ማየትና እኔ አዳኛቸውና ጠባቂያቸው እንደሆንኩ መቀበል አለባቸው፡፡ ይህም በአለም ላይ ሊሆን ያለው ነገር እንዲሆን ያደረገው አንዱ ዓላማ ነው፡፡

"የተወደድሽ ክሌር እነዚህ ነገሮች እጅግ ጨለማና አስቀያሚ ናቸው፡፡ ከሙሽራዬ ጋር ማሳለፍ የምፈልገው ጊዜ በዚህ መልኩ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአይምሮሽ ውስጥ እጅግ የከበደ እንደሆነ ስለማውቅ ነው ይህንን እያወራሁ ያለሁት፡፡ በፊት እንደነገርኩሽ ኒብሩ የምትባለው ፕላኔት ነች እነዚህን ሁሉ ይዛ ያለችው፡፡ ይህቺ ፕላኔት በኢጋንንት የተወረረች

ፕላኔት ናት፡፡ እነርሱ በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ መገኘት የሚችሉ ስለሆነ ጊዜና ቦታ ለእነዚህ ፍጥረታት ምንም አይደለም፡፡ ይህ ማለት ከአንዱ ወርድና ስፋት ወደ ሌላኛው መሄድ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እናንተ ወደ ጨረቃ ለመሄድ እንደምታስቡት ሳይሆን እዛ ለመሄድ ስታስቡ በዛው ጊዜ እዛው መገኘት ማለት ነው፡፡

"አዎን ከአንዱ ወርድና ስፋት ወደ ሌላው ወርድና ስፋት በሮች ተከፍተዋል፡፡ የሰው እብሪት ይህንን አድርጓል፡፡ እኔ ለራሱ ደህንነት እንዲሆን በማለት የዘጋሁትን በሮች በዕብሪቱ ምክንያት ከፍቷል፡፡ እናም በዚህ ውጤት ይኖራል ደግሞም ይሞታል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን ደግሞ ተፈቅዷል፡፡

"አማኝ ስሜን ሲጠቀም ስሜ እጅግ ኃይል ያለውን የመሳሪያ ሥፍራ ይወስዳል፡፡ ነገር ግን እጅግ የሚያሳዝነኝ ነገር ሰዎች ሃይማኖት በጦርነት ላይ ምንም ሥፍራ እንደሌለው እንዲያምኑ መደረጋቸው ነው፡፡ በዚህም እጅግ ተሳስተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለጉዳታቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ የእኔ መላእክቶች ጥይትን እንዲሁም ሚሳይልን እንኳን ለማቆም ኃይል እንዳላቸው ምንም መረጃው የላቸውም፡፡ አለም እንደዚህ እንዲያስቡና በደንብ ቢጠቀሙበት በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ የሚሰራውን መንፈሳዊ ጦር  እንዳይጠቀሙበት ተደርገዋል፡፡ እነዚህም ፍጥረቶች በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ የሚቀሳቀሱ ናቸው፡፡

"በሌላ አነጋገር ጠላቶቻችሁን በእኔ ስም ለመዋጋት ከእኔ ጋር በእውነት ላይ የተመሰረት ግንኙነት ያስፈልጋችኋል፡፡ ይህም በሐዋርያት ምዕራፍ 19 ከቁጥር 13 ጀምሮ በምሳሌ እንደቀረበው ነው፡፡

> <u>*"ኢጋንንትንም እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶች። ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ። የካህናትም አለቃ ለሆነ አስቄዋ ለሚሉት ለአንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት። ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፦ ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቆስለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም። ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፥ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፥ የጌታም የኢየሱስ ስም ተከበረ፡፡"*</u>

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ … "ይህ ወቅት ከየትኛውም ጊዜ መወዳደር የማይችል ተስፋ የሚያስቆርጥ ጊዜ ነው፡፡ ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ ሰዎች እነዚህን ጭራቆች ለመግደል መሳሪያ ይዘው አልሰራ ሲላቸው የሚደርስባቸው ተስፋ መቁረጥ ነው፡፡

"ተወዳጆች እናንተ ከሄዳችሁ በኋላ ጊዜው ሲደርስ ልጆቻችሁ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት የምትተዉላቸው አንዳንድ ነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡ እኔን በመንፈስና በእውነት የያዙ በወደቁ መላዕክቶች ላይ ይህ ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡ በፊት እንደነገርኳችሁ ከወደቁ መልአክቶች (*alien*) ውስጥ መልካም የሚባል በፍፁም የለም፡፡ ሁሉም በማታለል ሰዎች እንዲያመኗቸው ራሳቸውን የደበቁ የተለያየ ድርሻ ያላቸው ኢጋንንቶች ናቸው፡፡ ልታምኗቸው አትችሉም፡፡ ሲናገሩ እጅግ ለስላሳና የረጋ የሚመስሉት እንኳን በውስጣቸው ንዴት የተሞሉና ሲመቻቸው ወዲያው የሚባሉ ጭራቆች ናቸው፡፡

ወዳጅ መስለው የሚቆዩት ሌሎቹን በመረባቸው ውስጥ ለማስገባት እንዲመቻቸው ነው፡፡ እናም እናንተ ስትሄዱ የሌለ ታሪክን በመፍጠር ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ከዚህ ያለፈ ጥያቄ የሚያቀርብ ካለ ምግባቸው ይሆናሉ፡፡

"በምንም አይነት መልኩ ቢሆን እነዚህን የወደቁ መላዕክቶች (*demon aliens)* ወደቤታችሁ እንዲገቡ እንዳትጋብዟቸው፡፡ ስሜን ጠርታችሁ አባሯቸው እንጂ በምንም አይነት መንገድ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት እንዳይኖራችሁ፡፡ በዚህ አለም የአሁኑ ትውልድ እግዚአብሔር የለም የሚል አስተሳሰብ እንዲኖር ለማድረግ መሰረቱ ተገንብቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ እኔ ማን መሆኔን እስኪረዱና አዳኛቸው አድርገው እስኪቀበሉኝ ድረስ እኔን ማወቅ አይችሉም ደግሞም ኃይል ያለውን ስሜን አይጠቀሙም፡፡ ስለዚህ ይህንን አሁን የምነግራችሁ ሌሎችን እንድታዘጋጁ ነው፡፡

ጌታ ሌላ ልትለን የምትፈልገው ነገር አለ?

"ለማለት የምፈልገው አንድ ነገር እያንዳንዳችሁን እጅግ እንደምወዳችሁ ነው፡፡ ለአገልግሎት ከንጥቀት ወደኋላ ለመቅረት የፈቀዳችሁትን ደግሞ አመሰግናችኋለሁ፡፡ በጣም በሚያስደስት ሁኔታ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ በዛን ጊዜ ነገሮች የሚካሄዱት አሁን እንደሚካሄዱት ሁኔታ ሳይሆን ከተፈጥሮ ሁኔታ ባለፈ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ያለ እርዳታ አልተዋችሁም፡፡ ነገር ግን ቀናችሁ ሁሉ በፀሎትና በማድመጥ መሞላት አለበት፡፡ ይህንን ችሎታ ነው እንዲያዳብሩ የምረዳቸው፡፡ ይህም በውስጥ ያለውን የውይይት ምልልስ በመዝጋት ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ያለውን የእኔን መገኘት የሚያስከትል ነው፡፡

"ብዙ ብልህ ሰዎች ብዙ የሚገርም ነገርን የሚሰሩ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ብቻ አስታውሱ ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና። እናንተ ፀልያችሁ እኔ ምንም ስሜት የማይሰጥ አንድ ነገር እንድታደርጉ ስመራችሁ ምንም ይሁን አድርጉት፡፡ የእናንተ መታዘዝ ነው ከጠላቶቻችሁ እጅ ፈልቅቆ ነፃ የሚያወጣችሁ፡፡

(ክሌር)፡- እናም ያንን ሲል "ምንም ይሁን ምንም ብቻ አድርጉት፡፡" በዚህ ጊዜ "ዘ ቾዝን" የሚለው ፊልም ትዝ አለኝ፡፡ ክፍሉም የቃና ገሊላ ሰርግ የሚያሳየው ነበር፡፡ ሰዎቹ ወይን አልቆባቸው ነበር፡፡ እነርሱም የማንፃት ስርአትን ለመፈፀም ውሃ የያዙትን የድንጋይ ጋኖችን ባሉበት ክፍል ቆመው ነበር፡፡ እናም ኢየሱስ ጋኖቹን ውሃ እንዲሞሏቸው ነገራቸው፡፡ ይህ ምንም ስሜት የሚሰጥ ነገር አልነበረም፡፡ ሰውዬው ወይን አልቆብኛል አለ እንጂ ውሃ አልፈልገም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ "ቶማስ ሁሉ ነገር ስሜት ላይሰጥ ይችላል ነገር ግን ምን እንደሚሆን ዝም ብለህ ተመልከት" አለው፡፡ ከዚያ በኋላ ያለው ሁሉ ታሪክ ነው፡፡ ጌታ በጋን ውስጥ ያለውን ውሃ ሁሉ ወደ ወይን ቀየረው፡፡ ይህም የሆነው ሰውዬው አድርግ እንደተባለው ዝም ብሎ በማድረጉ ነው፡፡ የተባረከችው የጌታ እናት "እርሱ የሚላችሁን አድርጉ" ብላቸው ነበር፡፡ እነርሱም እንደተባሉት ሲያደርጉ ከሚያስፈልጋቸው በላይ የወይን ጠጅ አገኙ፡፡ ከዚህም በላይ የወይን ጠጁ ጣዕም ማንም ቀምሶ የማያውቀው አይነት እጅግ ጣፋጭ ነበር፡፡ ይህ ሊሆን ደግሞ ግድ ነው፡፡

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች በታኦስ በእኔ የሆነውን አንድ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ በቅርቡ በበጋ ወራት ዩፎ(UFO's) በታኦስ ሰማይ ላይ አየን፡፡ አንደኛው በአካባቢያችን ባለው በአልማርት ሰማይ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር፡፡ የተንጠለጠለው

ልክ ኮከብ የሚመስል ነው፡፡ ሰው ይህንን ተገንዝቦ እንደሆነ አላውቅም፡፡ በዛው ምሽት በሙቅ ውኃ ውስጥ ተዘፍዝፌ ሰማዩን እያየሁ እያለ ተመሳሳይ የሆነ ብርሃን ተንቀሳቅሶ እኔ እያየሁ ወዳለሁበት ተራሮች ምስራቅ ክፍል ሲቆም አየሁ፡፡ ምን ማለት እንዳለብኝ በፊት አውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሳላውቀው ከአንደበቴ አፈትልኮ የወጣው ቃል "ጌታ ከክፉ አድነን" የሚል ነበር፡፡ በዛችው ደቂቃ ውስጥ ቆሞ የነበረው በመሄድ ጭራሽ ጠፋ፡፡ ጌታ የነገረኝ ነገር እነዚህን ነገሮች ጭራሽ እንዳላያቸው ነው፡፡ ጭቅላታችሁን የሚነካ መንገድ አላቸው፡፡ በዚህ ከተማ ያለች አንዲት ሴት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኳስ ሜዳ ላይ ሲያርፍ አይታ በእነርሱ ተነደፈች፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ በፀጉሯ ላይ መላጣ ስፍራ አላት፡፡ እናም እነርሱን ስታይ አንድ ነገር እንደሆነች ትናገራለች፡፡ እንደዚሁም ሌሎችን አውቃለሁ በእነርሱ ተጠልፈው የነበሩ ሰዎች በራሳቸው ላይ መላጣ ስፍራ እንዳላቸው፡፡

ኸርት ድዌለርስ እባካችሁ ልባችሁን ለኢየሱስ ብቻ ጠብቁ፡፡ እንዲሁም እነዚህ ፍጥረታት እኛን የፈጠሩ አምላክ ናቸው የሚለውን  ውሸት አትቀበሉ፡፡ በፍፁም አይደሉም፡፡ እነርሱ የወደቁ መላዕክቶች፣ ከመንግስተ ሰማይ የተባረሩ እና ከሰው አካል ቁራጭ ለራሳቸው አካልና ዘረመል(DNA) ያዘጋጁ ናቸው፡፡ በእነርሱ የተጠለፉ ሰዎች አንድ  መልካም ነገር እንኳን አድርገው እንደማያውቁ ይነግሯችኋል፡፡ እነርሱ ሽብር ፈጣሪዎች፣ አካልን የሚያጎድሉና የሚደፍሩ እንዲሁም የሚጠልፏቸውን የሚገድሉ ናቸው፡፡ ስለዚህም ስልጣናችንን ተጠቅመን ከአካባቢያችንን እንዲሸሹ ማባረር እንጂ ከእነርሱ ጋር ተካፋይ ለመሆን ፍፁም ምክንያት የለንም፡፡

ደግሞም የመጡት ምድርን ለመርዳት ነው የሚለውን የውሸት የፈጠራ ታሪክ በመስማት ተታላችሁ አትሳቡ፡፡ ይህ እውነቱን  ለመደበቅ የተዘጋጀ መሸፈኛ ነው፡፡ ወደ ምድር የመጡበት እውነተኛው ምክንያት እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ለማጥፋት ነው፡፡ በተለይም በእግዚአብሔር ሐምሳል የተፈጠረውን ሰው ፈቃዱን በማግኘትና ከእነርሱ ጋር እንዲተባበር በማድረግ ምድርን ተቆጣጥረው ለማጥፋት ነው፡፡ በመጨረሻም ይህ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን ደግሞ ጣልቃ ይገባና እስከ መጨረሻው በእሳት ባህር ውስጥ ይጥላቸዋል፡፡

## የእግዚአብሔር ቁጣ ዘግይቶ የምህረት ጊዜ ተጨምሯል - ፌብርዋሪ 20 ቀን 2021 ዓ.ም

## A Love Letter to You - Feb 20, 2021

*(ክሌር)፡- የጌታ ኢየሱስ ሰላምና ጥበቃ ይብዛላችሁ ያበርታችሁ፡፡ አሜን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በአገራችን እየተካሄደ ስላለው ነገር የሚቀርበው መረጃ እየተካሄደ ካለው ጋር ሲወዳደር እጅግ አናሳ ነው፡፡ ይህ ቢሆንም ግን በፀሎት እየቀጠልን በሄድን ቁጥር የጥርመሳ አፋፍ ላይ እየደረስን እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሐሳብ በአይምሮዬ መጣ፡፡ ይህም  ጌታ ቀደም ብሎ እንደነገረን ማያሚ ሲመታ ወይም በኢየሩሳሌም ያለው የሙስሊሞች መስገጃ ጥፋት ሲደርስበት የሦስተኛው የአለም ጦርነት ይነሳል  ብለው አንዳንዶች እየጠበቁ ይሆን? የሚል  ነው፡፡ እንደሚመስለኝ ይህንን ሐሳብ ጌታ በአይምሮዬ ሳያስቀምጠው አልቀረም፡፡ ምክንያቱም መልሱን ወዲያው ነው የሰጠኝ፡፡*

*ኢየሱስም  . ." አዎን ይህንን ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህም እኔን በመወከል ቁጣው ተሰርዞ የምህረት ጊዜ እንደተጨመረ እንድትነግሪያቸው እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህም ሑነቶች አሁን የሚገለጡት በተለየ መንገድ ነው፡፡ ማያሚ አሁንም በኢላማ ውስጥ ብትሆንም ቀዳሚ ኢላማ የሆነችው ከተማ ግን የኒዮርክ ከተማ ናት፡፡ ቢሆንም በበቂ ፀሎትና*

*መስዋዕት እቅዱን ለሌላ ጊዜ በማሻገር ሥራ ላይ እንዳይውል በማድረግ ለማዘግየት የሚቻልበት ዕድል አለ፡፡ ክሌር እንዲገባሽ የሚያስፈልገው ግን ይህች ከተማ ጠብቃ ያቆየችው የቆሻሻ ሸታ ወደ አባቴ አፍንጫ ከመድረሱም በላይ ከተማዋ የሚገባትን ጥፋት ሳታስተናግድ እስካሁን መዘግየቱ ነው፡፡ የዚህም ቆሻሻ ሽታ መነሻው ባመዛኙ ቆጥራችሁ የማትጨርሱት ምንም የማያውቁ ህፃናት ጩኸት ነው፡፡  ይህም የሆነው የሰይጣን እምነት በመስፋፋቱና ምንም የማያውቁ ህፃናት ህይወት በመጥፋቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውርጃን ሳይጨምር ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ የደም ጎርፍ ከዛች ከተማ እየወጣ ነው፡፡ ይህም ደግሞ ለጥፋቷ የሚዳርጋት ምክንያት ነው፡፡*

*"ለእኔ ታማን የሆኑትን ከዚያ ሥፍራ ለማስወጣት ብዙ ጊዜ ሞክሬያለሁ፡፡ ነገር ግን ምንም ጥቅም የለውም፡፡ የዚህችን ከተማ ጥፋት ካዘገየው ዋነኛው ምክንያትም ክፉን የሚቃወም መልካም መኖሩ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን የክፉው ሚዛን አይሎ ከተማዋ ልትጠፋ የሚቀራት እጅግ ጥቂት ጊዜ ነው፡፡ ምንም በማያውቁት ህፃናት ላይ ከጥልቁ ጨለማ በጭካኔ የሚደረገውን ወንጀል ስላልተገለጠላችሁ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ልታውቁ አትችሉም፡፡ ነገር ግን ከገሃነም ሁለተኛው እንደሆነ ይህንን ያህል ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡ ከዚህ ከተማ ጥልቀት የሚወጣው ጩኸት በመንግስተ ሰማያት ያለውን ሁሉ በዕንባ የሚያራጭ ነው፡፡*

*"እንዲሁም በአለም ላይ እየተካሄደ ባለው ቀጥታና ተዘዋዋሪ በሆነ የክፉ እንቅስቃሴ ምክንያት ፍትህን የሚፈልጉት ጩኸት ጭምር ነው ወደ አባቴ የደረሰው፡፡ እርግጥ ነው ፀሎት በተወሰነ መልኩ ይሰራል፡፡ ነገር ግን እኛ የምናየውን ማየት ብትችሉ ምህረት እንዴት እስከ መጨረሻው እንደተዘረጋ የበለጠ ይገባችሁ ነበር፡፡ ኢያችሁ ኢያንዳንዱ ቀን ባለፈ ቁጥር ክፉ የበለጠ እየተገለጠ ይወጣል፡፡ ይህም የሚሆነው የክፋት መጠኑ በከፍተኛ ደረጃ እየተገለጠ ሲሄድ ነው፡፡ በሌሎችም ከተሞች ለምሳሌ እንደ ቻርሎት፣ ሰሜን ካሪአላና ያሉ ከተሞች የክፉ ምሽግ ለመሆን እየተነሳሱ ይገኛሉ፡፡ ገንዘብ ባለበት ሁሉ ክፉ በተለያየ አይነት እርከን ይገኛል፡፡"*

*(ክሌር)፡- በዚህ ጊዜ ዕንቅልፍ እንዳይዘኝ እየታገልኩ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ጌታ ሲያናግረኝ ብዙ ጊዜ የሚያስቸግረኝ ነገር ነው፡፡ ይህንንም ለማሸነፍ ብዙ ጊዜ እታገላለሁ፡፡ ከበስተጀርባው የሚሰራውንም ኢጋንንትን እገስፃለሁ፡፡ አንዳንዴም እጅግ ደካማ እሆንና ትንሽ ዕረፍት እወስዳለሁ፡፡ እናም ከዕንቅልፌ ስነሳ ታድሼ እነሳለሁ፡፡*

*ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "የኔ ፍቅር እንደደከመሽ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ከአንቺ ጋር  ለመነጋገርና ለመወዛወዝ እፈልጋለሁ፡፡ እንዲህ ልበል ከአንቺ ጋር ለመሆን እጓጓለሁ፡፡ እናም በጥልቅ ከእኔ ጋር ካልሆንሽ በቀር አንቺም አስቸጋሪ ነሽ፡፡ ልክ አይደለም?"*

*(ክሌር)፡- አዎ ጌታ ትክክል ነው፡፡ ጌታ ከእኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሁላችሁም ጋር ሊሆን እጅግ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም በፀሎት ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይፈልጋል፡፡*

*ጌታም  . . . " በምታይው ራዕይና በምሰጥሽ ቃል በራስሽ የበለጠ እንድትተማመኚ እፈልጋለሁ፡፡ የምሰጥሽ ራዕዮች ማሰብ ከምትችዪው በላይ የበለጠ ትክክለኛ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከእኔ እንደሆነ ሳይታወቅ  ብዙ ጊዜ ያልፋል፡፡ ለምሳሌ የባህር ኃይሉ ሲሰግድ ያየሽው ትርጉም ያለው ራዕይ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እኔ እንደተናገርኩሽ ወይም እንዳሳየሁሽ በራስሽ ካልተማመንሽ በስተቀር ትጠይቃለሽ ደግሞም ትደናቀፊያለሽ፡፡ ይህ ደግሞ እኔ የሰጠሁሽ ራዕይ*

*ፍሰቱን በመዝጋት እንዳይገለጥ ያደርጋል፡፡ ወደ ሙሉ የራስ መተማመን መመለሻ መንገድ ደግሞ አለሽ፡፡* የሳብሽው ካርድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ እናም ይህንን ብታመዛዝኚው ለአንቺ መልካም ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ እየተናገረው ያለው ስለ ሬማ ካርዶች ነው፡፡ የሬማ ካርዶች የተቆራረጡ ትንንሽ ካርዶች ሆነው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተፃፈባቸው ሲሆኑ እንደሚመስለኝ አንድ ሺህ ያህል ይሆናሉ፡፡ እናም ከዚህ የሬማ ሳጥን ውስጥ ዝም ብዬ አንድ ካርድ ስስብ እንዲህ የሚል ወጣልኝ፡፡" የእግዚአብሔርን መንገድ በሙሉ ልባችን ተቃወምነው፡፡ ስለዚህም አሁን ያለንበት መንገዳችን ተመርዞ በፊታችንን ያለውን መንገድ መራራ በማድረግ ሊቆጣጠረው እየሞከረ ነው፡፡ ስለዚህም እኔ አሁን ምን እየሰራሁ እንዳለሁ በማመን ለመቀበል ተማሪ፡፡"

(ክሌር)፡- በጣም የሚገርመው ነው፡፡ ይህ ትክክለኛ ነገር ነው፡፡ ይህም በቅርብ ሊሆን ስላለው ንጥቀት ምክንያት መራራ እየሆንኩ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት እጅግ አስፈላጊ በሆነው ነገር ላይ ራሴን ልሰጥና ጌታ የሰጠኝን ራዕይ ለመጨረስ ደግሞ ነፃነት አለኝ የሚል ደረጃ ላይ ስለደረስኩ ነው፡፡ ይህ መነሳሳት ደግሞ ተግባሩ በትክክል እንዳይከናወን መንገድ እየዘጋ እንደሆነ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ነገር ግን ደግሞ ቀደም ብዬ ወደዚህ መረጋጋት ስላልደረስኩ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ሳያልቁ ምድርን ለቀን ስለ መሄድ አሁን እያወራን እንገኛለን፡፡ አዎ ይህ በመሆኑም ተስፋ በመቁረጥ ድብርት ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ አዎ ጌታ ሆይ ስለዚህ ነገር እየተቋቋምኩህ ነው፡፡ እናም ስለዚህ የተመጠነ ጊዜ የመራራነት መርዝ እየተሰማኝ ነው፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠን እየፀለይኩ ነው፡፡ ጌታ ልትረዳኝና ስለዚህ የበለጠ ልታስረዳኝ ትችላለህ?

*ጌታም . . ." ይህ መርዝ በቀረው ጊዜ እንኳን ሊሰራ የሚችለውን ጥቂት ነገር እንዳይሰራ ያደርጋል፡፡ ይህ ጥልቅና ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ለአሁኑ ጊዜ የሚለቀቀውን የመንግስተ ሰማያትን የመፍጠር ፍሰት እንኳን ይዘጋል፡፡ ይህ እንደሚሰማሽና ደስ እንደማይልሽ አውቃለሁ፡፡ እናም ይህ ደግሞ ህይወትሽን እየታገለ የወደፊት እንቅስቃሴሽን እየገታ እንደሆነ አውቀሻል፡፡"*

*(ክሌር)፡- ጌታ አንተ የምትለው ሁሉ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ውስጣዊና ጥልቅ ከሆነ መሳቀቅና መራራነት ራሴን እንዴት እንደማወጣ አላውቅም፡፡ እባክህ ጌታ ሆይ እርዳኝ፡፡*

*"አሁን ነገሮችን እየዘጋብሽ ወዳለው ነገር እየገባን ነው፡፡ ተስፋ በሚያስቆርጥ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደሆንሽ ተሰምቶሻል፡፡ ነገር ግን ይህ የተሰማሽ አንቺ ብቻ ሳትሆኚ ንጥቀቱ እየተቃረበ እንደሆነ የተረዱ ሁሉ ናቸው፡፡ ይህንን ቻናል ትተው የወጡ እንኳን ከመወሰዳቸው በፊት ለእኔ ለማድረግ የፈለጉትን ለመስራት እየታገሉ ነው፡፡ አለም አቀፍ የሆነ መሳቀቅ ነው የሚታየው፡፡ ምክንያቱም ከአመታት በፊት እንደነገርኩሽ በፕሬዚዳንት ትራምፕ ምክንያት በዚህ የሚጀምረው ማንፃት አለምን ሁሉ በመድረስ የተበላሹ መንግስታትን ሁሉ ስለሚዳስስ ነው፡፡ ይህ ትልቁ የመነቃቃት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም የፖለቲካው መነቃቃት በመቅደም መንፈሳዊው መነቃቃት እየተከተለ ይሄዳል፡፡*
"ውዴ ህይወትሽን ለእኔ በሰጠሽኝ ጊዜ ከምንም ጋር ሳታያይዢ ነው የሰጠሽኝ አይደለም?

አዎን ጌታ እውነት ነው፡፡

"ስለዚህ ከመወሰድሽ በፊት አብረን ምን መስራት እንዳለብን አንዳንድ የምትጠብቂው ነገር አለ አይደለም?

አዎን ጌታዬ፣ እጅግ በጣም እጠብቃለሁ፡፡ በህይወት የቆዩ መከናወን ያለባቸው ብዙ ብዙ ህልሞችና እቅዶች አሉ፡፡

ጌታም . . . "አንዳንዱ ከብዙው በጥቂቱ የተከናወነ አለ፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የተከናወነ ነው፡፡ ለምሳሌ የመንደሩ መመስረት፡፡ ይህም ሆኖ ግን አሁንም ለምን ይህንን እንደምፈቅድ ትጠይቂኛለሽ፡፡"

ጌታ ይህ እውነት ነው፡፡ እስካሁንም አልገባኝም፡፡

*"በየቀኑ እየጨመረ የመጣውን የመሬት መንቀጥቀጥና እሳተ ጎሞራ አስተውለሽዋል?"*

*አዎን ጌታ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ ነገሮችን ለአራት አመታት ማዘግየትና የጀመርነውን እንድንጨርስ ማድረግ እንደምትችል አውቃለሁ፡፡*

*ይህንን ለማድረግ ዘላለም በፊትሽ አለ ነገር ግን በዛ መንገድ አታስቢውም፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት ተሰጥቶሽ የነበረውን ዕድል ስላልተጠቀምሽበት ከዚህ የውድቀት ስሜት የመጣ ነው፡፡"*

*ጌታ ያልከው ሁሉ ትክክል ነው፡፡*

*ጌታም . . ." ነገር ግን አንድ ዋናና አስፈላጊ የረሳሽው ነገር አለ፡፡ ይኸውም የአባቴን የተመጠነ ጊዜና ውሳኔውን ማክበር ነው፡፡ ከሴር አንቺ አንድ ነፍስ ነሽ፡፡ ነገር ግን በምድር ላይ ሚሊየኖች እየተሰቃዩ ነው፡፡ ደግሞም መሰቃየታቸው ይቀጥላል፡፡ የእነዚህን ነፍሶች ስቃይ ማድመጥ አለብን፡፡ እናም እንደ እውነቱ ከሆነ ከፉ እንዲያበቃ ቀን ተቀጥሮለታል፡፡ እናም አሁን ያላችሁት በዛ የጊዜ ክልል ውስጥ ነው፡፡ ጊዜያችሁን በአግባቡ ያለመጠቀማችሁ የእኛ ስህተት አይደለም፡፡ ነገር ግን ያም ቢሆን ገና ከጅምሩ ያ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ ከሴር በሌላ አነጋገር እኛ ስለአንቺ ሸፍነነዋል፡፡ ተወዳጅ ሆይ ውድቀቶችሽን አይተናል፡፡ እናም አሁንም እንወድሻለን ደግሞም በአንቺ ደስ ብሎናል፡፡ በህይወትሽ የነበረውን ውጣ ውረዱ በምን ምክንያት እንደሆነ ብዙ ሳይገባሽ ለማሸነፍ እጅግ ብዙ ሞክረሻል፡፡ አንዳንዶች የተሰጣቸው ጀልባ ሙሉ ፀጋ፣ አንዳንዶች ጥቂት ጀልባ ፀጋ፣ አንዳንዶች ደግሞ ገና ጥቅም ላይ ያልዋለ አዲስ ጀልባ ፀጋ እንዲሁም አንዳንዶች በባልዲ ፀጋ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዋናው ቁም ነገሩ በተሰጣችሁ ፀጋ ምን እንደሰራችሁበት ነው፡፡*

*"እንዲሁም ከማንም፣ ከምንም፣ ከአለም ሁሉ አስበልጠሽ እኔን መውደድሽን እወደዋለሁ፡፡ ይህ ደግሞ የጀመርሽውን ሥራ ባትጨርሽም፣ ነፍሶችን ወደ እኔ ባታመጪም እንኳን ይህ ለእኔ መፅናናት ሆኖኛል፡፡ እንዲሁም የገጠመሽን ተቃውሞ አሸንፈሽ ለእኔ ፍቅር ታማኝ በመሆን ከእኔ ጋር በመጣበቅሽ በዚህ ደስተኛ ነኝ፡፡*
"ልክ እንደ አንቺ ብዙ ነፍሶች ደካሞች ናቸው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን እንዲያውቁ የምፈልገው ለእነርሱ ትንሽ የሚመስላቸው በእኔ ላይ የሚያፈሱት ፍቅርና አድናቆት ከፍተኛ ዋጋ እንደምሰጠውና እንደምቀበለው ነው፡፡ ብዙ አድራጎትሽ እስካሁንም የሚመራው አለም ነገሮችን እንደሚፈርጀው ነው፡፡ እኔ ግን በፊትሽ ያለውን መጋረጃ ስገልጥ የሚታየው፣ ይህም አብረን ወደፊት ያመጣነው ፍሬ፣ በአለም ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ያደረጉትን ባዶ ሊያደርገው የሚችል

ነው፡፡ ይህም የፈጠረው በእኔ ጥላና ከንድ ውስጥ መጠለያ ያገኙ የነፍሶችን ባህር ነው፡፡ አዎን ባህር !!! ያልገባሽ ነገር ብዙዎች በአንቺ ተነክተዋል ነገር ግን ለአንቺ ተሰውሮ አይታይሽም፡፡ እነዚህም ነፍሶች ራሳቸው የሚሰሩትን ሞኝ ነገር አንቺ ከእኔ ጋር ሆነሽ ስታሳልፊ ለማየት ይጓጓሉ፡፡

"እነርሱ ብዙ ጊዜ የሚያምኑት በእኔ እንደማይፈለጉና እንደተገፉ ነው፡፡ ነገር ግን ያ ከእውነት የራቀና የሰይጣን አገልጋዮች የሚነግሯቸው ነው፡፡ እነዚህ የሰይጣን አገልጋዮች የሚፈልጉት የክርስትና ህይወት ሰው ሊኖረው የማይቻል ነው በማለት ሰዎችን ከእኔ ማራቅ ነው፡፡ ስለዚህም እኔ ምንም የማይመስለኝን ጥቂት ነገር ትልቅ የመንግስቱ ጉዳይ በማስመሰል በዛ ይቀጠቅጢችኋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የልብሽን መጉበጥ አያለሁ፡፡ ደግሞም የጠፋውን ጊዜና ፀጋ በማሰብ በንስሐ በረኸርሙ ስትተነፍሺ እሰማለሁ፡፡ ይህ የሚሰማሽ እጅግ አስከፊ ቢሆንም በፀሎት ወደ እኔ ስትቀርቢ ደግሞ ደስ ይለኛል፡፡

"በቅርቡ ለአንድ ወንድም የኔን ፍቅር ስታስረጂ "እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሊያይህ ይደሰታል፡፡ እርሱ ሁልጊዜ አንተን ለማፍቀርና ለመቀበል ዝግጁ ነው፡፡ ይህም ውሻህ ምንም ብታደርገው አንተ ስትመጣ በሩ ላይ ወጥቶ ጭራውን እያወዛወዘ እንደሚቀበልህ አይነት ነው፡፡" ብለሽ የተናገርሽው ነጥብ ትክክል ነው፡፡ ደግሞም በኢንጊሊዘኛው ውሻ የሚለው ቃል እግዚአብሔር ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ (God & Dog) አፃፃፍና አነባበብ መኖሩ የአጋጣሚ አይደለም፡፡ በእውነት ነው የምላችሁ በአጋጣሚ አይደለም፡፡ ይህም የሆነበት ሁለቱም ከምክንያት ውጪ አፍቃሪ ስለሆኑ ነው፡፡ ከድመቶችሽ አንዱ ወደ ሽንት ቤት በመግባት የሽንት ቤቱን ወረቀት ቢቀዳድደው ምን ይሰማሻል? ትጠያቸዋለሽ?"

ጌታ በፍፁም፡፡ እርስ በርሳቸው የጥላቻ ድምፅ ሲያሰሙ ወይም ሲጣሉ ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ያድርጉ ምንም በመሳቅ ፍቅሬን እገልጥላቸዋለሁ፡፡ እርስ በርሳቸው ሲጣሉ ግን በባህርያቸው ተስፋ እቆርጣለሁ፡፡

ኢየሱስም . . ." እኔም የሚሰማኝ ተመሳሳይ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚያስቅ ነገር ትሰሪያለሽ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አባካኝ ልትሆኚ ትችያለሽ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር አጠፋሽ ብዬ ፊቴን አላዞርብሽም፡፡ በአንፃሩ ግን እራራልሻለሁ፡፡ ምክንያቱም በራስሽ እንዴት ተስፋ እንደምትቆርጪ ስለማውቅ ነው፡፡ ሌሎች አገልጋዮችን ስትሙቺ ግን የምትወጃቸው ድመቶችሽ ሲጣሉ እንደሚሰማሽ አዝናለሁ ደግሞም ተስፋ እቆርጣለሁ፡፡

"ኸርትድዌለርስ በደንብ እንዲገባችሁ የምፈልገው ነገር አንድ አጋንንት እናንተን በሐሳብ የማያሰቃይበት ወይም እናንተን ከእኔ ለመለየት በሚቀጥለው ምን ማድረግ እንዳለበት እቅድ የማያወጣበት አንድም ደቂቃ የለም፡፡ እናንተ ያላችሁት ሁልጊዜ በጦር ሜዳ ላይ ነው፡፡ ለዚህ ነው ነፍሶች ወደ መንግስተ ሰማይ ሲሄዱ እጅግ የበዛ ሰላምና ደስታ የሚሞሉት፡፡ ምክንያቱም በህይወታቸው አንድ ጊዜ እንኳን ራስን በመጥላት በተመረዘ፣ እሳትን በሚረጭ ቀስት ያልተወጉበት ጊዜ ስለሌለ ነው፡፡ ለዚህ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጊዜ የምናገረው፡፡ በድብርት ህይወት በትግል ለምን እንደኖራችሁ በዚህም ደስታ ወይም መነሳሳት ለምን እንዳጣችሁ በደንብ ልታውቁ አትችሉም፡፡

"እንደዚህ የሚሰማችሁ ከሆነ እኔ ለማድረግ የምፈልገው እናንተን ማቀፍና ፍቅሬን ማልበስ እንዲሁም እናንተ በእውነት የእኔ እንደሆናችሁ፣ ለእኔ ግድ እንደሚላችሁና እኔን የሚያስደስት ህይወት ለመኖር የምትፈልጉ በመሆናችሁ ማመስገን

ነው:: ለእኔ ለመኖር ስለፈለጋችሁ ነው ጥላቻ በተሞላበት ቀስት ሰውነታችሁንና አይምሮአችሁን እየተወጋችሁ ያላችሁት:: እነርሱ ከእኔ ጋር ከተቀራረባችሁ እንደማፈቅራችሁ፣ እንደምፈውሳችሁ፣ እንደማነሳሳችሁ፣ እንደምመልሳችሁ፣ እንደማበረታችሁ፣ እንደማነሳሳችሁና እንደገና በሁለት እግሮቻችሁ እንደማቆማችሁ ስለሚያውቁ ነው:: ስለዚህም እነርሱ የሚመርጡት የጥቃት መንገድ የማትረቡና በእኔ የተተዋችሁ እንደሆናችሁ አድርጎ ማቅረብ ነው::

"እስካሁን ምንም ስሩ ምንም እናንተ በፍፁም የማትረቡ አይደላችሁም:: ብዙ ስቃይ የሞላበት የመስቀል ሞት የሞትኩት ለእናንተ ነው:: ይህም ስለማፈቅራችሁና ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ እንድትኖሩ ስለምፈልግ ነው:: ለኃጢያታችሁ ዋጋ መክፈል እንደማትችሉ ስለማውቅ እኔ ከፈልኩ:: በዚህም ምክንያት ሰይጣን ስለሚጠላችሁ ወደ ገሃነም እንዴት እንደሚጎትታችሁና እንደሚጥላችሁ በጥንቃቄ ነው የሚያጠናው:: በዚህም ከመጥፎ ማንነቱ ጋር አብራችሁ እንድትኖሩ ለማድረግ ነው::

"እናንተ ከፈቀዳችሁልኝ በህይወታችሁ የሆነ ምንም ነገር፣ የሰራችሁት ምንም ነገር፣ ወይንም ለመስራት ያልቻላችሁት ነገር በክንዴ አቅፌያችሁ በደቂቃ ውስጥ መፈወስ የማልችልው ምንም ነገር የለም:: ቁስላችሁ እጅግ ጥልቅ እንደሆነ አውቃለሁ፣ እንዲሁም ራሳችሁን እንዴት በጥልቅ እንደምትጠሉ አውቃለሁ:: ስለዚህም እነዚያን ቁስሎቻችሁን በደሜ በማዳን እኔ ወዳዘጋጀሁላችሁ ደስታ፣ ምስጋናና ውለታ፣ እንዲሁም ምክንያት ወደሌለው ፍቅር እናንተን ከፍ ለማድረግ ነው:: ይህ ደግሞ እናንተ ሰራችሁም አልሰራችሁም ሊቀር የሚችል ነገር አይደለም:: ድመታችሁ አንድ ነገር በመስራቷ ወይም ባለመስራቷ ሳይሆን እንዲሁ ዝም ብላችሁ እንደምትወዷት ማለት ነው:: ድመቶቻችሁ ጥሩ ባይሆኑና ኩራተኖች ቢሆኑም ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅር ምንም ሊቀይረው አይችልም:: እዚህጋ ድመትን እንደ ምሳሌ የምጠቀመው ኩራተኞች፣ የራሳቸውን ብቻ የሚያከናውኑና ምላሽ የማይሰጡ በመሆናቸው ነው::

"ስለ እናንተ ምን እንደሚሰማኝ ለብዙ ቀናት መናገር እችላለሁ:: ነገር ግን ይህንን በየቀኑ ባደርግም ለእያንዳንዳችሁ ያለኝን ፍቅር ጥልቀቱን፣ ስፋቱና ርዝመቱን ገና መረዳት ትጀምሩ ይሆናል:: ለዚህ ነው ይህንን እየደጋገምኩ የምናገረው:: የኔ ውዶች ለእኔ በእውነት እጅግ ውዶች እንደሆናችሁ እናንተን በየጊዜው ማስታወስ ይገባኛል:: እናም ለእናንተ እጅግ ብዙ መልካም ነገሮችን በዚህ ምድርና በመንግስተ ሰማይ አቅጃለሁ:: በእርግጥም የሄድኩት ሥፍራን ላዘጋጅላችሁ ነው!!! ያዘጋጀሁላችሁንም ሥፍራ ስታዩ እጅግ ትደነቃላችሁ:: እናም በስተመጨረሻው እወስዳችሁና ፍቅሬ ምን ያህል እንደሆነ ስትረዱ እናንተን በማየት እደሰታለሁ:: በጥቃቅኑ ነገር እንኳን እናንተን በማሰብ ተጠንቅቄ ያዘጋጀሁትን ስታዩ ለእናንተ ያለኝን ጥልቅ ፍቅር፣ እንዲሁም ለእኔና ለመንግስቴ ስላደረጋችሁት ስለ እያንዳንዱ መስዋዕት እውቅናና ውለታ ማድረጌን መረዳት ትጀምራላችሁ::

"እንደ እውነቱ ከሆነ ያ ቀን እስኪመጣ ድረስ እጅግ እጓጓለሁ:: ምክንያቱም በስተ መጨረሻው በአምላካችሁና በፈጣሪያችሁ በየትኛውም ጊዜ ቢሆን፣ ስትቆሙም ሆነ ስትቀመጡ ወይም ስትወድቁ በተመሳሳይ መልኩ መፈቀራችሁን ስለምትረዱ ነው:: ያንን ቀን ለማየት እንዴት እጓጓለሁ! ለአንዳንዶቻችሁ ደግሞ ይህ በቅርብ ጊዜ ይሆናል::

"ታዲያ እዚህጋ ዋናው ነጥብ ምንድነው? ዋናው ነጥብ እኔ የምፈልገው በፍቅሬ ዋስትና እንዲሰማችሁ ነው:: ለምሳሌ ቀኑን በፆም ለማሳለፍ አስባችሁ ነገር ግን ጣፋጭ ምግብ ብትበሉና ወደ እኔ ለፀሎት ብትቀርቡ የእናንተን አብሮነት

እንዴት በደስታ እንደምቀበለው ብታዩ ትደነቁ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ስታጠፉ አፍራችሁ ከእኔ ከመሸሽና ከመራቅ ይልቅ በደስታ ሰላም ትሉኝ ነበር፡፡ እንደዚህ ስል ግን ለእኔ ስለ ምታቀርቡት ስጦታ ደንታ ቢስ እንድትሆኑ ፈቃድ እየሰጠሁ ሳይሆን ከዚህ የበለጠ ማድረግ ትችሉ እንደነበር እንድትገነዘቡ፣ ይህም ባይሆን ግን ከእናንተ ጋር ለመሆን እንደምጓጓ እንድታውቁ  ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፍቅሬን በዚህ መንገድ ስትረዱ መሰዋዕቱን በትግል ከማቅረብ ይልቅ በቀላሉ ለማቅረብ ጥንካሬ ሊሰጣችሁ ይችላልና ነው፡፡

"በዚህ ምድር ላይ አጋንንቶች እንደ አሁኑ ጊዜ ሙሽራዬን ከእጄ ለመንጠቅ የሞከሩበት ጊዜ ፍፁም ኖሮ አያውቅም፡፡ እያንዳንዳችሁን እንዴት እንደሚጠሏችሁ አታውቁም፡፡ ጠቅላላ አጀንዳቸው እናንተን ከእኔ መለየትና ወደ ገሃነም ጎትቶ ለማስገባት ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ለእግዚአብሔር የማትገቡ፣ በእኔ የማትወደዱና ተስፋ እንደሌላችሁ በመንገር ነው፡፡

" ነገር ግን የኔ ውዶች ይህንን የተስፋ ቃል ጠላቶቻችሁ እንዳይቀሟችሁ አጥብቃችሁ ልትይዙና በልባችሁ ሸሽጋችሁ ልታስቀምጡት ይገባል፡፡ በደከማችሁ ጊዜ እነዚህን የተስፋ ቃሎች በማንሳት በፍቅሬ እንደገና መተማመናችሁን አንሱ፡፡ ይህንን እወቁ ምንጊዜም ቢሆን እኔ ከእናንተ በተቃራኒው አልቆምም፡፡ ስለዚህም ሁልጊዜ በጎናችሁ እንደቆምኩ፣ ለሚቀጥለው እርከን ፀጋ እንደምሰጣችሁና እንደማጠነክራችሁ አስታውሱ፡፡ እየሄዳችሁ ያላችሁት ወደ ዘላለም ደስታ ነው፡፡ ስለዚህም አንገታችሁን ቀና አድርጋችሁ ለመደሰት ምክንያት አላችሁ፡፡ እኔ ያለሁት በጎናችሁ ስሆን የቆምኩት ደግሞ ለእናንተ ነው፡፡ ይህንን እየሰራን ያለነው አብረን ስለሆነ እናሸንፋለን፡፡"

## የመዳናችሁ ቀን ከምንግዜውም ይልቅ ቀርቧል - ፌብርዋሪ 28 ቀን 2021 ዓ.ም.

## Your redemption is hear, Feb 28, 2021

(ክሌር)፡- ጌታ የምትለን ነገር አለ?

ኢየሱስም. . . "የኔ ውዶች እናንተን ወደ መንግስተ ሰማያት ወስጄ ከእኔ ጋር እንድትኖሩ ለማድረግ እቸኩላለሁ፡፡ ወደ እኔ ልወስዳችሁ በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ ናችሁ፡፡ ብዙ ጠብቃችኋል ይህ ደግሞ ከባድ ነው፡፡ አሁን ግን እየቀረበ ነው፡፡ የተወደዳችሁ ራሳችሁን ንፁህ አድርጋችሁ ጠብቁ፡፡ በዙሪያችሁ ያሉትን ለመውደድ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ፡፡ በተለይም ጠላቶቻችሁን እንዲሁም ጨለማ ለሆነው አለም የኔን የፍቅር ሽታ ተዉላቸው፡፡

"በዚህ ወቅት በአለም ላይ ያለው ነገር እናንተ እንደምትገምቱት አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የምትገኙት በመቅሰፍት ምላጭ ጠርዝ ላይ ነው፡፡ ይህም የሆነው አለም ሊፈረድበት የመጨረሻው ጊዜ ስለደረሰ ነው፡፡ ህፃናቶችን ከአለም ሁሉ እንደሚያዘዋውሩ፣ እየተዘመተ ያለው ህፃናትን የማሰቃየትና የመግደል ሰይጣናዊ ተግባራት ይህም ከማህፀን ጀምሮ እስከ ታዳጊ ህፃናትን ያሉትን እንደሆነ አውቃችኋል፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ማንም ሰው ሊገምተው ከሚችለው በላይ እጅግ የእኩይ ተግባራት ናቸው፡፡ የምታደንቋቸው የሆሊውድ ተዋንያን ከምድር ካሉ የሰው ልጆች ሁሉ ከከፉዎቹ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሰዎች ከህፃናት ውስጥ አድሬናሊን የሚባለውን ንጥረ ነገር ለማውጣት ህፃናትን የሚያሰቃዩ ናቸው፡፡ ይህንንም ንጥረ ነገር በመጠጣት ሰውነታቸው እንደተጠበቀ እንዲቆይ ለማድረግና እድሜያቸው ከ50 እስከ 60 ቢሆንም ሲታዩ ግን ከ30 አመት በታች ይመስላሉ፡፡ የዚህም ሚስጥር በአድሬናሊን

የተሞላውን የህፃናቶችን ደም ስለሚጠቀሙ ነው፡፡ እነርሱ ለሚሰሩት ለዚህ አሰቃቂ ክፉ ድርጊት ምንም ፀፀት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ይህንን የሚቆጥሩት እንደ ልዩ መብት አድርገው ነው፡፡

"ህዝቤ ይሆናል ብላችሁ የማትገምቱት ትክክለኛ ያልሆኑ ብዙ ነገሮች በአለም ላይ እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ይህንን የምነግራችሁ ንጥቀቱ በአባቴ ዕይታ እንዴት በቂ ምክንያት እንዳለው ነው፡፡ ክፉ ሰዎች ከሰው ባህርይና መልካም ተግባር ውጪ በመሆን ገደቡን አልፈዋል፡፡ ከዚህ ከተበላሸ ትውልድ እንስሶች እንኳን ክብር አላቸው፡፡ ሰይጣን ይህ ትውልድ ክፉ እቅዱን እንዲደግፍለት ጥሩ አቅዶ ስለነበር አሁን ፍሬው እየታየ ነው፡፡

"ይህ ቢሆንም ግን ኃይሌንንና ምህረቴን ልገልጥላቸው ላሰብኳቸውና ሲወለዱ ጀምሮ ትክክለኛውን መንገድ እንዲስቱ ለተደረጉ ፀጋዬ አይጎድልባቸውም፡፡ ውዴ ብዙ ነገሮች እንደማይገባሽና በአይምሮሽ ውስጥ ማለቂያ የሌለው ጥያቄ እንደሚመላለስ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው እየሰራሁና እየፈቀድኩ ያለሁትን ዝም ብለሽ እንድታምኚኝ የጠየቅሁሽ፡፡ ዙሪያሽ ድምፄን በሚሰሙና ምን እየሰራሁ እንደሆነ በሚገባቸው ነፍሶች ከብቤሻለሁ፡፡ እናም አንቺ ስትነጠቂ እነርሱ ይተኩሻል፡፡ ምንም ልትጨነቂ አይገባሽም፡፡ በአንቺ የጀመርኩትን ስራ ለመጨረሻው ጊዜ መሪ አድርጌ በመረጥኳቸው በተቀደሱ እጆችና ችሎታ ባላቸው ሰዎች ይቀጥላል፡፡ የጀመርኩትን እቀጥላለሁ ደግሞም ፍሬ እንዲያፈራ አደርጋለሁ፡፡ ወደ ምድር ስትመለሺ ከሄድሽ በኋላ ምን እንደተሰራ በማየት ትደነቂያለሽ፡፡ እውነት የሰራጫል፣ ውይይቱም ይቀጥላል፣ ታናናሾችም በእኔ መጠለያ ያገኛሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያኔን ከውድቀት የሚያነሳ ደረጃውን የጠበቀ ቅድስና ይመሰረታል፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ሙሽሮቼ ስለታዘዙ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ለመሆን የቀረሽን ጥቂት ዘመን ወደ ዘላለማዊው፣ ወደማያልቀውና ክብር ወደሞላበት ለመግባት ከእኔ ጋር በመሆን፣ ሙዚቃ በመፃፍ፣ በመዘመርና ስራሽን በደስታ በመስራት እንድታሳልፊ እፈልጋለሁ፡፡ እንዲሁም ገና ብዙ የሚሰራ ሥራ ወደፊት አለ!!!

"እስካሁን ምን መስራት እንዳለበት ብዙ ያልገለጥኩልሽ ነገር አለ፡፡ ይህም እጅግ ታናሽ ስለሆንሽና በእኔ ስለታመንሽ ነው፡፡ ነገር ግን በዛ ጊዜ ለማመን ትቸገሪያለሽ፡፡ በተሰበረ እርሳስ እንዴት ቆንጆ አድርጌ እንደምፅፍ ትረጃለሽ፡፡ እንዳንቺ ደግሞ ታናሽ የሆኑና የተሰበሩ ብዙ አሉ፡፡ እናም በእነርሱም መፃፌን እቀጥላለሁ፡፡

"በጠቅላላ አዲስ የሆነ እውነተኛ የቅድስና ደረጃ እየመጣ ነው፡፡ ከአሁን ወዲያ የምሰራው በዲግሪ በመመረቅ ወይም ከስም በፊት በሚለጠፍ ስም ምክንያት ሳይሆን እኔ የምሰራው ታናናሾች በሆኑ፣ እኔ ራሴ መፃፍና መሳል በምችልባቸው፣ እኔ ራሴ ሙዚቃን መስራት በምችልባቸው፣ ፈውስ ማካሄድ በምችልባቸው፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኔን እኔ ራሴ ማስተዳደር በምችልባቸው ንፁህና ቅን ልብ ባላቸው ነው፡፡ ምክንያቱም በታናሽነት ብዙ መስራት እችላለሁና ነው፡፡

"እናም ለሁላችሁም እንዲህ እላለሁ እስካሁን ህልማችሁን ሥራ ላይ ተግባርያዊ ያላደረጋችሁ እንዲገባችሁ የምፈልገው ምድሪቷን ካነፃሁ በኋላ ስጦታችሁን የተራቡ ነፍሶችን ለመለወጥ ትጠቀሙባቸዋላችሁ፡፡ በመንፈሴና በመላዕክቶቼ እርዳታ፣ እንዲሁም ከውስጣችሁ በነፃነት በሚፈሰው በእያንዳንዱ መንፈሳዊ ስጦታዎች እገዛ ለእድገታቸውና ለለውጣቸው ተመድባችሁ ትሰራላችሁ፡፡ ይህንን የምነግራችሁ ባልሰራችሁት ስራ ማዘን ስለሌለባችሁ ነው፡፡ ምድርን ሰርቼ ስጨርስ መልሳችሁ እንድትገነቡ፣ እንድትደግፉ፣ እንድታበረታቱና በምድሪቱ ላይ የእኔን መንገድ እንድትገነቡ እፈልጋችኋለሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ በሙስና የተዘፈቀውና እምነት የሚያጎድለው ለመምራት የተመረጡትን በማስፈራራት

መግዛት የለበትም፡፡ ከአሁን ወዲያ አስፈራርቶ መዝረፍ፣ ዛቻና ጉቦ አይኖርም፡፡ ከአሁን ወዲያ ሥራ እንዲሰሩ የተመደቡ ለራሳቸው መልካም ነገር የሚፈልጉ አይሆኑም፡፡ በአንፃሩ ግን የኔንና የሌሎችን ፈቃድ የሚፈፅሙ ይሆናሉ፡፡

"መላዕክቶቼ ሁሉንም ዞሮ በመቆጣጠር አገልጋዮቼን ይረዳሉ፡፡ እንዲሁም የክፉን መንገድና ብልሽት ለመከተል የሚሞክሩትን ደግሞ ይደመስሷቸዋል፡፡ ውሸት መናገር፣ መስረቅ፣ ማጭበርበርና ሌሎች ህብረተሰቡን ሲገዙ የነበሩ አስከፊ ኃጢያቶች ከአሁን ወዲያ ሊኖሩ አይችሉም፡፡ እነዚህን ነገሮች ለማድረግ የሚሞክሩ እጅግ ይቀጣሉ፡፡ ስለዚህም የሚያብበው መልካም ብቻ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ለርህራሔ ገደብ የለውም፡፡ ስለዚህም በኃጢያት የተጣመሙትን ለመፈወስና እንደገና ለማስተማር ፕሮግራሞችን እመሰርታለሁ፡፡ እርግጥ ነው በዚህ ወቅት ባለፈ ህይወታቸው በኃጢያት ይኖሩ የነበሩ በህይወት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ምድሪቱ ስትታደስ ክፉ የሰሩ ሰዎች ላይነፁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ንስሐ እንዲገቡና እንዲለወጡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ እኔ የምህረት አምላክ ነኝ፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ የተሰጣችሁ ስጦታዎች በማደግና በማንፀባረቅ እጅግ የከበረ ፍሬ ያፈራል፡፡ ለቆሰሉትና ለተጎዱት የወደብ ላይ ብርሃን፣ የፍቅርና የደህንነት ወደብ ትሆናላችሁ፡፡ እናንተ ለእኔ የተበላሸውን የሰው ልጅ እንዲሁም ለማመን የሚያቅተውን ስቃይ የደረሰባቸውን ለመፈወስና ለማፍቀር ብቻ የምትፈልጉ የብርሃን አገልጋዮች ትሆናላችሁ፡፡ ሁሉም ይፈወሳል፡፡ ማንም ቢሆን ስነ ልቦናዊ፣ አይምሮአዊና አካላዊ ጉዳት ደርሶበት የማይፈወስ የለም፡፡ ሁሉም በእኔ ፍቅር መለወጥ አለበት፡፡ እናም የእኔ ሙሽራ በዚህ የፈውስና የለውጥ ሥራ የመንግስቱ መልዕክተኞች ሆናችሁ ትሰራላችሁ፡፡ በእኔ ቅባት፣ ኃይል፣ ፍቅርና ርህራሔ ትንቀሳቀሳላችሁ፡፡ በነፃም እንደተቀበላችሁ በነፃ ታካፍላላችሁ፡፡ ይህ ነው የሚመጣው መንግስቴና የሚከናወነውም የእኔ ፈቃድ፡፡

"ስለዚህ ለእናንተ እንዲህ እላለሁ የተሰጣችሁን ጊዜ ሳትጠቀሙ ስለተነጠቃችሁ አትዘኑ፡፡ እነዚህን ስጦታዎች ጥቅም ላይ ሳይውሉ እንዲቀሩ አልሰጠኋችሁም፡፡ እኔ የሰጠኋችሁ ተኮትኩተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው፡፡ መላዕክቶች እንደሚያገለግሉ ፈውስን በምድር ላይ ለማምጣት በሙላት ለማገልገል እንድትችሉ በመንግስተ ሰማያት ትማራላችሁ፡፡ ይህም ስነ ፅሑፍ፣ ጥበብ፣ ሙዚቃ ወይም ሌሎች መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚጠቅሙት መልሶ ለመገንባትና ለመፈውስ ነው፡፡ እነሆ እኔ ልመጣ በደጅ ነኝ፡፡ ስለዚህም የመዳን ቀናችሁ መቃረቡን አውቃችሁ፣ አንገታችሁን ቀና አድርጉ፣ ልባችሁን አዘጋጁ፣ የሠርግ ልብሳችሁን አንፅታችሁና መብራታችሁን ሞልታችሁ ተዘጋጅታችሁ መምጣቴን ተጠባበቁ !!!

**ትልቁ መንቃት/ዘ ግሬት አዌክኒግ/ ምንድነው? - ማርች 8 ቀን 2021 ዓ.ም**

**What is the great awakning, March 8, 2021**

*እስካሁን አይተንና ሰምተን የማናውቀውን የአለሙን ድንቅ ነገር ለመረዳት እንድንችል ጌታ አይኖቻችንን፣ ልባችንና አይምሮአችንን ይክፈት፡፡ አሜን፡፡*

*የተወደዳችሁ ቤተሰቦቼ የተማርኩትን ነገር ለእናንተ ለማካፈል በደንብ እንዲገባኝ ለማድረግ ሳምንቱን ሙሉ እየሞከርኩ ነበር፡፡ አንድን መልዕክት ለማቅረብ ለሦስት ቀናት ያህል ስታገል ነበር፡፡ በመጨረሻም መልዕክቱ እንዲገባችሁ መሰረታዊ የሆነውን ነገር እንዳልገለጥኩላችሁ ተረዳሁ፡፡ ይህም ለአለማችን ሊቀርብ ያለው አዲስ ኃይል ነው፡፡ ስለዚህም ነገሩን እንደገና ከስር መሰረቱ መጀመር አለብኝ፡፡ መልዕክቱም ይህ ነው፡፡*

*ነገሩ የጀመረው ፕሬዚዳንት ትራምፕ በነበረበት ጊዜ ጎን ለጎን ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ በመጀመሪያ ያጋጠሙኝ ቡድኖች ነበሩ፡፡ ከዚህም ቡድን ውስጥ ዶክተር ቻርሊ ዋርድ የሚባል ክርስቲያን አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በቢት ሹት፣/Bit Chute/ በራምብልና በቴሌግራም ነው፡፡ በፊት በፊት በዩ ቲዩብ ላይም ነበር፡፡ አሁን ግን ከዚያ አስወጥተውታል፡፡ ይህም ሰው ከአለም ላይ ብዙ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ስለሚሰበስብ ቴሌግራም ቻናሉን ሰብስክራይብ አደረግሁ፡፡ እነዚህም መረጃች ሆን ተብለው ከህዝቡ የሚደበቁና ከሚታየው በስተጀርባ የሚገኙ ድርጊቶችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ እርሱና ሌሎች ብዙዎች ይመጣል እየተባለው ግሬት አዌከኒግ ወይም ትልቁ ከእንቅልፍ መንቃት እየገለፁ ይገኛሉ፡፡ እንደሚመስለኝ ይህ ነገር በአለም ላይ እየተካሄደ ካለው ቆሻሻን ከማገፃት ጋር፣ እንዲሁም በጥልቁ መንግስት የተወሰደውን የአሜሪካን የፋይናንንስ ሁኔታ እንደገና ለአሜሪካ ህዝብ ከመመለስ ጋር የተያያዘ ሲሆን ያገኘሁት ግን ከዚህም እጅግ ጥልቅ የሆነ ነገር ነው፡፡*

*በአጭሩ ስገልፀው በቅርብ ጊዜ አለምን የሚለውጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየመጡ ነው፡፡ ይለውጣል ስላችሁ ፍፁም የሚለውጥ ማለቴ ነው፡፡ እነዚህም ነፃ ኢነርጂ/ኃይል/፣ ማንም ሰው ሊጓዝበት የሚችል የአየር ላይ ትራንስፖርት፣ እንዲሁም ከዚህ ሁሉ የሚደንቀው ደግሞ የህክምና አልጋዎች /Med beds- ሜድ ቤድስ/ ጉዳይ ይገኙበታል፡፡ አቫተር/ Avatar/ የሚለውን ፊልም አይታችሁ ከሆነ ትክክለኛውን የሰው አካል ወደ አቫተር ወይም የአቫተር አካል ወደ ትክክለኛው የሰው አካል ሲለውጥ ያያችሁት ነው የህክምና አልጋዎች ወይም ሜድ ቤድስ የሚባለው፡፡ እነዚህ ሜድ ቤድስ የሚያደርጉት ነገር የእናንተን ዘረመል ያነቡና በፕላዝማ ኤነርጂ አማካኝነት አካላችሁን እጅግ ምቹ ወደሆነ አሠራር ይመልሱታል፡፡*

"እነዚህ የህክምና አልጋዎች ወይም ቤድ ሜድስ ልባችሁን እንደገና ፍፁም ሊገነቡት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም አራተኛ ደረጃ የሚገኘውን ሊምፎማ የሚባለውን የካንሰር አይነት/*Lymphoma/* በ10 ደቂቃ ውስጥ ያድኑታል፡፡ እግሮችንና እጆችን እንዲሁም ማንኛውንመ የአካል ክፍል መልሰው ያበቅላሉ፡፡ ይህም የሚከናወነው ህመም ሳይኖርና በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰውነታችሁን በመጠገን እንዳያረጅ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህ በጣም የሚደንቅ ነገር ነው!!! ቻርሊ፣ ሮበርት ዴቪድ እስቲል እንዲሁም ስምኦን ፓርክ የሚባሉትን ሰዎች ያካሄዱትን ውይይት ስሰማ የ5D አለም የሚለውን ሲደጋግሙት ሰማሁ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወርድና ስፋቶችን (*dimensions*) ነው፡፡ እነርሱ እንደሚሉት አብዛኛዎቻችን የምንኖረው በ*3D አለም ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን  የ5ኛው ወርድና ስፋት ደረጃ (5D) የበለጠ ፈርጀ ብዙ ወርድና ስፋት ያለው ይመስላል፡፡* ለምሳሌ *የ4D አለም የሚያመለክተው የሰውን አስተሳሰብ ማወቅን፣ በቦታው ላይ በአካል ሳይገኙ ነገሮችን ማየትንና መስማትን፣ እንዲሁም በቃል መነጋገር ሳይኖር ከሰው ጋር መግባባት መቻልን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ደግሞ በመንግስተ ሰማይ እንደሚቻልና አሁንም በፀሎት ወቅት ይህ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን በዚህ በሚወራው ግሬት አዌከኒንግ ወይም ትልቁ ከእንቅልፍ መንቃት ይህ ችሎታ እንደሚኖርና ይህም ደግሞ ከአሉታዊ አስተሳሰብ በመውጣት አውንታዊና ተስፋ ሰጪ ወደሆነ ሽግግር እንደሚደረግ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት/ bilocation/ የ5ኛው  ወርድና ስፋት ከስተት ምሳሌ ይመስለኛል፡፡ ለእነዚህ ቃላቶችና አባባሎች አዲስ ስለሆንኩ ስህተት ከሰራሁ እባካችሁ አርሙኝ፡፡*

በሜድ ቤድስ መታከም ምን እንደሚመስል ትንሽ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ያህል ምሳሌ ልስጣችሁ፡፡ ለህክምና ቀጠሮ ትይዛላችሁ፣ ወደ ህክምናው ሄዳችሁ ክዳኑ መስታወት ሆኖ ወደሚያሳይ መሳሪያ ላይ ትወጣላችሁ፣ ከእናንተ ዘረመል ጋር በሚስማማ ፕላዝማ ኤነርጂ ይመረምራችኋል፡፡ ከዚያም ማሽኑን የሚያንቀሳቅሰው ሰው በተገኘው የምርመራ

ውጤት መሰረት እንድትድኑ ፕሮግራም ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም በደቂቃዎች ውስጥ ከማንኛውም በሽታ ፍፁም ድናችሁ ትወጣላችሁ፡፡ እግር ወይም እጅ ከሌላችሁ ይበቅልላችኋል፡፡ የልብ ድካም ካለባችሁ አዲስ ልብ ይኖራችኋል፡፡ አይምሮን የሚያዛባ ነገር ካጋጠማችሁ ያከማችኋል፡፡ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት የስነ ልቦና ቀውስ የደረሰባቸውን በዚህ ማሽን ማከም ተችሏል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን በአለም ላይ እየተካሄደ ያለው ነገር ከምድር በታች ካሉ ከተሞችና ከመሽሎኪያ ዋሻዎች ህፃናቶችን ከቦታ ወደ ቦታ ከሚያዘዋውሩት እጅ እየታደጓቸው የደረሰባቸውን የአይምሮ ጉዳትና የማይፈለጉ ሐሳቦችን በዚህ አይነት መንገድ እያከሟቸው ይገኛል፡፡

ይህ ለሰለጠነው አለም ምን ማለት እንደሆነ ትረዳላችሁ??? ይህ ማለት ከአሁን ወዲያ ጎጂ ለሆኑ መድኃኒቶች የሚወጣ ውጪ የለም! ኦፕራስዮን የለም! አርቲፊሻል እግሮችና እጆች አያስፈልጉም! አይነ ስውርነትና ያለመስማት የለም፣ ኦቲዝም የለም! የአይምሮ መዛባት የለም! በጉዳት ምክንያት የሚከሰት የአይምሮ መታወክና ድባቴ የለም! ማለት ነው፡፡ ይህ ህክምና  የሚከናወነው ደግሞ በጥቂት ደቂቃዎችና ካለምንም ህመም ነው፡፡

በተጨማሪም ነዳጅ፣ የተመሰቃቀሉና አየሩን የሚበክሉ መኪናዎች አያስፈልጉም፡፡ ለኤልክትሪክ ወይም ለማሞቂያ ክፍያ አያስፈልግም፡፡ እንዲሁም በእንጨት የሚሰሩ ምድጃዎች ወይም በጋዝ የሚሰሩ ማሞቂያዎች አያስፈልጉም ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ አለም ከአሁን ወዲያ ምን እንደሚመስል ልትገምቱ ትችላላችሁ? እጅግ መልካም ከመሆኑ የተነሳ እውነት ይሆናል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን ታስላ/ *Tesla/ የእነዚህን ቴክኖሎጂ ጉዳይ ግልፅ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ቢሆን ግን በስግብግብ ሰዎች ምክንያት እስካሁን ግልፅ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡* አሁን ግን እነዚህ ስግብግብ ሰዎች ተይዘው በሚሊታሪ ፍርድ ቤት ቀርበው እየተፈረደባቸው ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙዎቹ ገንዘብ እየተከፈላቸው አሜሪካን ለማጥፋት ከተነሱ ከአለም ከተወጣጡ በጣት ከሚቆጠሩ ክፉ ሰዎች ጋር በማበር ይሰሩ እንደነበረ መረጃው ይፋ በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሰዎች የፈፀሙት ነገር እጅግ ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ይህም ህፃናትን በማሰቃየት፣ ከእነርሱ ደም በመውሰድ፣ የወሲብ ባርያ በማድረግ፣ እንዲሁም ህፃናቱን በመግደል እንደ መዝናኛ በመቁጠራቸው ነው፡፡
የተወደዳችሁ የዚህ አለም የጨለማው ወገን ከምትገምቱት በላይ ከምንም ነገር እጅግ የጨለመ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የአገሩ አርበኞችና መልካም የሆኑ የሰራዊቱ መሪዎች ወደ ትራምፐ በመሄድ የተደረገውን ጭካኔ የሞላበት አድራጎት በማቅረብ አገሪቷን ወደ ቀደመ ሁኔታዋ ለመመለስ እንዲረዳቸው ጠይቀውት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ አሁን ባለው አስተዳደር ፊት ለፊት የሚደረገው ሁሉ እንዲሁ ለታይታ የሚደረግ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ሰዎች ይህንን ጨዋታ እንዲጫወቱ የተደረጉ ሰዎች እንጂ ትክክለኞቹ አይደሉም፡፡ ይህ ሁሉ በቅርብ ግልፅ ይሆናል፡፡ እስከዛው ግን እንደሚታየው ሆኖ ይቀጥላል፡፡

*የጊዜውን ሁኔታ ስከታተል በአርበኞቹ አመለካከት መሰረት የሚመጣውን አለም የሚለውጠውን የ5D አለም እንድተዋወቅ ተደረግሁኝ፡፡ ነገር ግን ባየሁት አንድ ነገር ተቸግሬያለሁ፡፡ ይህም በቪዲዮው ሜድ ቤድ /med bed/ የሚባለውን ያስተዋወቀችውና መረጃውን የሰጠችው ሴት በመጨረሻ መግለጫዋ ላይ ይህ ቴክኖሎጂ ከዚህ ምድር ባልሆኑ ማስተሮች እንደተሰጠ ገለፀች፡፡ በሌላ አነጋገር ከሌላ የሰለጠነ አለም የመጡ ሰዎች ማለት ነው፡፡ እናም ፕሮግራሙን ጨርሳ ስትወጣ እራሷን የገለፀችው ካሚራ በሚል ስም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሰውና እንስሳት በላቦራቶሪ ተዳቅለው የተሰጣቸው ሳይንሳዊ መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰውነቱ የአሳማ ሆኖ ራሱ የሰው ማለት ነው፡፡ እናም ጨርሳ*

*ስትወጣ የተሰማኝ ነገር ከተፈጥሮ ህግ ውጪ (psychic) ከእኛ ጋር ለመገናኘት ከጋላክቲክ ፌደሬሽን ኦፍ ላይት (Galactic Federation of Light) የተመደበችልን እንደሆነ ነው፡፡*

*አሁን ይህንን እንመልከት፡፡ እኔ እንደማምነው የሜዲካል አልጋዎቹ /The med beds/ በራሳቸው አዲስ ቴክኖሎጂ ከመሆን ሌላ ገለልተኛና ምንም ያልሆነ ነገር ነው፡፡ ይህም ልክ ኢንተርኔትና ኤም አር አይ/ MRI/ ቴክኖሎጂዎች ገለልተኛ እንደሆኑ ሁሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ችግሩ ሜድ ብድስ የተባለው ማሽን ከኤሊየንስ /aliens/ ጋር መያያዙ ነው፡፡ እናም ቀድሜ እንደነገርኳችሁ ኤሊየንስ የወደቁ መላዕክቶችና አጋንንቶች ሲሆኑ አካል ለብሰው ወደ ምድር የመጡ ናቸው፡፡ እኔ እንደማምነው ከሆነ እነዚህ የሚንቀሳቀሱት በ5ኛው ወርድና ስፋት አለም (The fifth-dimension) ውስጥ ነው ወይም የተሰሩበት ነገር (substance)* በተለያየ ወርድና ስፋት/ *(inter-dimensional) መንቀሳቀስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው በቅፅበት መታየትና መሰወር የሚችሉት፡፡ እኛም በመንግስተ ሰማይ እንደዚህ እንደምንሆን አምናለሁ፡፡ በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ልምምዱ ያላቸው ደግሞ የሚንቀሳቀሱት በልዩ ልዩ ወርድና ስፋት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ምንም ከፋት የለውም፡፡ ይህ በፊሊጶስ ህይወት ውስጥ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ሲያገለግል ተከስቶ ነበር፡፡*

*ነገር ግን ይህ ሜድ ቤድስ እና የ5D አለም ሲቀርብ ከተሰጠው መረጃ ማጠቃለል የሚቻለው እነዚህን ቴክኖሎጂዎች የሰጡን እጅግ የሰለጠኑ አካላት እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እና ደግሞ መንፈሳዊ የበላይነት እንዳላቸው ለማሳየት ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰላም፣ ስለ ብርሃን፣ ስለ ስምምነትና ስለ አዲስ አለም ይናገሩ ነበር፡፡ የኔ ጥያቄ "ጌታችሁ ማነው?" የሚል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእናንተ ጌታና አዳኝ እንደሆነ ትመሰክራላችሁ? ወይስ የአዲሱ ዘመን እንቅስቀሴ እንደሚያምነው ከሌላ አለም የመጡ ጌቶችን /ascended master/ ታምናላችሁ? ለእናንተ ኢየሱስ ማነው?*
*በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ መካከለኛውን ትራንስ/ a trance medium/ ሳጠና ኢየሱስ የሚቆጠረው ከላይ ከመጡት ብዙ ጌቶች እንደ አንዱ ጌታ ተደርጎ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ በድንቅና በምልክቶች ተገልጦልኝ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ገለጠልኝ፡፡ ሌሎቹ የተባሉት ነገሮች ሁሉ ውሸትና ሰዎችን ለማሳትና በመጨረሻም በአንድ ሰው ውስጥ የሚያድረውን ሰይጣን እንዲያመልኩ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም ማጭበርበር ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ መልዕክቱ በሁለተኛው ምዕራፍ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ትልቁ ማሳት ብሎ የገለፀው ነው፡፡*
"ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" *(2ኛ ተሰሎንቄ 9-12)*

*አሁን እኔን ያሳሰበኝ ነገር ሰይጣን ይህንን አዲስና ገለልተኛ የሆነውን ቴክኖሎጂ እንደ ትሮይ ፈረስ መጠቀሙ ነው፡፡ ይህም የሰዎችን ልብ ከእግዚአብሔር የሚመልስና ከላይ የመጡ የሚባሉትን አካላት እንዲያመልኩ የሚያደርግ፣ እንዲሁም ፍፁም ልዩ ቅርፅ የያዘ ሃይማኖት የሚያስተዋውቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ሃይማኖት መሰረታዊ ኃሳቡ ኃጢያትን የሚፈቅድና ሰዎች እንደፈለጉ እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው፡፡*

*እዚህ ላይ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ እኔ እንደማምነው ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ያዳነኝ አንድ ነገር ቢኖር እውነትን ብቻ ፈላጊ በመሆኔ ነው፡፡ ያገኘሁት ፍፁም እውነት መሆኑን እስከማወቅ ድረስ በምንም ነገር መረጋጋት አልቻልኩም ነበር፡፡ እናም በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ እኔ የማምነውን የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ አማልክትን እንዲሁም አንድ፣ እውነተኛና ህያው የሆነውን አምላክ ልዩነት በፀጋው ሲገልፅልኝ በውስጥ ማንነቴ በዘመኔ ሁሉ ስፈልገው የነበረው እውነት ይህ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ በተጨማሪም እርሱን በመከተሌ ያገኘሁት ፍሬ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ መራኝ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም አልሜ የማላውቀው መከናወን ደግሞ በህይወቴ ተከሰተ፡፡ በእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ውስጥ እየኖራችሁ መሆኑን እንደማወቅ ደስ የሚያሰኝ ስሜት የለም፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ስትሆኑ በዙሪያችሁ የምትሰሩትን ስራ በሚያግዟችሁ ሰዎች ትከበባላችሁ፡፡ በዙሪያችሁ ከተከበባችሁት ረብሻ በላይ በሰላም ትኖራላችሁ፡፡ እንዲሁም ህይወታችሁ በምትኖሩት እውነት ፍሬ ያፈራል፡፡ እናም ደግሞ ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕት ሌሎችን ወደ እርሱ በማምጣት የእግዚአብሔር ወዳጆች ትሆናላችሁ፡፡*

*ጌታ ስለዚህ ነገር ልትለን የምትፈልገው ነገር አለ?*

ኢየሱስም . . . " በአየር ላይ በተለያየ ቀለም ፣ በተለያየ ቅርፅና መጠን አካል ለብሰው የሚመጡትን አጋንንትና መላዕክት የሚመርጡ በትልቁ ማጭበርበር ውስጥ ተጠምደው ይጠፋሉ፡፡ ይህም የአውሬውን ምልክት በመቀበልና ይህንን አሳዛኙን ማታለያ በማመናቸው ነው፡፡ ይህንን የማጭበርበሪያ መንገድ የሚያምኑ እውነተኛ መንፈስን የመለየት ፀጋ የሌላቸው ናቸው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን ተራና ርሑሩህ የሆኑት፣ እንዲሁም ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው በዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉ መሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም የተወሳሰበና የበራላቸው ምሁራኖች በዚህ የሚጠመዱ ናቸው፡፡ እነዚህም እግዚአብሔርን እንደ አናፂ ወይም በትንንሽ ሁኔታ ውስጥ አለ ብለው የማይቀበሉ፣ እንዲሁም በሰራተኛው መደብ ወይም ዳግም በተወለደው ተራ አማኝ ውስጥ አለ ብለው የማይቀበሉ ናቸው፡፡

"በመንፈስ የሚያውቁኝ ብቻ ናቸው የሚፀኑትና ከወደቁ መላዕክቶች ጋር ስምምነት የማያደርጉት፡፡ እኔ ከላይ ከመጡት ከእነርሱ ማስተሮች እንደ አንዱ እንደሆንኩና ያስተማርኩት ግን ስህተት እንዳለበትና ኃጢያት እንደሆነ ለህዝቡ ያቀርባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በፍፁም ልባቸውና ማንነታቸው ከእውነት ጋር የተጣበቁ ይህ አባባል የሚያሳስት ነገር እንዳለበት ይጠረጥራሉ፡፡

"በስራ ላይ ሊውሉ ያሉ ቴክኖሎጂዎች በራሳቸው ገለልተኛና መልካም እንደሆኑ በደንብ ግልፅ ላደርግላችሁ፡፡ ነገር ግን ገበያ ላይ የሚውሉት ከበላይ ከመጡ አለም አቀፋዊ ስልጣኔ ካላቸው ከጋላክሲ አካላት ነው በሚል መረዳት ጋር ተያይዟል፡፡ በሌላ አነጋገር ይህንን ሁሉ ስቃይ ሊያስወግድ የሚችል ቴክኖሎጂ የሰጠን አካል እንዴት ክፉ ሊሆን ይችላል? የሚል የሚያስት አመለካከትን ለማምጣት ነው፡፡ መልሱ ቀላል ነው፡፡ እነዚህ አካል ለብሰው የመጡ የወደቁ መላዕክቶች ናቸው፡፡ እነርሱ እጅግ ብልህና ስለተለያዩ የአለም ወርድና ስፋት ፊዚክስ (*inter-dimensional physics of the worlds)* በደንብ የገባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም በመነሳት ለሁኔታው እንዲስማማ በማድረግ የሚያሳምን ውጤትን ይዘው መጥተዋል፡፡

"ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን አድርገው የሚያቀርቡት በጎ አድራጊና ከሁሉ የላቀ ንቃተ ህሊና ያላቸው አስመስለው ነው፡፡ እናም እነርሱ እኔን እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው አይቀበሉም፡፡ ምክንያቱም የእነርሱ ጌታ ሰይጣን ስለሆነ ነው፡፡ እውነተኛ ፍላጎታቸው እናንተንና መልካም የሆነውን ሁሉ ለማጥፋት ነው፡፡ እኔን እንደ አዳኝ አድርገው ያልተቀበሉትን ሲያዩ ይተማመናሉ፡፡ ምክንያቱም ለስህተትና ለትልቁ ማታለል ስለተውኳቸው ነው፡፡

"በእውነትም ይኼ ትልቁ ማታለል ነው፡፡ ይህ ደግሞ መንፈስን የመለየት የሰላ ችሎታ፣ ቃሉን የማወቅና ከወጥመዱ የመራቅ ጉብዝናን ይጠይቃል፡፡ አያችሁ ሰይጣን መንግስቱን በአንድ በኩል ለማምጣት ካልቻለ በሌላ መንገድ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም ከእኔ ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት ከሌላችሁ እነርሱ በሚሰጡት ሥነ - አመክኖ (*logic)* ትደገፋላችሁ፡፡

"ህዝቤ እባካችሁ በሙሉ ልባችሁ ከእኔ ጋር ተጣበቁ፡፡ በተጨማሪም የነቁትን፣ ነገር ግን በስህተት ውስጥ ያሉትን አስጠንቅቋቸው፡፡ የሚስቱት አብዛኛዎቹ በተለየ መልኩ መልካምና ደግ ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በጠለቀ ወዳጅነት ደረጃ አያውቁኝም፡፡ ከእኔ ጋር ያላቸው ግንኙነት ከተለመደው የሃይማኖት ልምምድ ያለፈ አይደለም፡፡ ስለዚህም መንፈስን የመለየት እውቀታቸው የተጣመመ ነው፡፡ በሃይማኖት ስላደጉ ብቻ ስለ ክርስትና እምነት ማወቅ ያለባቸውን ሁሉ እንደሚያውቁ ነው የሚያምኑት፡፡ በእውነት የሚያውቁ ቢሆን ኖሮ ትልቁን ማታለል ለይተው ያውቁት ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ኢየሱስ ነኝ ከሚል አካል ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከእነርሱ ጋር ያለሁት እኔ ሳልሆን አታላይ ኢጋንንት ነው፡፡ ይህም በእሳት ምሰሶ ውስጥ ተገልጬ አንቺን ከተመሳሳይ ኢጋንንት ነፃ እንዳወጣሁሽ ማለት ነው፡፡

"እያንዳንዳችሁን እጅግ አፈቅራችኋለሁ፡፡ ነገር ግን ሊገባችሁ የሚያስፈልገው ነገር ጠላት የእናንተን ትኩረት ለመቀየር አከራሪ ከሆኑት፣ እንዲሁም መፅሐፍ ቅዱስን ተጠቅመው ስህተትን ከሚፈልጉና ከሚተቹ ጋር ለማገናኘት ሙከራ ያደርጋል፡፡ ይህ ሃይማኖት እንጂ ወዳጅነት አይደለም፡፡ ለእናንተ ያለኝ ፍቅር ገደብን አያውቅም፡፡ ደግሞም ልቤ በመንግስተ ሰማይ ለእናንተ ያቀደው መልካም እቅድ እንጂ ሌላ ምንም የለውም፡፡ ስለዚህም እባካችሁ አጥፊ ኃይል ይህንን አስደናቂ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የእናንተን መተማመን ከዚያም አምልኮን ለማግኘት ሊጠቀምበት እንደሚችል ለአንዳፍታም እትዘንጉ፡፡

"ውዶች ጌታ እኔና እኔ ብቻ ነኝ፣ ሌላ ማንም የለም፡፡ ለእናንተ ያለኝ እቅድ ሁሉ አዎንና አሜን ብቻ ነው፡፡ የምሄደው ሥፍራን ላዘጋጅላችሁና እኔ ባለሁበት እናንተም እንድትሆኑ ነው ብዬ ነግሬያችኋለሁ፡፡ ውዶች በሰማይ ሥፍራን ሳዘጋጅላችሁ ከላይ እስከ ታች እያንዳንዱ ነገር የተሰራው እናንተ ከምትወዱት ነገር ነው፡፡ የተወደዳችሁ እያንዳንዱን የልባችሁን ጥቃቅን ፍላጎት አውቃለሁ፡፡ እናም ስታልሙት የነበረውን ህይወት ለእናንተ ለመስጠት ደስተኛ ነኝ፡፡ ይህም እኔን አምናችሁ ለእኔ በመኖራችሁ የሚደረግላችሁ ስጦታ ነው፡፡

"ስለዚህ መፅሐፍ ቅዱስን፣ እንዲሁም ከእኔ ጋር እውነተኛ ወዳጅነትን ችላ አትበሉ፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ነገሮችን ሲያቀርቡ ያልተጣራና ጠባብ በሆነ መንገድ ነው፡፡ በሚቀጥለው መልዕክት ስለዚህ ማጭበርበር /*deception/* ሰፋ ባለ ሁኔታ እገልፀዋለሁ፡፡ እኔን ማወቅ የላቀ መፅናናትና ደስታ አሁን ከእናንተ ሞልቶ ይፍሰስ፡፡ አሜን፡፡"

**የወደቁ መላዕክት /*Aliens*/ መጓጓዣዎች አየሩን ይሞሉታል - ማርች 10 ቀን 2021 ዓ.ም.**

**Alien Vehicles Will Fill the Skies, March 10th, 2021**

*ጌታ ብርታቱን፣ ጥበቡንና ፅናቱን ይስጣችሁ፡፡ ቅዱስ ስሙን እንድትጠብቁና በሁኔታዎች ሁሉ እንድትጠቀሙበት ያስተምራችሁ፡፡አሜን፡፡ ይህንን ቪዲዮ ከማዳመጣችሁ በፊት ዘ ግሬት አዋከኒንግ ምንድነው? የሚለውን ቪዲዮ መጀመሪያ እንድታደምጡት እመክራችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ይህንን መልዕክት በደንብ ለመረዳት ያ ቪዲዮ መሰረታዊ የሆኑ ብዙ መረጃዎችን ስለሚሰጣችሁ ነው፡፡*

*የተወደዳችሁ የምጀምረው በምስራቹ ቃል ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስን ካወቃችሁትና ዳግም ተወልዳችሁ ጥልቅና እውነተኛ እምነት በጌታ ካላችሁ ስነ - ፍጥረት ሁሉ ለስሙ የማይታዘዝበት ምንም ሁኔታ የለም፡፡ ሰው፣ እንስሳት፣ ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጥረታት(ET)፣ በሽታ፣ ጅራታማ ኮከብ ፣ የእሳተ ጎሞራ ቅልጥ ድንጋይ ፣ ሱናሜ የትኛውም ይሁን የጌታ ኢየሱስን ስም ሊቋቋም እንደማይችል ተማመኑ፡፡ ይህም በፍፁም እምነት "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቁም" ብሎ ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ሂድ፣ በቃ ተዉ፣ ታሰር ወዘተ በማለት ነው፡፡ የትኛውም ፍጥረት ቢሆን የእርሱን ኃይል ሊቋቋም የሚችል የለም፡፡ ችግር የሚገጥማችሁ ግን እነዚህን ቃላት በፍፁም እምነት ካልተናገራችሁ፣ ያዘዛችሁት የእርሱ ፈቃድ ካልሆነና በስሙ ኃይል ካላመናችሁ ብቻ ነው፡፡ ማወቅ ያለባችሁ በጣም አስፈላጊው ነገር በመጀመሪያ ዳግም መወለድ እንዳለባችሁና ከእርሱ ጋር ቤተሰባዊ መቀራረብ ያላችሁ መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ስሙን ለመጠቀም ልዩ መብት አላችሁ፡፡*

*ይህንን ነጥብ ግልፅ ለማድረግ ከዚህ በፊት ያወራሁላችሁን አንድ ታሪክ ደግሜ ላውራላችሁ፡፡ አዲስ ዳግም የተወለደ አንድ ሰው ከክርስቲያን ጓደኛው ጋር በመሆን በተራራ ላይ በእግር እየተጓዙ እያለ በድንገት አንድ ሴት ድብ እየጮኸች በፊታቸው መጣች፡፡ እነርሱ ያላዩት ልጇ ለካ በሳሩ ላይ ነበር፡፡ አዲስ ዳግም የተወለደውም ክርስቲያን ነገሩ ምን እንደሆነ እንኳን በደንብ ሳይረዳ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቁሚ" አላት፡፡ ድቧም የምታደርገውን አቁማ፣ ወደ ጎን መንገዷን ቀይራ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስን አዳኝ አድርጎ የተቀበለው በቅርብ ነው፡፡ ነገር ግን ያ ድቧን ለማቆም ሥልጣን እንዲኖረው ለማድረግ በቂ ነበር፡፡ ምናልባት ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጥረታት (ET) ቢያጋጥማችሁ አንድ የገጠመኝን ደግሞም ብዙ ጊዜ የነገርኳችሁን ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ በምሽት ውጪ ቁጭ ብዬ እያለሁ ከእኛ ቤት ብዙም ሳይርቅ አንድ ተጓዥ አይሮፕላን በዛፎቹ ላይ አየሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ምንም ሳላስብ "ከክፉ አድነን" አልኩኝ፡፡ እናም በዛው ቅፅበት ፍፁም ጠፉ፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ እኔን ተጠቅሞ የተናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ በዛን ጊዜ ተናገርኩት ምንም ሳላስበው ነው፡፡*

*በዮሐንስ 15፥ 7 ላይ እንዲህ ተፅፏል፡፡ "<u>በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል</u>፡፡"*

*እንዲሁም በማቴዎስ 17 ፡20 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡፡ "<u>እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፣ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም</u>።" ማቴዎስ 17፡20*

"ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ፣ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፡፡" ማቴዎስ 21፡21

የተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ ፍፁም በሆነ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ሲነገራቸው እንደሚበረከኩ ጌታ በግልፅና በትክክል የተናገረበት ሌላ ቦታ የለም፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ገደብ አበጅቼ "አዎ ዛፍ ልትረግሙና ሊደርቅ ይችላል፣ ስለ ሱናሜ ግን አላውቅም ልላችሁ አልችልም፡፡" ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፡፡ ቀይ ባህርን ከፍሎ እስራኤላውያኖችን ከሞት ካሻገራቸው፣ በአንፃሩ ደግሞ ባህሩን ወደ ቦታው መልሶ ጠላቶቻቸውን ሁሉ ካጠፋ፣ ሱናሜንም ለማጥፋት ፈቃዱ ከሆነ ያደርገዋል፡፡ የእርሱን ፈቃድ ለማወቅ ደግሞ ከጌታ ጋር ወዳጅ ከሆናችሁ ፈቃዱን ለመለየት ማስተዋሉ ይኖራችኋል፡፡ እንደ ፈቃዱ ብትለምኑ ደግሞ እርሱ ያደርገዋል፡፡

እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ሉቃስ 10፡19

*ቤተሰቦች ያለሁት እየገነባኋችሁ ነው፡፡ ምክንያቱም እዚህ የምትቀሩ አነዚህ ዘግናኝ ፍጥረታት እናንተን ኢላማ እንዳያደርጉ ለማስቆም የስሙ ኃይል ያስፈልጋችኋል፡፡ አሁን ምን እየጠበቃችሁ እንደሆነ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡ በመጀመሪያ ግን ይህንን አጥብቄ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ በጎ አድራጊ የሚባል ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሚመጡ ፍጥረታት የሉም (ET)፡፡ በፍፁም አንዳቸውም በጎ ወይም መልካም አይደሉም፡፡* ሰይጣን ከሦስተኛው ሰማይ ሲጣል አንድ ሦስተኛውን መላዕክት ከእርሱ ጋር ይዞ እንደወጣ የሚታመን ነገር አለ፡፡

በራዕይ መፅሐፍ ምዕራፍ 12 እንዲህ ተፅፏል "ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው።"(ራዕይ 12፡3-4)

እንዲሁም በቁጥር ሰባት "በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፡፡ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፡- አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም። ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።"(ራዕይ 12፡7-12)

*ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሚመጡ ፍጥረታት (ETs) ለሰው ልጅ የሰጡት ቴክኖሎጂዎች አንድና አንድ የሆነውን አጀንዳቸውን ለማስፈፀም እንደ ትሮይ ፈረስ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህም አጀንዳ በምድር የሚኖር ማንኛውም ሰው ሰይጣንን እንዲያመልክ፣ እንዲሁም ሰው የሚባለው ፍጡር ሁሉ ወንድ፣ ሴት፣ ህፃን ሳይባል ሁሉንም ጎትተው ወደ ገሃነም ከእነርሱ ጋር ለመውሰድ ነው፡፡*

*አሁን ደግሞ ስለ ሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነገረውን እንመልከት፡፡ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ ከፈጠረው ፍጥረታት ደግሞ ሉሲፈር የሚባል መልአክ ነበር፡፡ ይህ መልአክ ከወደቀ በኋላ ግን ስሙ ሰይጣን ተብሏል፡፡ ይህም መልአክ ወደቆ ሲጣል ከመላዕክቶች አንድ ሶስተኛውን ይዞ ነው የተጣለው፡፡*

"በበታችህም ብል ተነጥፎአል፥ ትልም መደረቢያህ ሆኖአል ብለው ይመልሱልሃል።አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!አንተን በልብህ። ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመስላለሁ አልህ።" (ኢሳያስ 14፡11-14)

"እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።" 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4

"ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።" (ሉቃስ 10፡17-20)

*እንዲሁም* "በተኲላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።" (*መዝሙር 91፡13)*

*እናም እነዚህ ድንገት የሚገለጡ የወደቁ መላዕክቶች/aliens/ ከቃሉ እውነት ጋር እንዴት እንደሚያያዙ፣ ይህ ሁሉ እንዴት ሊሰራ እንደሚችል እንዲገባኝ እየታገልኩ ነበር፡፡ በተለይም ባሳለፍናቸው ጊዜና ወቅቶች አንዳንድ ስለወደፊቱ የተነገሩ ትንቢቶች በሚደንቅ ሁኔታ መፈፀማቸውን እያሰላሰልኩ እያለሁ የኔ ድንቅ ኢየሱስ በምህረቱ ሐሳቤን አቋርጦ ወደ እኔ መጣ፡፡ እርሱ እንዴት መልካም ነው!*

*ኢየሱስም እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ. . ." ውዴ ግራ እንደገባሽ አውቃለሁ፡፡ በመጀመሪያ ሊገባሽ የሚያስፈልገው በቃሉ የተገለጡ ምልክቶች በብዙ አይነት የስልጣኔ ደረጃዎች፣ በብዙ አይነት የጊዜ ደረጃዎች፣ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሯቸው እንደሚችልና ራሳቸውን ለመድገም እንደሚችሉ ነው፡፡ ለምሳሌ በታሪክ ውስጥ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህም ኔሮን፣ ካሊጉላ፣ ሂትለርንና ሌሎችንም መውሰድ ትችያለሽ፡፡ እነዚህ ሁሉ የክርስቶስ ተቃዋሚ ተብለው ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነደዚህ እያልኩ ብዙ ልዘረዝር እችላለሁ፡፡ ነገር ግን መልዕክቱን ረዥምን የማይቻል ከማድረግ ይልቅ በርዕሱ ላይ እናተኩር፡፡*

"የወደቁ መላዕክት/*demon aliens/* ወደ ምድር እንደሚጣሉና ተገልጠው ሰማዩን እንደሚሞሉት መገንዘብሽ ትክክል ነው፡፡ ደግሞም ብዙ አጋጣሚዎች ተከስተው እንደነበረና ክስተቱም እየቀጠለ መሆኑም እውነት ነው፡፡ መንግስታት ከእነርሱ ጋር ስምምነት ገብተዋል፡፡ የገቡትም ስምምነት የወደቁ መላዕክቱ ሰዎችን ጠልፈው ከምድር በመውሰድ ሰዎችን የሚመስልና አጋንንቶች ሊኖሩበት የሚችሉበትን ሰውነት ለመፍጠር የጀመሩትን ምርምር እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ነው፡፡

(ክሌር)፡- ነገር ግን በቅርቡ እንደሰማሁት ፕሬዚዳንት ትራምፕ ግሬይ ኤሊየንስ ከሚባሉት ጋር ስምምነቱን አላደሰም፡፡ ከዚህም የተነሳ ከእኛ ሶላር ሲስተም (*solar system*) ወይም ከምድር ክልል በአጃቢ እንዲወጡ እየተደረጉ ነው፡፡

ከምድር በታች በሚገኙ ከተሞች የነበሩ የምድር መሸሎኪያዎች እንዲጋዩ በተደረጉ ጊዜ እንኳን እነዚህ ግሬይ (*gray*) የሚባሉት ፍጥረታት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እጅግ በብዛት ይገኙ ነበር፡፡

ኢየሱስም . . ."ዋናው ቁም ነገር በመጀመሪያ ደረጃ ሰይጣን ለስልጣን፣ ከበላይ ሆኖ ለመግዛትና ለመመለክ ከፍተኛ ጉጉት አለው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የማይረካ ቅናት በሰው ልጆች ላይ ስላለው ሰዎችንና ምድርን ለማጥፋት ከፍተኛ ፍላጎት አለው፡፡ ለዚህ ነው ጥላቻው እጅግ የጋለው፡፡

"ሰዎችን የሚጠላው ደግሞ በእኛ ማለትም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በመወደዳቸው ነው፡፡ እንዲሁም ምድርን የሚጠላት በእኛ ውብና ማራኪ ተደርጋ ለሰው ልጆች ስለተሰራች ነው፡፡ እኛን መንካት አይችልም፡፡ ነገር ግን እኛ የፈጠርነውንና የወደድነውን በመጉዳት በተዘዋዋሪ እኛንም ይጎዳል፡፡

"ስለዚህ የሰይጣን አጀንዳ ሁለት ገፅታ ያለው ነው፡፡ በአንድ በኩል ሰዎች እንዲያመልኩት ማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎችንና ምድርን ማጥፋት ነው፡፡ ስለዚህም ለሰዎች እጅግ የበላይ የሆነ ቴክኖሎጂ ቢሰጥ፣ ይህም ከፍተኛ የሆኑ መላዕክቶች ብቻ የሚያውቁት ሲሆን፣ በዚህም ራሱን አምላክ አድርጎ በማቅረብ አምልኮን ይቀበላል፡፡ አንቺ መልካም የሚባል ከከባቢ አየር ውጪ የሚመጣ ፍጡር( *extra-terrestrial)* ወይም ኤሊየን (*alien*) የለም ብለሽ የተናገርሽው ትክክል ነው፡፡ እነርሱ ሁሉም አጋንንቶች ሲሆኑ ለራሳቸው የተለያየ አይነት ሰውነት የፈጠሩ ናቸው፡፡ ይህም የምድር የሆነውን፣ እኛ ፈጥረን ከአብ ልብ ውስጥ መንፈስ የሰጠነውን ለመበዝበዝ ነው፡፡ እናም መልካምና ደግ ነን በማለት ሊያሳምኗችሁ ይሞክራሉ ደግሞም ይህንን ተቀብለው የሚያምኑ ይኖራሉ፡፡ መልካም ፖሊስ እና መጥፎ ፓሊስ በመባል የሚገለፀውን አባባል ታውቃላችሁ፡፡ ሁለት ፖሊሶች አንደኛው ጥሩና አዛኝ የሆነ ሌላኛው ደግሞ ንቁና ለስራው የተሰጠ ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ፖሊሶች ናቸው፡፡ እነዚህም የወደቁ መላዕክትና አጋንንቶች በጭንቅላታችሁ እነደዚህ ሊጫወቱባችሁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም "እነዚህ መልካሞቹ ናቸው፣ እነዚያ ግን መጥፎዎቹ ናቸው፡፡ አ! ሌላው ደግሞ መጣ በእውነት መልካም የሆነና ሁሉንም ነገር የሚያሳርፍ" ትላላችሁ፡፡ አይደለም፣ በፍፁም እንደዚያ አይደለም፡፡ ይህ ማታለያ ነው፡፡ ምንም የማይዛነፍ ማታለያ ነው፡፡ ሁሉም አንድ ቡድን ናቸው፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡፡ <u>"ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።</u>" (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡3-4)

በዚህ ክፍል የቆሮንቶስን ሰዎች ከመንገድ እየወጡ ስለሆነ እየገሰፃቸው ነው፡፡ በቁጥር 12 ላይ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡፡"<u> ነገር ግን በዚያ በሚመኩበት እንደ እኛ ሆነው ሊገኙ፥ ምክንያትን ከሚፈልጉቱ ምክንያትን እቆርጥ ዘንድ አሁን የማደርገውን ከዚህ ወዲህ ደግሞ አደርጋለሁ። እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።"</u>(2ኛ ቆሮንቶስ 11፡12-15)

"እነዚህ ፍጡሮች እኛ የፈጠርነውን በመወሰድ ኢጋንንት በዛ ውስጥ እንዲኖሩበት ለማድረግ እንደገና ሰሩት፡፡ ይህ ፊደሬሽን አፍ ላይት ወዘተ . . . የሚባሉት በጣም ብልህ የሆኑ የወደቁ መላዕክቶች ሲሆኑ ሌሎቹ አካል የለበሱት ኢጋንንቶች ደግሞ  እንደ ሰይጣን መንግስት አደረጃጀት በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፡፡ ፕሌዲያንስ *(Pleiadeans)*፣ ቬኑሲያንስ *(Venusians)* ፣ ነጭና ረጃጅሞች *(Tall whites )*፣ ተዳቅለው እንደ ሰው ሆነው የሚታዩ፣ እንዲሁም ግራጫዎቹ (*grays*) ሁሉም ከኢጋንንቱ አለም የመጡ የመናፍስት አካላት ሲሆኑ በእግዚአብሔር አብ ላይ አምፀው ከመንግስተ ሰማይ የተባረሩ ናቸው፡፡

"እነዚህ ከሦስተኛው ሰማይ ቀድሞ የተባረሩ ሲሆኑ አሁን ደግሞ በቅርቡ ከሁለተኛው ሰማይ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ተባረው ወደ ምድር ይጣላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ነው እጅግ ብዙ በሆነ መጠን መታየት የሚጀምሩት፡፡ ክብ የሆነውና ሌሎች ቅርፅ ያላቸው የአየር ላይ መጓጓዣዎቻቸው ሰማዩን ሁሉ ይሞሉታል፡፡ በዚያን ጊዜም ሞኞችን ወደ መጓጓዣዎቻቸው እንዲገቡ ይጋብዟቸዋል፡፡"

(ክሌር)፡- እዚህጋ ህዝቅኤል ከአመታት በፊት በህልሙ ያየውን አንድ ነገር ልንገራችሁ፡፡ ባለቤቴ ህዝቅኤል የአየር መጓጓዛዎችን ስለሚወድ በህልሙ ወደ አንድ መጓጓዣ ለመግባት እየተጓዘ እያለ ጠባቂ መልአኩ "አይሆንም ወደዛ እንዳትገባ" በማለት ከለከለው፡፡ ስለዚህም ሳይገባ ተመለሰ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ህዝቤ ከእነዚህ ኢጋንንቶች ጋር ምንም የምታደርጉት ጉዳይ የላችሁም፡፡ እነርሱ እውቀታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መላዕክቶች ስለሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ፍላጎታቸው እናንተ እንድትጠፉ ነው፡፡ ስለዚህም ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር አይኑራችሁ፡፡ እደግመዋለሁ፣ ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር አይኑራችሁ፡፡ ከአጠገባችሁ እንዲሄዱ በእኔ ሥም እዘዟቸው፡፡ ይህ ደግሞ እነርሱ ማን እንደሆኑ ለማወቅ የምትፈልጉትን ግልፅ የሚያደርግና ፍጥረታቸው በትክክል ምን እንደሆነ የሚያሳያችሁ ይሆናል፡፡

"ብዙዎች እነዚህ እጅግ የተዋቡ ፍጥረታት ከላይ የመጡ የበላይ አካላት፣ በሞራል ደረጃም የበለጠ ስነ ምግባር ያላቸው ይመስላቸዋል፡፡ እውነቱ ግን ፍጡራኑ ያመፁ መላዕክቶች ሲሆኑ ወቅቱ ሲደርስ በሁለተኛው ሰማይ ላይ እንዳይኖሩ የተከለከሉና ወደ ምድር የሚጣሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ለሚሊኒየም ያህል አይምሮንና ኢነርጂን በመጠቀም ታላቅ ምኞት ያላቸውን ሰዎች በማታለል፣ በማግባባት፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎችን በመስጠት፣ የሰዎችን አመኔታና ድጋፍ አግኝተን ይረዱናል በማለት ተስፋ ሲያደርጉ ነበር፡፡ የዚህ ሁሉ የሰይጣን ልፋት በእግዚአብሔር መልክና ሃምሳል የተፈጠረውን የሰው ልጅ አምልኮ ለማግኘትና ሲመኝ የነበረውን ከእግዚአብሔር የበለጠ ክብር ለማግኘት ነው፡፡
በ2ኛው ተሰሎንቄ ጳውሎስ የሚናገረው ስለዚህ ነው፡፡ "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

*(ክሌር)፡- እዚህ ላይ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ እኔ እንደማምነው ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ያዳነኝ አንድ ነገር ቢኖር እውነትን ብቻ ፈላጊ በመሆኔ ነው፡፡ ያገኘሁት ፍፁም እውነት መሆኑን እስከማወቅ ድረስ በምንም ነገር መረጋጋት አልቻልኩም ነበር፡፡ እናም በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ እኔ የማምነውን የአዲሱን  ዘመን እንቅስቃሴ አማልክትን እንዲሁም*

*አንድ፣ እውነተኛና ህያው የሆነውን አምላክ ልዩነት በፀጋው ሲገልፅልኝ በውስጥ ማንነቴ በዘመኔ ሁሉ ስፈልገው የነበረው እውነት ይህ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ በተጨማሪም እርሱን በመከተሌ ያገኙሁት ፍሬ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ መራኝ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም አልሜ የማላውቀው መከናወን ደግሞ በህይወቴ ተከሰተ፡፡ በእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ውስጥ እየኖራችሁ መሆኑን እንደማወቅ ደስ የሚያሰኝ ስሜት የለም፡፡*

*ኢየሱስም ቀጠለ . . ." በደመናት ከሰማያት ስመጣ ሲያዩኝ፣ ይህ ማታለል ይሰበራል፡፡ እናም እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን እውነቱ እንዳለ ተገልጦ ያዩታል፡፡ እኔን የማያውቁ እርሱን ያመልኩታል፡፡ በዚህም ለስልጣን ያለው ጥም ይረካል፡፡ ይህም የሚሆነው እኔ መጥቼ ለአንድ ሺህ አመት ወደ ተዘጋጀለት እስኪጣል ድረስ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋችኋል፣* "<u>ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል</u>።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

*"ህዝቤ እነዚህ አዲስ ቴክኖሎጂዎች ማለትም ተሴላ(Tesla) ፣ ሜድ ቤድስ (Med Beds) ፣ ነፃ ኤነርጂ (free energy)፣ 5ጂ ንቃተ ህሊና (5G consciousness) የሚባሉት ሁሉ እኔ በፈጠርኳቸው የሥነ ፍጥረት (universe) ክፍል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ እናም እነዚህ መላዕክቶች እንደዚህ አይነቱ ነገር ስለሚገባቸው ይህ የሆነው ከእነርሱ ከፍተኛ ንቃተ ህሊና ክፍል አንዱ ብቻ እንደሆነ፣ ይህም ደግሞ አምላክ ከመሆናቸው ጋር የተገናኘ መሆኑንና ከእናንተ የበለጠ ንቃተ ህሊና እንዳላቸው ለማሳመን እየሞከሩ ነው፡፡ እነዚህ የወደቁ መላዕክቶች እኔ ከፈጠርኩት የሥነ ፍጥረት ክፍል አባል ናቸው፡፡ እናም እንዴት እንደሚሰራ ለማየት ችሎታው ስላላቸው ያንን በማንቀሳቀስ አሰቃቂ ለሆነው ህግወጥ ውጤት ተጠቀሙበት፡፡ እነዚህንም ቴክኖሎጂዎች እንደ ትሮይ ፈረስ በማድረግ ነፍሶች እንዲያምኗቸው ለማድረግ በኃይልና በታምራት፣ እንዲሁም በምልክቶች፣ ከተቻለ የተመረጡትን እንኳን ለማሳት ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ እንደሚሆን ደግሞ በቃሉ ተገልጿል፡፡ ኢያልኩ ያለሁት ፈጠራዎቹ በራሳቸው ገለልተኛና እንዳውም ጥሩ ናቸው፡፡ ቢሆንም ግን እነዚህን ቴክኖሎጊዎች ያመጡላችሁ አካላት ኤጋንንቶችና የወደቁ መላእክቶች ናቸው፡፡"*

*(ክሌር)፡- ጌታ ጋላክቲክ ፈደሬሽን ኦፍ ላይት (Galactic Federation of Light) ምንድነው?*

ኢየሱስም . . . " ይህ ያገኘሽው አባባል እነርሱ "አዲስ" ብለው ከሚጠሩት ከመንፈሳዊ እንቅስቃሴ አባባሎች አንዱ ነው፡፡ ሰይጣን ከመውደቁ በፊት ሉሲፈር፣ የብርሃን ተሸካሚ፣ ይባል እንደነበረ ይህንን አስታውሺ፡፡ ይህ አሁን የምናገረው በቃሉ የተፃፈውን ትልቁን መሳት ተብሎ የተጠቀሰውን ነው፡፡"

"<u>ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል</u>።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

ኢየሱስም . . . የኔ ፍቅር ይህ ግልፅ የሆነ ስዕል እንደሰጠሽ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በዚህ ነገር እንዴት ብዙ እንደታገልሽ አውቃለሁ፡፡ አሁንም ግን የሚያሳሳት መስሎ ይታይሻል፡፡ አሁን ደግሞ ሁሉም ኸርትድዌለርስ እንዲገባቸው አድርጌ ልግለፀው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ድንቅ እንደሆነ ልንገራችሁ፡፡ ነገር ግን ችግሩ ያለው ቴክኖሎጂውን የሰጧችሁ አካላት በአይምሮአቸው የሚያስቡት እናንተን ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ ከመኖሪያ ሥፍራቸው ተፈናቅለው ወደ ምድር የመጡት ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው ነገር አልቆባቸው አይደለም፡፡ እነርሱ ወደ ምድር የመጡት መላዕክቶቼ ከሁለተኛው ሰማይ አስገድደው በማባረር ወደ ምድር ጥለዋቸው ነው፡፡ የዚህም ምክንያት እኔ መጥቼ ሁሉን ነገር ከማስተካከሌ በፊት መካሄድ ያለበት ትልቁ የማንፃት ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡ ሁሉንም አንድ ላይ ሰብስቤ ወደ እሳቱ ባህር እጥላቸኋለሁ፡፡ እና ደግሞ መንግስት በትከሻዎቼ እንጂ እነሱ እንደሚሉት በጋላክቲክ ፌደሬሽን ኦፍ ላት *(Galactic Federation of Light)* አይደለም፡፡ ይህ የሰይጣንን አሰቃቂ አጀንዳዎች ለመሸፈን ብቻ የቀረበ ነው፡፡ *በዚህ መልኩ የቀረበው ለምሑራኖች ሲሆን እነርሱ ሃይማኖትን ጠልቀው ያልቀመሱና ሃይማኖትን ቀላልና የተራ ሰዎች አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው፡፡* ስለዚህም ምሑራኖቹ *ከማይታየው አለም የሚፈልጉት ጥበብን ስለሆነ ዝንባሌያቸው ወደ መንፈሳዊው አለም ሚስጥራት ነው፡፡"*

*(ክሌር)፡- የተወደዳችሁ እስካሁን ካቀረብኩላችሁ መልዕክቶች ሁሉ እንደዚህ የከበደኝ የለም፡፡ የማስጠነቅቃችሁ በሰው ልጆች ላይ ሁሉ ሊወድቅ ያለው ትልቁ መሳት እየመጣ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማታለል በ60ዎቹ የአኳርስ ዘመን በመባል፣ አሁን በዚህ ዘመን ደግሞ ትልቁ መነቃቃት ወይም ዘ ግሬት አዋክኒንግ (The Great Awakening) ፣ የ5D አለም፣ በሚል በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ መሰረቱን ጥሏል፡፡ አሁን የደረሰበት ደረጃ ግን በሙሉ አቋሙ አካል ለብሶ የምድሪቱን ሰዎች ለማጥመድ ተዘጋጅቷል፡፡ ውዶች አይኖቻቸው እንዲከፈትና ነፃ እንዲወጡ ፀልዩላቸው፡፡ እንዲሁም ፈተናው ሲመጣ ፀንታችሁ እንድትቆሙ ለራሳችሁ ፀልዩ፡፡*

"*መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፡፡*" (1ኛ ጢሞቲዎስ 4፡1-2)

እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና ( በዘመናችን እንደ ሜታፊዚክስ ትምህርት) ፣ እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና *(በዘመናችን እስፒሪቹአል ኢንተሌክቹዋሊዝም እንደሚባለው)* በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።(ቆላስያስ 2፡8)

ጌታ ኢየሱስም . . . "በሌላ አነጋገር 'እኛ የበራልን ክርስቶስን በሚመስሉ አካላት፣ ይኸውም ከላይ በወረዱ ጌቶች ወይም አለቆች ነው፡፡' በሚሉት አትማረኩ፡፡ እነዚህም በእኔ አማካኝነት ደህንነት አያስፈልግም የሚሉ ናቸው፡፡"
"ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" (ራዕይ 12፡9)

(ክሌር)፡- ይህ ክፍል በሌላ አነጋገር ሲገለፅ እርሱና መላዕክቶቹ ከ2ኛ ሰማይ እንዲወርዱ የተደረጉት በኃይል ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ ይህ የተከናወነው ሰይጣን ከሶስተኛው ሰማይ ሲጣል ነው ብላችሁ ትሟገቱኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ማስታወስ ያለባችሁ አንድ የእግዚአብሔር ቃል በተለያየ ጊዜ ለሚከሰቱ እውነቶች ሁሉ የሚሰራ ነው፡፡

"በዚያን ጊዜም ማንም እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ፥ ወይም። እነሆ፥ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ። እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኋችሁ። (ማርቆስ 13፡21-23)

(ክሌር)፡- የኔ ውዶች ከሰው አቅም በላይ የሆኑ ሰዎች እንደገረሙና እንደደነቁ የሚያደርጉ በጣም አስደናቂ ነገሮች ለዕታ ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ኃይል ስላላቸው ያጠመዳሉ፣ ያሰምጣሉ ሰዎችም በእነርሱ ይረታሉ፡፡ ይህንን ብቻ አስታውሱ እነዚህ ነገሮች በተለያዩ ወርድና ስፋት (*interdimensional)* ማንነት ባላቸው አካላት ኢነርጂዎችን በማንቅሳቀስ ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ልክ ባለ ሦስት ወርድና ስፋት ያላቸው ስዕሎችን በአየር ላይ ማንጠልጠል እንደሚቻል ማለት ነው፡፡ ይህንን ማጭበርበር ሊለዩ የሚችሉት ከፍ ያለ ወይም የሰላ መንፈስን የመለየት ችሎታ ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ሙሽሮቼ አፍቅራችኋለሁ፡፡ ቀኑ እየመጣ ነው፣ በእውነትም እየመጣ ነው፡፡ መመልከታችሁን ቀጥሉ፡፡ አሁን እንኳን ቢሆን ወደ ጥፋት ከገባችሁበት ወጥታችሁ ወደ መጀመሪያ ፍቅራችሁ ተመለሱ፡፡ የተወደዳችሁ እየጠበቅኋችሁ ስለሆነ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡ ከእኔ ጋር የቀረበ ወዳጅነት ሲኖራችሁ ሌላ አምላክ እንድታመልኩ ከሚመጣባችሁ ፈተና ታመልጣላችሁ፡፡ አንድ ሆነው ከሚሰሩ፣ ነገር ግን ደግሞ በሶስትነት ከተገለጡ ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ እኔ የእናንተን መልክ ይዤ፣ እንደ እናንተ ተወስኜ፣ ሰውነቴን ለስቃይ አሳልፌ ሰጥቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ እናንተን የእኔ ለማድረግ ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ መርሳት የሌለባችሁ በፍፁም ንፅህና በዘላለማዊ እጆቼ በጥንቃቄ እንደማቅፋችሁና ፍቅሬን በፍፁም እንደማታጡት ነው፡፡ ለመገኘቴ አይኖቻችሁን ከፍታችሁ እዩ፡፡ ይህ ፍቅር ደግሞ ገደብ የሌለው ነው፡፡ በክንዶቼ እረፉ፣ በቃሎቼ ላይ እርፉ፣ ቃል በገባሁላችሁ ላይ እረፉ፡፡ እናም ደግሞ በእኔ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ልብ፣ አንድ አይምሮና አንድ አካል እንደሆንን ሙሉ መተማመን ይኑራችሁ፡፡"

## እናንተ የወንድማችሁ ጠባቂዎች ናችሁ - ማርች 21 ቀን 2021 ዓ.ም

### You are your brother’s keepers, March 21, 2021

የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ ጌታ ይባርካችሁ፡፡ በዚህ ሳምንት ከግንቦት አንድ በፊት ክፉ በእኛ ሊፈፅመው ያቀደው ሥራ ስለነበር ከሌላ ጊዜ የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን፡፡ በዚህ ያለው ህብረተሰብ ጌታን ለመከተልና አንዱ ሌላውን ለማገልገል በጥልቅ ራሱን የሰጠ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ላይ መሆናችንና የእያንዳንዳችን የግል አገልግሎት ሲያድግ ማየት ለእኛ ደስታችን ነው፡፡ ቢሆንም ግን ጠላታችን ሰይጣን ይህንን በማየቱ ደስተኛ አልሆነም፡፡ ለምን? ምክንያቱም ፍፁም ስምምነት ስላለ፣ አንዱ ሌላውን ስለሚያገለግል፣ በየዕለቱ ከአምላካችን ጋርና ከእርሱ እውነት ጋር ስለተያያዝንና በአለም ላይ ባሉ ነፍሶች ላይ ለውጥ እያመጣን ስለሆነ ነው፡፡

እኛ እያደግን፣ መንፈስ ቅዱስ እያሰፋንና ትምህርቶቹን ለአለም ሩቅ አካባቢዎች ሁሉ እንድናደርስ እየፈለገ ነው፡፡ ይህ እንዴት ቆንጆ ነገር ነው! ነገር ግን ከዚህ መስፋፋት ጋር ደግሞ የጠላት ጥቃት አለ፡፡ ምክንያቱም እርሱ የሚፈልገው ስለራሳችን ብቻ እያሰብን እርስ በርሳችን እየተጣላን ተሰብስበን እንድንቀመጥ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደተናገርኩት እኛ የተመረጥነው በእግዚአብሔር ተሞልተን በመፍሰስ ሌላውን እንድናገለግል ነው፡፡ የተጠራነው ለልዩ አገልግሎት ቢሆን

ወይም ለተመረጡት ወንጌልን መመስከር ቢሆን አገልግሎታችን ከጌታ ተቀብለን ለሌሎች የምንሰጥ የክብር እቃዎች ነን፡፡

ሰይጣን አንድን አገልግሎት ለማጥፋት ሲፈልግ የሚጠቀመው ከውስጥ ባሉት ሰዎች ነው፡፡ ይህም በመሪዎች ላይ ጥላን በመጣልና ፍርድን በማስቀመጥ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ እየሰራ ባለው መሪ ላይ በእያንዳንዱ በሚያደርገው እርምጃ ኩራት ዘሎ እንዲይዘው ይቀሰቅሳል፡፡ መራራነትንና ፍርድን በመሪዎች ላይ ማነሳሳት ከቻለ እግዚአብሔር ለመሪዎቹ የገባላቸውን ቃል ለማበላሸት ልዩ የሆነ ጥሩ አጋጣሚ አግኝቷል ማለት ነው፡፡

ጠላት እያንዳንዳችንን የሚያነበን እንደ መፅሐፍ ነው፡፡ ምርጫችን ምን እንደሆነና በምን መንገድ እንደምናስብ ያውቃል፡፡ ሰነፍ ስንሆንና በራሳችን መንገድ ለመስራት ስንፈልግም ያውቃል፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲፈፅም ራዕይ አድርጎ በሰጠው መሪ ላይ ትችትን ያነሳሳል፡፡ ለመስራት የተጠየቅነውን አንድን ሥራ ለምን እንዳልሰራን ለራሳችን ይቅርታ ለማድረግ የበዛ ጫና አለ ብሎ ማነሳሳትን ይወዳል፡፡  እኔ ጫና እንዳላበዛባችሁ ጥንቃቄ ለማድረግ እጅግ እጥራለሁ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዳችሁ ጫና ሊፈጥርባችሁ የሚችል የራሳችሁ ትልቅ ፍላጎት አለ፡፡ ሰይጣን ደግሞ ይህ እንዴት እንደሚሰራ ስለሚያውቅ ያንን ያዘጋጃል፡፡  አሁን እያወራሁት ያለሁት ለእኛ ህብረተሰብ አባላት ነው፡፡ እነርሱ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለመስራት ስለሚፈልጉ አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን በሥራ ጫና ውስጥ ይከታሉ፡፡

እኔ በእኔ ፍጥነት ደረጃ የማይሄድና መካከለኛ የሆነ ባል በማግባቴ እጅግ እድለኛ ነኝ ፡፡ ምክንያቱም በአካባቢ ያሉትን ሰዎች ድካም ተገንዝቤ ቀስ ማለት እንድችል ረድቶኛልና ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ማንም የህብረተሰቡ አባል ጫናን ከሚፈጥሩና የጊዜ ተመንን ከሚጠቀሙ አጋንንቶች ለመጠበቅ እሞክራለሁ፡፡ ነገር ግን ቅድም እንደገለፅኩት አንዳንዶቻችን ራሳችንን ማስጨነቅ ልማድ አድርገነዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ቀስ በሉ ብንባልም እንደሚገባው መጠን ቀስ ማለት አንችልም፡፡ ለእኔ አንዳንድ ጊዜ ቀስ ማለት በፍፁም ከባድ ነው፡፡ ጌታ ግን ቀስ የሚያስደርግበት መንገድ አለው፡፡ ሰይጣን ነገሮችን ማፍጠን በመካከላችን አለመስማማትንና መከፋፈልን ለማምጣት ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ በደንብ ገብቶታል፡፡ ስለዚህም ለእያንዳንዳችን እንዴት አለመስማማትን እንደሚያነሳሳ በጥንቃቄ ያቅዳል፡፡ ለአንዱ የጊዜ ተምን ነው፡፡ ለሌላው ደግሞ የራሱ ምርጫ ነው፡፡ ለብዙዎች ደግሞ ጊዜው ያለፈበት ስንፍና ሲሆን ይህም ሥራውን የበለጠ ጥረት በሚያስፈልገው በሌላ መንገድ መስራት አለመፈለግ ነው፡፡ እነዚህ ሌላ በጣም አስፈላጊ የሆነ ፕሮጀክትን ለመጨረስ ይጣደፋሉ፡፡ ስለዚህም የተሰጣቸውን መመሪያ በመተው በራሳቸው መንገድ ይሰሩታል፡፡ እኔ ይህንን በጌታ ላይ ፈፅሜዋለሁ፡፡ ጌታ ይቅር በለኝ፡፡

ይህ ምን ያመጣል? መሪነትን ይሸረሽራል፣ መሪዎችን ይንቃል፡፡ እናም ነገሮች መስራት በማይገባቸው መንገድ እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡ በተባሉት መንገድ ለምን እንዳልሰሩት ሲጠየቁ ደግሞ ያለ የሌለ ጥሩ ነው ብለው የሚያምኑባቸውን ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ መጀመሪያ ይህንን መስራት ነበረብኝ፣ ሥራውን ለመስራት የሚያስፈልገኝ ነገር የለኝም ነበር፣ በፊት በሌላ አይነት መስራት ጀምረነው ነበር ፣ እና አሁን ከመጀመሪያው ጀምሬ መስራት አለብኝ??? እነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ራዕዩን ለተቀበለው ሰው ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠት ስለሚቸገር ተስፋ ይቆርጣል፡፡ ደግሞም ጊዜ፣ ገንዘብና ሃብት ይባክናል፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶቻችን አጭር መንገዶችን መጠቀም እንፈልጋለን ወይም በእግዚአብሔር ተጠያቂ የሚሆነው ሰው ያቀረበውን እጅግ ጥሩ ነገር በመተው የራሳችንን ሐሳብ እንጨምራለን፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው የእርሱ ፍላጎት ሳይጠየቅ ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ አሉ የተለያዩ ነገሮችን እንዲያነቡና እንዲሰሙ አንድ ሰው ሲጠይቃቸው ፍፁም መማር የማይፈልጉና ቁጥር ሥፍር የሌላቸውን ምክንያቶችን በማሽጎድጎድ መንገድን የሚዘጉ፡፡ ስለዚህም መንገድን የሚዘጉ አጋንንቶችን እየተቃወምን እጅግ በከባዱ እየፀለይን ነበር፡፡ ምክንያቱም መንገድ የመዝጋት ነገር በብዛት ይካሄዳል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ነገሮች እንዳይከናወኑ ያዘገያል ደግሞም ያሰናክላል፡፡ ጌታ የሚፈልገው ደግሞ አንድ ልብና አንድ ሐሳብ ሆነን አንዳችን ለሌላችን እያካፈልን አንድ ሥፍራ ላይ እንድንቀመጥ ነው ፡፡ እኔ ደግሞ እዚህ ሥፍራ ተገኝቻለሁ፡፡

ይህንን አንድ ነገር ልበል፣ ጌታ ሆን ብሎ ነው በዚህ ምድር ላይ አንድ ሰው ብቻ አድርጎ ያላስቀመጠን፡፡ በዘፍጥረት መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ብሏል፡፡ በደብዳቤዎቹም የወንድሞችን ህብረት ጥላችሁ አትሂዱ ብሏል፡፡ እግዚአብሔር የስልጣን እርከኖችን የሚመሰርተው በህብረቱ ውስጥ ሰላምንና ስርአትን ለመጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ከውጪ ምንጭ ምንም አልቀበልም ካለና ግንኙነቱን ከውስጥ ከጌታ ጋር ብቻ የሚያደርግ ከሆነ፣ በራሱ ላይ አጥር በመስራት ጌታ ለህብረቱ ጥቅም እንዲውሉ የሰጠውን የፀጋ ስጦታዎች ሳይጠቀምበት ይቀራል፡፡ ነገር ግን ማድረግ ያለብን እግዚአብሔር በሰጠን ጥበብ ላይ መደገፍና እንዲሁም ሌሎችን በመስማት መነካት መቻል ነው፡፡

ስለዚህ በዛሬው ቀን  በህብረተሰቡ ውስጥ ትንሽ መስተካከል ያለበትን ነገር ለማስተካከልና ለማስቀጠል ስነሳ ያጋጠመኝ ነገር አንድ አባል አንድ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰባት አጫጭር የሰውነት ማንቀጥቀጥ (strokes) ደርሶበት ነው፡፡ እዚህጋ ስለዚህ ጉዳይ ትንሽ መግለጥ የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ ይህ ሰው ላለፉት ሁለት ሳምንታት ያህል ውጥረት የበዛበት ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከሁለት ሳምንት በፊት የመገናኛው መስመር ሽቦ ተበጥሶ ስለነበር የሚያስተላልፈው መልዕክት ለህብረተሰቡ በሰአቱ አልደረሰም ወይም በመካከል መቆራረጦች ነበሩ፡፡ ስለዚህም ከተራራው ህብረተሰብ ጋር አስፈላጊ የሆኑ የቃል ልውውጦች ካለማድረጉ የተነሳ ባይተዋርነት ተሰምቶት ነበር፡፡

የመገናኛው ሽቦ ከተበጠሰ በኋላ ቴክስት ሲያደርጉ ወይም ስልክ ሲደውሉ አገልግሎት የለም ወይም ኔትዎርክ ቢኖርም መጥፎና የተቆራረጠ ነበር፡፡ እናም በወቅቱ ተወያይተን መሰራት እንዳለበት ተነጋግረን ነበር፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች እስከዛሬ ሳይስተካከል ቀርቶ በዚህ ሰው ላይ ከባድ ጫና ፈጥሮበት ለዚህ ዳረገው፡፡

በዚህ ላይ ለመጨመር የምፈልገው በዚህ ተራራ ላይ ያሉ ሁሉ እጅግ የሚደንቁና ትክክል የሆነውን ለመስራት፣ እንዲሁም በዝርዝር ያወጡትን ሥራ ለመጨረስ እጅግ በብርቱ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን የጥድፊያውን ቁልፍ ተጭናችሁ ፍጠን ፍጠን በማለት የሚቀሰቅሰውን አጋንንት ከላካችሁ የሰይጣን ትንንሽ ዲያቢሎሶች ደግሞ መልካም ለመስራት የተነሳሳውን ሰው ከአቅም በላይ ሰርቶ በመድረቅ እሳት አቀጣጣይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በአንድ በኩል ሥራውን ለመስራት ኃላፊነት የተሰጠው ሰው በአንድ ነገር ከተናደደ የተናቀና ምንም ስፍራ እንዳልተሰጠው ይሰማዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እየተሰራ ያለው ፕሮጀክት እያለቀ ስለሆነ ከጀርባው አንድ አቀጣጣይ ያስፈልገዋል፡፡ ይህም ቢሆን ግን አንድ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥመን ሁሉን በሙተው ትኩረት ወደሚያስፈልገው ጉዳይ መሮጥ አለብን፡፡ ጌታ ከዚህ በላይ ምንም መናገር አልፈልግምና እባክህ አንተ ትቀጥላለህ?

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." ልጆቼ እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ ፍቅር ይታገሳል፣ ፍቅድ በጎነት ያደርጋል፣ ፍቅር ከራሳችን የበለጠ ለወንድሞቻችን ግድ እንዲለን ያደርገናል፡፡ ፍቅር በሚያስፈልገው ሁሉ ራሳችንን መስጠት ነው፡፡ ፍቅር ግትር አይደለም፡፡ ስለዚህም በዛ ሰው ፊት ያስቀመጥኩት ጉዳይ የትኛው እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በማወቅ ቅድሚያን ይሰጣል፡፡ ፍቅር ምክንያት አይሰጥም ወይም አያማርርም፡፡

"የኔ ውዶች በዚህ መጠለያ ውስጥ የተቀደሰውን ፈቃዴን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቻለሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን አስታውሱ ያላችሁት ገና ስልጠና ላይ ነው፡፡ የሚያስፈልገው የቅድስና ግብ ላይ ገና አልደረሳችሁም፡፡ ለወንድሞቻችሁ ወይም ለእህቶቻችሁ ወዲያው በሚያስፈልጋቸው ነገር ምላሽ በምትሰጡት ልክ ምን ያህል እንደምትወዷቸውና በእነርሱ በኩል እኔንም ምን ያህል እንደምትወዱኝ ያንፀባርቃል፡፡ አንድ ነፍስ እጅግ አስቸኳይ ነገር እንደሚያስፈልገው ተነግሯችሁ  ከእነርሱ ይልቅ የእናንተን ፍላጎት ካስቀደማችሁ ራስ ወዳዶችና የወንድማማች ፍቅር እንደሌላችሁ ያሳያል፡፡

"እርስ በርስ እንድትስማሙ እፈልጋለሁ፡፡ ሰምታችሁ ምላሽ መስጠት ብቻ ሳይሆን ያ ሰው የተጨነቀበትን ነገር ልክ እንደ እርሱ ተሰምቷችሁ ቅድሚያ ሰጥታችሁት የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ ነው፡፡ በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁ ገና እጅግ ራስ ወዳዶች ስለሆናችሁ በልባችሁ አታዳምጡም፡፡ የምታደምጡት ምክንያትያዊ በሆነ መልኩ ስለሆነ ምላሽ ለመስጠት ቅድሚያ የምትሰጡትም ደስ እንደሚላችሁ ነው፡፡"
ክሌር)፡- እናዘዛለሁ የምመደበው ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ ነው፡፡

ኢየሱስም . . . እንደዚህ ስታደርጉ የምትጎዱት እርዳታ ለማግኘት የሚሰቃየውን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ሁሉ ነው፡፡ በመጨረሻም የምትጎዱት ራሳችሁንና እኔንም ነው፡፡ አንድ ሰው ሲሰቃይ ሁሉም ይሰቃያል፡፡ የራሳችሁ የሆኑትን እንኳን መንከባከብ ካልተማራችሁ እንዴት አድርጌ ነው የውጪውን አለም እንድታገለግሉ የምጠቀምባችሁ፡፡

"እውነታው ሲታይ አንዳችሁ ከአንዳችሁ እንደ ጋብቻ በቃል ኪዳን ተሳስራችኋል፡፡ ይህም ቃል ደግሞ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ኃላፊነት እንዲኖራችሁ ያደርጋችኋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ከራሳችሁ የበለጠ ለሌላው ግድ እንዲላችሁና አስፈላጊ በሆነው በዛው ወቅት ቸርነት ማድረግና መታዘዝ ይገባችኋል፡፡ የተወደዳችሁ ሆይ ህይወታችሁን ለጓደኞቻችሁ ስጡ፡፡ ይኸውም ፍላጎታችሁን፣ የራሳችሁን ቅድሚያ፣ ለመስራት የምትመርጡት ፕሮጀክት፣ አንድን ነገር ለመስራት የምትገፋፉበትን መተውን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም የወንድማችሁ ጠባቂዎች ትሆናላችሁ፡፡

"አንድ ነገር ቢጠፋ ወይም ትክክል ባይሆን 'ይህ የእኔ ችግር አይደለም፣ እኔ በራሴ ሥራ ተጠምጃለሁ' ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ እናንተ ለመርዳት ምንም ጥረት የማታደርጉ፣ ከወንድማማች ፍቅርና ቸርነት የጎደላችሁ ናችሁ፡፡ እኔ ብሆን ምን አደርጋለሁ? የያዝኩትን የኔ የምለውን ልዩና አስፈላጊ ሥራ አቆምና የጠፋበትን ነገር አፋልገዋለሁ፡፡ ወይም ለማቃለል ችግር የሆነበትን ነገር እንዲያቃልል እረዳዋለሁ እንጂ በጭካኔ እያጉረመረምኩ 'ይህ የእኔ ችግር አይደለም፣ የጠፋበትን ሄዶ ራሱ ሊፈልግ ይገባል አልልም፡፡

"እኔ እንድትረዷቸው የላኳቸውን ነፍሶች ሳታከብሩ ስትቀሩ እኔን ታቆስሉኛላችሁ ለራሳችሁም ውድቀትን ታመጣላችሁ፡፡ በልባችሁ አድምጣችሁ እኔ እንደምፈልገው በአግባቡ መልስ ካልሰጣችሁ ለሐዘን ትዳርጉኛላችሁ፡፡

አንዳንዶቻችሁ ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ በደንብ ታውቁታላችሁ፡፡ እናንተ ወደ እርሻ ሄዶ እንዲሰራ አባቱ ሲልከው እሺ ብሎ በመሄድ የአባቱን ፈቃድ ሳይሆን እርሱ አጣዳፊ ብሎ ያሰበውን የሰራውን ልጅ ትመስላላችሁ፡፡

"በዚህ አመት ከሜይ (ከግንቦት) አንድ በፊት ጠላት ይህንን ህብረተሰብ ለመከፋፈልና ለመጣል እየረገማችሁና አጋንንቶችን እንደመደበ አውቃችኋል፡፡ ይህም የሆነው ይህንን ህብረተሰብ በልዩ መንገድ የሚጠላውን ሰይጣንን ለማስደሰት ነው፡፡ ማዘር ከሴር እንደነገረቻችሁ የዛሬ 20 አመት ልክ በዚህ ጊዜ ህዝቁልንና ከሴር ተለያተው እርሷ ብቻዋን በዚህ ተራራ ላይ ቆይታ ነበር፡፡ ያን ጊዜ የለየኋቸው አንድ ላይ በሰላም ከመኖራቸው በፊት ሁለቱም ሊወጡት የማይችሉት ከባድ ጉድለት ነበረባቸውና ነው፡፡ እናም እኔ የጠራኋችሁ ደግሞ አንድ ላይ በሰላም እንድትኖሩ ነው፡፡ ከተለያዩ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ራሳቸውን በግልፅ ማየት ሲጀምሩና ንስሐ ሲገቡ እንደገና አንድ ላይ አመጣኋቸው፡፡ ማናችሁንም ቢሆን ከህብረተሰቡ ለመለየት ፍላጎቴ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳችሁ ከአንዳችሁ በመስመር እንድትገቡ ለማድረግ ካስፈለገ አደርገዋለሁ፡፡ ከዚህ ቀደምም ከዚህ ህብረተሰብ ለቀው በሄዱት ነፍሶች ይህንን መረዳት ትችላላችሁ፡፡ አንድ ህብረተሰብ ከዚህ አይነት ወንድማማች ፍቅርና ቸርነት ውጪ ሊኖርና ሊቀጥል አይችልም፡፡ በአለም ከሚመጣው ከፈተና አስመልጥሻለሁ ብዬ ቃል የገባሁላት ቤተክርስቲያን ፊላደልፊ ናት፡፡ ለምን? ምክንያቱም እርሷ በፍቅር የተሞላችና አንዱ ለአንዱ ግድ የሚላት ቤተክርስቲያን ስለሆነች ነው፡፡"

(ከሴር)፡ - እዚህጋ አንድ የምናገረው ነገር አለኝ፡፡ በራዕይ መፅሐፍ ኢየሱስ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በፃፈው ደብዳቤ ላይ የወንድማማች ፍቅር ከምትባለው ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ነቀፋን ፅፏል፡፡ ይህችም ቤተ ክርስቲያን ፊላደልፊያ ስትሆን ትርጉሙም የወንድማማቾች ፍቅር ማለት ነው፡፡ ለዚህችም ቤተክርስቲያን አለምን ሁሉ ሊፈትነው ከሚመጣው ፈተና በንጥቀት እንደሚያስመልጣት ቃል ገብቶላታል፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . ." እንዲገባችሁ የምፈልገው የራሳችሁን ጫናና ውጥረት የምትፈጥሩት ራሳችሁ እንደሆናችሁ ነው፡፡ ወጥመድ ውስጥ የምትገቡት እናንተው ናችሁ፡፡ ደግሞም በዚህ ማታለያ በየቀኑ እየተሸወዳችሁ ትወድቃላችሁ፡፡ ይህ በየቀኑ የሚጥላችሁ ታዲያ ምንድነው? "ስርቼ መጨረስ አለብኝ" የሚል አጋንንታዊ አባዜ ነው፡፡ ይህም የአጋንንት ወጥመድ እንደ ፓቭሎቭ ውሻ ዘላችሁ በመሮጥ እሰራለሁ ብላችሁ ባዘጋጃችሁት ዝርዝር መሰረት ሰርታችሁ ትጨርሳላችሁ፡፡"

(ከሴር)፡- በእውነት ለመናገር እኔ እንደዚያ ነበርኩ፡፡ በግብ የታጠርኩ ነበርኩ፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆቼን እጅግ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ችላ የምል ነበርኩ፡፡

ጌታም . . . "ከመንግስተ ሰማይ ስትታዩ የምትመስሉት አይምሮአችሁ በቀላሉ በአንድ አቅጣጫ የተያዘና እንደ ተራብ ውሻ አንድ አጥንት ሲወረወርላችሁ ያንን ሄዳችሁ ቶሎ እንደምታነሱ ነው፡፡ እና ደግሞ እያጋነንኩ አይደለም፡፡ ይህ በአለም በነበራችሁ ህይወት የሰለጠናችሁበት ወዲያው ዘላችሁ የምትሮጡበት የአለም አካሄድ ነው፡፡ አካሄዳችሁ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በእውቀት ሳይሆን በአለም በነበራችሁ ጊዜ እንደተቀረፃችሁት እንደዛው ናችሁ፡፡ ይህንን ለመለወጥ አሁን ጊዜው ስለሆነ የምትለወጡበትን ፀጋ እሰጣችኋለሁ፡፡

"ማንም እንደ ባርያ ነኝ ከፊታችሁ ቆሞ ቶሎ በሉ እያለ ጅራፍ የሚያወዛውዝባችሁ የለም፡፡ አዎን እናንተ ካሰባችሁት የተግባር ሰሌዳ ውጪ በየጊዜው የሚቀያየር የፕሮግራም ለውጥ ሊኖር ይችላል፡፡ እናም ያ ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እያሰለጠንኳችሁ ያለሁት እግዚአብሔርን መታዘዝ፣ ከራሳችሁ አጀንዳ ውጪ መሆን፣ ራስን መግዛትና እግዚአብሔር እንደሚፈልጋችሁ መለዋወጥ መቻል ነው፡፡ እነዚህንም ለውጦች የፈጠርኳቸው እናንተን ለማጎልመስ ወይም ቅዱስ የሆነውን መታዘዝ እንድትለማመዱና ከራሳችሁ መንገድ እንድትለዩ ለማድረግ ነው፡፡ አልለወጥም ብላችሁ በራሳችሁን መንገድ ከቀጠላችሁና ለነፍሳችሁ እየተጉ ባሉት ፊት በርሬ እሄዳለሁ የምትሉ ከሆነ መንፈሳዊ እድገታችሁን ወደኋላ እየጎተታችሁት ነው፡፡  እኔ እንኳን አባቴ ሙሽራህን ሄደህ አምጣ ሲለኝ ሙሽራዬን ለማምጣት ዝግጁ መሆን አለብኝ፡፡ አባቴ ይህንን ሲለኝ እየሰራሁ ያለሁትን ሥራ ለመተውና አባቴን ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን አለብኝ፡፡ እናንተስ ብትሆኑ ከዚህ ውጪ መሆን አለባችሁ?

"ዛሬ የተገለጠው ይህ መልዕክት ከገባችሁ ለብዙ አመታት ያሳለፋችሁት ህይወት እድገታችሁን ወደኋላ እንዴት እንደጎተተ፣ ከትልቅ በረከት እንዴት እንዳጎደላችሁና መራራ ህይወት እንዳሳለፋችሁ የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለዚህ እባካችሁ መልዕክቴን ወደ ልባችሁ በማስገባት ማዘር ክሌር በልዩ ሁኔታ ለቅድስና ህይወታችሁ እድገት ለመርዳት የተመረጠች እንደሆነች ተረዱ፡፡ የእርሷን ጥያቄ በራሳችሁ ምክንያት አስፈላጊነቱን ካሳነሳችሁትና ካልተቀበላችሁት ያልተቀበላችሁት እኔን እንጂ እርሷን አይደለም፡፡ በዚህ ሥር ምን ይገኛል? ራስን ከሚገባው በላይ ከፍ ማድረግና ኩራት ነው፡፡"

"እነዚህን ቃላቶች ስትሰሙ የትህትናን ፀጋ እየለቀቅሁላችሁ ነው፡፡ በፊት ስትመላለሱ የነበራችሁበትን መንገድ ንስሐ በመግባት ፀጋዬን ተቀበሉ፡፡ ጌታ የሚወደውን ይቀጣልና፡፡ ምክንያቱም በፍቅር ስለሚወዳቸው ብቻ ነው፡፡ በእርግጥም ምድራዊ አይምሮአችሁ ሊይዝ ከሚችለው በላይ እጅግ እወዳችኋለሁ፡፡ እናንተም እንደዚያው ውደዱኝ፡፡"

## በጆርባ እየተካሄዱ ያሉ ክስተቶችና የኮሮና ቫይረስ ክትባት ሚስጥር - ኤፕሪል 10 ቀን 2021 ዓ.ም

**America behind, April 10, 2021**

*ውድ ቤተሰቦች የጌታ ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ ሁላችንም ለመስማትና ምን ሆኖ ይሆን? እስካሁን ለምን አልሆነም? ብለን የምንጠይቃቸውን ጥያቄዎች መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ምክንያቶች ላቀርብላችሁ ፈለግሁ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ከፊታችን ተወግደው በሚቀጥለው መልዕክቴ በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ብቻ ማተኮር ስለፈለግሁ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ትክክለኛ ያልሆኑ ብዙ ዘገባዎች ስለሚቀርቡ የዝርዝር ሁኔታው ትክክለኛነት ማንም ሊያምን አይችልም፡፡ አንዳንድ ሰዎች በአይምሮአቸው ፕሬዚዳንት ትራምፕ እስካሁን ለምን በይፋ ወደ ፕሬዚዳንት ቢሮው አልተመለሰም በማለት ግራ የሚያጋቧቸው ነገሮች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ይህ ሊሆን እየተቃረበ ነው፡፡*

*የመከላከያ ኃይሉ ህገ መንግስቱን ለማስከበርና ህዝቡ ፕሬዚዳንት እንዲሆን የመረጠው ሰው ወደ ቢሮው ለመመለስ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በእጁ አድርጓል፡፡ ይህም ትክክለኛና ታማኝ የሆነውን የምርጫ ካርድ (authentic*

*watermarked ballots) በመመርመር አሁኑ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ያሸነፈው ብቸኛው እስቴት ብታምኑም ባታምኑም ኮሎምቢያ ዲስትሪክት መሆኑን በምርመራው ደርሰበታል፡፡ ኒውዮርክ ከተማና ካሊፎርኒያ እንኳን ያሸነፈው ተሸንፏል የተባለው ፕሬዚዳንት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የፕሬዚዳንቱን ሚና እየተጫወቱ ያሉት ሌሎች ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ በጣም የሚገርም ነገር መሆን አለበት! ባለፈው ጊዜ በአይሮፕላኑ መውጫ ደረጃ ላይ ሦስት ጊዜ የወደቀው ሰው ፕሬዚዳንቱ ሳይሆን ሌላ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው በቀደመ ህይወቱ እንዲህ አይነት ችግር እንዳለበት ይነገራል፡፡ እንደማምነው ከሆነ ምናልባት በቢሮው ያለው የአሁኑ ፕሬዚዳንት በሰራው ኢ - ሰባዊ ድርጊት፣ ህፃናትን በማሰቃየትና በመድፈር ክስ ቀርቦበት ይሆናል፡፡*

*የመከላከያው አባላት በምድር መሽሎክሎኪያዎች ውስጥ ደርሰው እያጋለጡት ያለውን እጅግ የሚያስፈራ ወንጀል ስሰማ ደግሞ ህመም ፈጥሮብኛል፡፡ ይህ ደግሞ እየተካሄደ ያለው በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በአለም ሁሉ ነው፡፡ የተወደዳችሁ በምድር ሥር በሚገኙ ማስተላለፊያዎች የመከላከያ አባላቶች እየሰበሰቡ ያሉት ተቆራርጦ በላስቲክ የተጠቀለለ የህፃናቶችን አካል ነው፡፡ በዋይት ሃውስ ሥር ደግሞ የኢይጥ መንጋና የበረሮ ክምችት የተራረፈውን የሰው አካል ሲመገቡ ተገኝተዋል፡፡*

*በዩ ቲዩብ ሬስኩው ጂኢ (Rescue GE) የሚባል አንድ ቻናል አለ፡፡ በዚህም ቻናል ከህዝቡ ጀርባ እየተከናወነ ያለውን ይህንን ግኝት ለህዝቡ ይፋ ለማድረግ እቅድ እንዳለው ተናግሮ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ቀን በዚያ ቀን እያሉ ቀኖችን በመለዋወጥ እስካሁን ምንም ይፋ ያደረጉት ነገር የለም፡፡ እንዳውም በእነዚህ ሦስት ቀናት ምንም አዲስ ነገር አለጠፉም፡፡*

*ማርሻል ሎው በሥራ ላይ ከዋለ ብዙ ወራቶችን አስቆጥሯል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ መከላከያው ኃላፊነቱን ወስዷል ማለት ነው፣ አራት ነጥብ፡፡ ባለ ጥቁር ባርኔጣዎች/the black hats/ የሚባሉት የተበላሸው ሁኔታ ለህዝብ ይፋ ሲደረግ አገር እንዲያናውጡና እንዲበጠብጡ ለማድረግ አመፀኞችን ስለ ቀጠሩ ባለ ነጭ ባርኔጣዎች ትልቅ ጥንቃቄ እያደረጉ ነው፡፡ ይህም አገራዊ የሆነ ነውጥ እንዳይመጣ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ እውነታ ለህዝቡ ይፋ ከሆነና ዋና የብዙሃን መገናኛ አውታሮች ከተዘጉ፣ በአሜሪካ የተደበቀና ብዙዎችን ሊያጠፉ የሚችል የኒዩክላር መሳሪያ፣ እንዲሁም የሌሎች የጦር መሳሪያዎች ፍንዳታ ሊኖር ይችላል የሚል ፍራቻ እንዳለ አምናለሁ፡፡ የመከላከያ ጦሩ እነዚህን የጦር መሳሪያዎች ፈልጎ ለማግኘት ትልቅ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሲጋቶች እንዳልተወገዱ ግልፅ ነው፡፡ ወይም ደግሞ መከላከያው ሚስጥሩን ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ለህዝቡ ያቀርብ ይሆናል፡፡*

*ሌላው ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ሰዎች ያሉበት አደጋ የማይችል ስብዕና ነው፡፡ እኔ እንደምገምተው ጉዳዩ ለህዝቡ ቶሎ ይፋ ቢሆን ይህም የዋናዎቹ ሚዲያዎችም የመውረድ ጉዳይ ይጨምራል፣ አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ሊስቱ ይችላሉ፡፡ ነገሩን ዝም ብላችሁ ስታስቡት ልብ ወለድ ከመሆን ይልቅ እጅግ የተመሰቃቀለ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ከሁሉም የተሻለ ነው ብለው የመረጡት መንገድ ጉዳዩን ለህዝቡ ቀስ በቀስ፣ ትንሽ በትንሽ ጊዜ በመውሰድ መግለጥን ነው፡፡ ቀደም ብዬ በጠቀስኩላችሁ ቻናል ላይ አንዳንድ ነገሮች በትንሹ ፍንጭ በመስጠት ጥቁር ባርኔጣ አድራጊዎቹ ያቀዱትን የበቀል እንቅስቃሴ ወይም ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለማየት ይመስለኛል እንዲህ እየተደረገ ያለው፡፡ ደግሞም ከምንጮቼ እንደተረዳሁት ይህ ትክክል ሳይሆን አይቀርም፡፡*

*ሁላችንም በየቀኑ መቼ ነው የብዙሃን መገናኛ ዘልቀው ወደ ነገሩ የሚገቡት? ደግሞስ መቼ ነው እውነቱ የሚገለጠው? ኢያልን በጉጉት እየጠበቅን እንዳለን አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ነገሩ ይፋ እንዳይሆን ያልቻሉበት ሦስት ዋና ምክንያቶች አሉ፡፡ የበቀል እርምጃ ስጋት አሁንም እንዳለ ነው፡፡ እንቅስቃሴ ለማድረግ በሚነገር በእያንዳንዱ ወቅት የበለጠ ጥቁር ባርኔጣ ለባሽ ብቅ በማለት እየተጋለጠ ነው፡፡ እናም በዚህ ጊዜ በሚሰጠው የተሳሳተ መግለጫ ህዝቡ ፀጥ ይላል፡፡ ነገር ግን በአንድ አፍታ ሁሉም ቢቀርብለት በድንጋጤ ይዋጣል፡፡ ይህ በእንዲህ ኢያለ ጥቁር ባርኔጣ ለባሾች እየተያዙ፣ ክስ እየቀረበባቸውና እየተፈረደባቸው ይገኛል፡፡*

*ሰሞኑን በስዊዝ ካናል ማለፍ እቅቷት የቆመችው ኤቨር ግሪን የምትባለው መርከብ ሆን ተብሎ እንደተደረገ መረጃን ከሚያቀብለን ምንጭ አሁን ደረሰን፡፡ በደረሰን መረጃ መሰረት መርከቧ በጫነችው ኮንቴነር ውስጥ 1,200 የሞቱ ህፃናትና 1,300 በህይወት የሚገኙ ህፃናት ተገኝተዋል፡፡ እነዚህንም ህፃናት ለማዳን በቅንብር ሲሰሩ የነበሩት የአሜሪካ የመከላከያ ክፍል፣ የአሜሪካ ልዩ ኃይል፣ የራሺያ ምሑራን እንዲሁም ግብፅ ለዚህ ተባባሪ ነበረች፡፡ በተጨማሪም በመርከቧ ውስጥ በአንድ ጊዜ ብዙ ህዝብን ሊያጠፉ የሚችል የጦር መሳሪያ ተገኝቷል፡፡ በወቅቱ ከመርከቢቷ ጋር አብረው በካናሉ ውስጥ ተቀርቅረው የነበሩ መርከቦች ሁሉ እየተፈተሹ ነበር፡፡ ህፃናትን ለእኩይ ተግባር ስለሚያዘዋውሩት የተሰራውና ተዋናይ ጂም ካቪዜል የሚጫወተው እስከ አመቱ መጨረሻ ይኸውም በፈረንጆች 2021 ዓ.ም. ድረስ ለህዝብ ዕይታ እንደሚይቀርብ ተነግሯል፡፡ ይህም ምናልባት በአለም ሁሉ ላይ በብዛት በሚገኙ የምድር ውስጥ መሽሎክሎኪያዎች ውስጥ የተያዙትን ህፃናት ለማዳን የሚደረገውን ጥረት እንዳይደናቀፍ ሊሆን ይችላል፡፡*

*አሁን ደግሞ ወደ ኮሮና ክትባት እንለፍ፡፡ የኔ ውዶች እባካችሁ ክትባቱን አትውሰዱ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም እባካችሁ የኮሮና ምርመራውን ለማድረግ እንኳን አትፍቀዱ፡፡ የቀደመው ፕሬዜዳንት የወሰደው ክትባት ሃይድሮክሎሮኪን (Hydroxychloroquine) እና ሬምደሲፊር (Remdesivir)ነው፡፡ ይህም በአፍ በጠብታ መልክ የሚወሰድ ሲሆን ወታደሩም እየወሰደ ያለው ይህንን ነው፡፡*

እነርሱ ሞድርናን *(Moderna)* ፣ አስትራ ዜንካን *(Astra Zeneca)* ፣ ጆንሰን ኤን ጆንሰንን ጃንሰንን (*Johnson & Johnson's Janssen)* ወይም ፋይዘር ባዮቴክን (*Pfizer Biotech)* እየወሰዱ አይደለም፡፡ እነዚህ ሁሉ መርዞች ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ የኮሮና ቫይረስን ለመመርመር የሚጠቀሙበት የጥጥ መመርመሪያዎች ለአይን የማይታዩ ቺፕስ በውስጣቸው እንዳለ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ እነዚህም ቺፖች ምርመራውን በሚያደርጉ ወቅት በሰውነታችሁ ላይ ተጣብቀው በመቅረት መካንነትን፣ ሞርሊዮን (Morgellons’s disease) የሚባለውን በሽታ የሚያመጣና እንዲሁም ሌሎች በሽታ ሊያመጣ የሚችል በህይወት የሚገኝ ቫይረስ ተገኝቶበታል፡፡ ይህም ምርመራ የተደረገው ገና አዲስ ከተከፈተ ጥቅልል ውስጥ በማይክሮስኮፕ ምርመራ ሲደረግ ከአንዱ ባች ሁለቱ የመመርመሪያ ጥጦች በጫፋቸው ላይ በተመሳሳይ መልኩ እላይ የተጠቀሱት በሽታ አምጪዎች ተገኝቶባቸዋል፡፡ እባካችሁ ምርመራውን አታካሂዱ፡፡ እናንተ የምትመረምሩባቸው ምናልባት እነዚህን ነገሮች የተጫኑባቸው መመርመሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ጉዳት ሊስተካከል የሚችለው ምናልባት ሜድ ቤድ (med bed) የሚባለው የህክምና አልጋ አገልግሎት ሲጀምር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ነገር እየተደረገ ያለው የጥቁር ባርኔጣዎች አለም አቀፋዊ አጀንዳ የህዝብን ብዛት በእጅጉ ለመቀነስ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው የመሃንነት ጉዳይ ከኮሮና ቫይረስ መመርመሪያና ከክትባቱ ጋር የተያያዘው፡፡ ይህ ሁሉ ግርግር በምድር ላይ ያለውን የሰው ቁጥር ለመቀነስ ነው፡፡

*እስካሁን ምን እየተካሄደ እንዳለ ፍፁም ደስ የማይል ነገር አካፍያችኋለሁ፡፡ የሚቀጥለው መልዕክት እጅግ የተሻለ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እኔ የፈለግሁት ከጀርባ እየተካሄደ ባለው ነገር ማንኛውም ግራ የሚያጋባ ነገር ከልባችሁና ከአይምሮአችሁ እንዲወገድ ነው፡፡ ዋና የሚባሉት የብዙሃን መገናኛ አውታሮች አብዛኛው መረጃ ቢኖራቸውም ዘገባውን ለህዝቡ ለማቅረብ ፈቃደኞች አልሆኑም፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታ እንዲናገረን ያለመጠየቅ ትክክል ስላልመሰለኝ ጌታ የምትለን ነገር አለ? ብዬ ጠየኩት፡፡*

*ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ ..." ሙሽሮቼ በመጀመሪያ ምን ያህል እንደምወዳችሁ በመናገር ልጀምር፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች የእናንተን ማፅናናት እፈልጋለሁ፡፡ እኔ ህፃናቱን እያዳኑ ባሉት መከላከያ ሠራዊት ውስጥ እኖራለሁ፡፡ እናም መከላከያ ሰራዊቱ ይህንን ሊነገር የማይችል እጅግ አሰቃቂ ተግባር ሲያዩ እጅግ ይሰቃያሉ፡፡ እነርሱ ሲሰቃዩም እኔም አብሬያቸው እሰቃያለሁ፡፡ ይህንን አሰቃቂ ነገር ካዩ በኋላ አንዳንዶቹ የህይወታቸው ክፍላቸው ስለተናጋ ከዚህ ማገገም አለባቸው፡፡ ጎበዝ ለመሆን ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን ያዩት ነገር በአይምሮአቸው ተቀርፆ ያሰቃያቸዋል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም በማያውቁ ህፃናት ላይ የተፈፀመው ይህ የወንጀል ተግባር የሚያሳፍርና የሚያስፈራ ነው፡፡*

*ብዙ ወላጆች የልጆቻቸውን አሳዛኝ ሞት ይሰማሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እጅግ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውን ልጆቻቸውን የህክምና ክትትል በሚያስፈልጋቸው ሁኔታ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ የህክምናው አልጋ ወይም የሜድ ቤድ (med bed) የእነዚህ ህፃናት አይምሮ እንዲፈወስና ጤነኛ እንዲሆን ሊረዳቸው ይችላል፡፡ በዚህ በኩል እነዚህ የህክምና አልጋዎች በሥራ ላይ ውለው ተስፋ ያለው  ውጤት እያሳዩ ነው፡፡ በእነዚህ በታናናሾች ላይ የተነሳውን የሰይጣንን ቁጣ ልትገምቱት ከምትችሉት በላይ ነው፡፡ እጅግ ብዙ ህዝብን በአንድ ጊዜ በሞት የዳረገ ግድያ ያያችሁ ሰዎች በሰይጣን አይምሮ ውስጥ ያለውን ማየት ችላችኋል፡፡ እርሱ የሚኖረው ለዚህ ነው፡፡*

*"ክሌር የሰጠቻችሁ መረጃዎች በአብዛኛው ትክክል ናቸው፡፡ ብዙ መረጃዎችን በመተው ፊት ለፊት ገጠው የወጡትን እውነታዎች ብቻ ነው የነገረቻችሁ፡፡ አሁን ይህንን ስላወቃችሁ እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡ አሁንም በአለም ላይ ባሉ የመሽሎኪያ ስፍራዎች ሊደረስላቸው የሚገባ ገና ብዙ ህፃናቶች አሉ፡፡ መንፈሴ በእነዚህ ወታደሮች ላይ ስለሆነ እየመራኋቸው ነው፡፡ የተወደዳችሁ እነርሱ በጭቃኔ እጅግ ብዙ የተገደሉትን ስላዩና ደግሞም ምንም ሊመልሱት የማይቻል በመሆኑ እጅግ ተጎድተዋል፡፡ ስለዚህ ፀልዩላቸው፡፡*

"በተጨማሪም ክሌር ስለ ክትባቱ የነገረቻችሁ ትክክል ነው፡፡ ምርመራውንም ቢሆን ክትባቱን አትውሰዱ፡፡ የሚሰራው ክትባት ፕሬዚዳንቱ የወሰደው በአፍ የሚሰጠው ነው፡፡ ደግሞም እንድፈውሳችሁ በእኔ ላይ መደገፍ ትችላላችሁ፡፡ በሽታው ብዙ ድካም የሚፈጥር ቢሆንም በአመት በብዙ ሺዎችን ከሚገድለው ከፍሉ የበለጠ ኃይለኛ አይደለም፡፡ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ፀልያችሁ ምንም ለውጥ ከሌለ ብዙ ልጆችን ነፃ ለማውጣትና አገራችሁን ወደ ቀድሞው ሁኔታዋ ለመመለስ እንደ ሸክም እና እንደ ፆም የሚቆጠር ስጦታ እንደሆነ ተገንዘቡ፡፡ በህልምሽ በእናንተ አገር ስለሚኖሩ ቻይናዎች ያየሽው በጣም እውነተኛ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡"

ክሌር፡- አዎ ህዝቄኤልም አንድ ሌላ አይቷል፡፡ ያንን ምናልባት ነገ እናወጣው ይሆናል፡፡

ኢየሱስም . . ."በስተጀርባ የሚሰሩ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ነገር ግን የሚያውቁት እጅግ ጥቂቶች ናቸው፡፡ አደጋ መኖሩ ደግሞ እውነት ነው፡፡ የእናንተ ፀሎት ብቻ ነው አሜሪካን ከመወረር የሚያድናት፡፡ ቃል በቃል ማለት ይቻላል፣ አገራችሁ ያለችው በእናንተ የፀሎት እጅ ላይ ነው፡፡ እኔ ቶሎ እመጣለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ምን እንደሚከናወን በራዕይ መፅሐፍ ላይ ተፅፏል፡፡ በኋላ ለሚፈፀመው ነገር አሁን ፀልዩ፡፡ ፀልዩ፣ ፀልዩ፣ ፀልዩ፡፡ ባህላችሁ ተጠርጎ እንደሚወሰድና ፍፁም በአዲስ ባህል እንደሚተካ በማሰብ ፀልዩ፡፡ አገራችሁ ሌሎች መጥተው እንደሚወሯት በማሰብ ፀልዩ፡፡ ይህ ወደፊት የሚታየው በእውነትም እጅግ አሳዛኙ ነገር ነው፡፡ የኔ የምትሉት አገር ሳይኖራችሁ ሲቀር ምን እንደሚሰማችሁ አታውቁም፡፡ የስደተኞች አደጋ ድብርት ያለበት ነው፡፡ አሜሪካ የሚደርስባት ስቃይ በፊት ይኖሩ ከነበሩት የአገሩ ተወላጆች (*Native American peoples)* መሬታቸውን ነጥቀው ሲወስዱ እንዳደረጉባቸው አይነት ነው፡፡ ለዚህ ነው እጅግ ጥልቅ የሆነ ንስሐ መግባት እንዳለባችሁ እየጠራኋችሁ ያለሁት፡፡

"እኔ ምድርን ልገዛ ስመጣ ሁሉ ነገር ትክክል ይሆናል፡፡ ለእያንዳንዱም ትክክል የሆነውን እመልሳለሁ፡፡ እስከዛው ግን ምድር በተካረረ ጥላቻ፣ ባለመግባባትና ግራ በመጋባት ትሞላለች፡፡ የኔ ውዶች ብዙ ጊዜ አትጠብቁም፡፡ በንጥቀቱ ተካፋይ የምትሆኑት ምድርን መልሶ በመገንባት ሥራ ላይ ተሳታፊ ትሆናላችሁ፡፡ ፍትህ በምድር ላይ ለሁሉም ሰው እኩል መሆኑንና ሁላችሁም በሰላም አብራችሁ መኖራችሁን ትመለከታላችሁ፡፡ ይህ ለእናንተ የገባሁት ቃል ነው፡፡ ወደፊት ወደ መንግስተ ሰማይ ተመልከቱ፡፡ ወደኋላ የምትቆዩ ሙሽሮቼ ደግሞ እስከመለስ ድረስ ለአዲስ መንፈሳዊ ጉዞ የሚሆናችሁን አዲስ ትጥቅ ተመልከቱ፡፡ በረከቴ ይህንን መልዕክት በሚሰሙትና በሚያነቡት ሁሉ ላይ ነው፡፡ እናም የምጠይቃችሁ በዚህ መልዕክት ውስጥ ባለው ቃል መሰረት ተስማምታችሁ ለፀሎት እንድትጠቀሙበት እንዲሁም እንድትዘጋጁ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ ቶሎ እመጣለሁ፡፡

(ክሌር)፡- የጌታ መልዕክት እዚህጋ ያልቃል፡፡ መጨመር የምፈልገው ስለ ንጥቀቱ ብዙ ማረጋገጫዎች እንዳሉ ነው፡፡ በዚህ መጠለያ ውስጥ ቻይና ስትወረን፣ ስለ ንጥቀቱና ስለ ታላቁ መከራ ብዙ ያየናቸው ህልሞች አሉ፡፡ ልነግራችሁ የምችለው በጣም በቅርብ አንድ ነገር እንደሚሆን ነው፡፡ ይህም ንጥቀት ማንም ከሚጠብቀው በላይ እጅግ ቅርብ ነው፡፡ ስለዚህም እባካችሁ ኩራዛችሁን ዘይት ሞልታችሁና ክሩን አስተካክላችሁ ተዘጋጁ፡፡ ምክንያቱም ማንም ሊያምነው ከሚችለው በላይ ጌታ በቅርብ ሊመጣ ነው፡፡ ጌታ ይባርካችሁ፡፡ ለእኛም ፀልዩልን፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

**የጌታ ኢየሱስ ጥሪ ለተናቁትና ለማይፈለጉት - ኤፕሪል 22 ቀን 2021 ዓ.ም**
**Rapture update & My call to the unwanted, April 22nd, 2021**

የተወደዳችሁ ኸርትድዎለርስ የጌታ ብርታትና ጥንካሬ በህይወት ያቆያችሁ፡፡አሜን፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ነፍሶችን ወደዚህ ያመጣኋቸው በእምነት እንዲበስሉና እጅግ በሚያስፈልጋቸው ልዩ ችሎታ ላስጌጣቸው ነው፡፡ ከነሙሉ ክብሯና ችሎታዋ የነበረችውን የመጀመሪያዋን ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያኔን መልሼ ላመጣት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኖችን በነፃ ሐሳብ ባቋቋሙ ሰዎች ከአካሌ ብዙ ነገር ተወግዷል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩ በመረጥኳቸው መሪዎች ብዙ ጥሩ ትምህርቶች ተሰጥተው ነበር፡፡ ነገር ግን ከሰይጣን ከፍተኛ ጥላቻና ቅናት የተነሳ የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያን እንዲደግፍ ያዋቀርኩትን ለማስቀረት ችሏል፡፡ ይህም በጠላት ላይ ኃይል የሚሰጥ፣ ወንጌል እንዲሰራጭ የሚያነሳሳና የደከሙትን የሚያበረታ ነበር፡፡

"ስለዚህም በዚህ ስፍራ የምትማሩት ከኮሌጅ ምሩቆች ተወስዶባቸው የነበረውን የመዘጋጀት መሳሪያዎችን ነው፡፡ እነዚህም ስጦታዎች ለምሳሌ በቤተክርስቲያን ሹመት መቀበልንና ለህዝቤ ትቼ የሄድኩት የሥጋ ወደሙን አገልግሎት መስጠትን ይጨምራል፡፡ እነዚህ አለምን በወንጌል ለመድረስ እጅግ አስፈላጊ ስልጠናዎች ናቸው፡፡ እጅግ የተማርን ነን ብለው ራሳቸውን የሚቆጥሩትን፣ የማይወዳደራቸው የሌለ ጠቢባንንና ብቁዎችን ለማሳፈር ሞኝ የሚመስሉትን መርጫለሁ፡፡

"ልባቸው የእኔ ስለሆነ ሆን ብዬ ነው ታናናሾቹን በዚህ የመረጥኩት፡፡ ታናናሾች ስል ቁመና ማለቴ ሳይሆን በትህትናና በታዛዥነት የታጠቁ፣ ከንፁህ ልብ በመነጨ እኔን የሚወዱ፣ ወደምልካቸው ሁሉ የሚሄዱና የምላቸውን ሁሉ የሚያደርጉ ማለቴ ነው፡፡ የአሲሲው ቅዱስ ፍራንሲስ እንዳደረገው የሚመስል አዲስ ነገር በቤተክርስቲያን እያደረግሁ ነው፡፡ እየመረትኩ ያለሁት የአለምን ጥበበኞች አይደለም፡፡ እየመረጥኩ ያለሁት አለምን፣ ምቾቷንና ክብሯን ለእኔ ሲሉ የናቁትን ነው፡፡

"ሌሎች ቢንቋቸውም ለእኔ ግን እነዚህ የመጨረሻው ዘመን ታማኝ ጄነራሎቼ እና ወታደሮቼ ናቸው፡፡ ሪክ ጆይነር ቤት የሌለውና በመንገድ ላይ የሚኖር አንድ ወንድም በጥግ ላይ ቆሞ ወንጌል ሲመሰክር አሹፌበት ነበር ብሎ የተናገረውን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? ሪክ ጆይነርን ወደ መንግስተ ሰማይ ወስጄው ይህ ወንድም በዙፋን ላይ ተቀምጦ መላዕክቶችና ቅዱሳን ሲያዝ ተመለከተ፡፡ ሪክም ይህ ወንድም ከነበረው ቅዱስ ቅናት የተነሳ ባደረገው ነገር ስለፈረደበት ራሱን ወንጀለኛ አደረገ ፡፡ ይህም ወንድም የሞተው በመንገድ ላይ አብሮት ይኖር የነበረ ወንድም ከብርድ የተነሳ ሊሞት ሲል እርሱን ለማሞቅ ብሎ በእርሱ ላይ በመተኛት ነው፡፡ ስለዚህም ወንድሙን ከሞት ለማዳን የራሱን ህይወት አሳልፎ ሰጠ፡፡

"ክሌር እነዚህ ናቸው የእኔ ታላላቆች፡፡ እነዚህ ናቸው አለምን የናቁና ለአለም የማይገቡ፡፡ እንዲህም ቢሆንም ግን ከኩራታቸው የተነሳ እኔ ልጠቀምባቸው ያልቻልኩት እነዚህን ዋጋ እንደሌላቸው ይቆጥሯቸዋል፡፡ ይህንን ደግሞ በአለም ሁሉ ተግባርያዊ እያደረግሁት ነው፡፡ አለም የማያከብራቸውን እያስነሳሁ ነው፡፡ እነዚህ እጅግ ታናናሾች፣ ባዶ እና በእኔ ፍቅር ብቻ የተያዙ ስለሆኑ በእነርሱ ድንቅ ነገርን መስራት እችላለሁ፡፡ አለምን ለመተው እንዲሁም በአዳኛቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን መናቅ እንደሚገባ በመረዳት ነው ምርጫ ያደረጉት ፡፡

"ቤተ ክርስቲያኔን ከሥር መሰረቷ ጀምሬ ወደላይ እየገነባኋት ነው፡፡ የምመልሳትም ወደ መጀመሪያዋ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ይህም ከሮም የደመቀ ስርአትና ሁኔታ ጋር የአለም እሴት ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ወደነበረው ንፁህና ቅዱስ አካሌ ነው፡፡ ስለዚህም በእኔ መጠራታችሁን እያወቁ ነገር ግን በእነዚህ በደንብ በተቋቋሙት ቤተክርስቲያናት ተቀባይነት ያጣችሁ፣ ሁላችሁንም እየጠራኋችሁ ነው፡፡ አለም ያወጣውን መስፈርት የማታሟሉ፣ ለእናንተ ደግሞ ይህ ምንም የማይመስላችሁና ግድ የሚላችሁ የእኔ ጉዳ ብቻ የሆነ፣ እናንተን ነው መቀባትና መሾም የምፈልገው፡፡ ስለዚህ ይህ ግባዣ እንደ እናንተ ላሉት ሲሆን አንድ የምፈልገው ትንሹ ነገር ግን የኔን የእሴት መዋቅር እንዲመለከት ነው፡፡ እናም ይህንን ነፍስ ከፍተኛ ዋጋ እሰጠዋለሁ፡፡

"ዲግሪ ስለሌላችሁ ከአሁን ወዲያ የበታችነት እንዳይሰማችሁ፡፡ እኔ እየተመለከትኩት ያለሁት ዲግሪ የልባችሁን ሙቀት ነው፡፡ ያንን እሳት ህይወት እንዳለው ይዛችሁት ቆዩ፡፡ እናም አልማችሁ በማታውቁት መንገድ በሚደንቅ ሁኔታ

እጠቀምባችኋለሁ፡፡ ራሳችሁን እጅግ የበታች በማድረግ ወደፊት ለመምጣት የፈራችሁትን ሁላችሁን ባረኳችሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ ስለ ራሳችሁ እንደዚያ አትበሉ፡፡ የኔን ፈቃድ ለመፈፀም ባደችሁን፣ ተርባችሁና በእሳት ተቀጣጥላችሁ ወደ እኔ እንድትመጡ ባረኳችሁ።

"አሁን በዚህ ጊዜ አዘጋጅ እየመጣ ነው፡፡ ይህም የሚሰጠው ለበታች ለሆኑ ወንዶችና ሴቶች ነው፡፡ በእነዚህ ውስጥ ሆኜ የማበራው እኔ ነኝ፡፡ እነርሱ ለራሳቸው ብዙ አጀብ ወይም የራሳቸው የሆኑ ብዙ የተሰበሰቡ ሰዎች እንዲኖሯቸው ምኞት የላቸውም፡፡ ይህንን እየሰማችሁ እያለ አሁን በዚህ ቅዱስ እሳት ባረኳችሁ፡፡ ተቀበሉትና ወደ መንገድ ሁሉ ውጥታችሁ ለመኖር፣ እንዲሁም እኔን ለማገልገል ተስፋ ለቆረጡ ይህን አካፍሉ፡፡ በአንድ ወቅት እኔን ለማገልገል የነበራቸውን ህልም እንደገና አነቃቋቸው፡፡ ቀላል መንገድንና የወንድማማች ፍቅርን አስተምሯቸው፡፡ ፈውሷቸውና ቀቧቸው፡፡ በእኔ መታመንን እንደገና አድሱላቸው፣ የውድቀትና ያለመፈለግ ጨለማ ከላያቸው ላይ አንሱ ፡፡ እኔ አልጣልኳቸውም፡፡ የእኔ እጆች እነርሱን ለማቀፍ፣ ለመፈወስና ለማስታጠቅ ተዘርግተዋል፡፡

### *መንግስተ ሰማያት መግባቴን ንዴት እርግጠኛ ልሆን እችላለሁ? የተጋጀው በማይክ ፐራልታ*

**The Gospel Simply Explained, Mike Peralta**

(Taken from Love letters from Jesus – new- page 108)

"ዛሬ ብትሞቱ መንግስተ ሰማይ ለመግባት እርግጠኞች ናችሁ?

"እርግጠኛ ካልሆናችሁ እባካችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ . . .

ብዙ ሰዎች መልካም በመስራት ህይወታቸውን ስለኖሩ ብቻ መንግስተ ሰማይ እንደሚገቡ ያስባሉ፡፡ መልካም ነገሮችን ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ያንን ይፈልገዋል፡፡ ነገር ግን መልካም ሥራ መስራታችሁ ኃጢያታችሁን አይሸፍንም፡፡ ይህ ማለት ልክ ባንክ ሲዘርፍ የተገኘ አንድ ሰው ፖሊስ ሲይዘው ለድሆች እንደሚሰጥና ችግረኞችን እንደሚረዳ ምክንያት እንደሚያቀርብ ዓይነት ነው፡፡ ነገር ግን ለድሆች መርዳቱ ባንክ ዘራፊ መሆኑን አያሽርለትም፡፡ እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ወደ መንግስተ ሰማይ ገብቶ ከእርሱ ጋር እዲሆን ይፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስን በመላክ በእኛ ምትክ በመስቀል እንዲሞት ያደረገው፡፡

ዩሐንስ 3፡16 "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"

"መጥፋት የሚለው ቃል የዘላለም ህይወት ተቃራኒ ሲሆን ይህም የዘላለም ሞት ወይም ገሃነም የሚለውን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዴት መቅረብ እንዳለብንና እንዴት መዳን እንደምንችል በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ትዕዛዝ ሰጥቶናል፡፡ ይህንንም ያደረገው ስለሚወደንና ከዚህ አለም ስንለይ ሁላችንም በመንግስተ ሰማይ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ስለሚፈለግ ነው፡፡

ሮሜ 3፡23 እንዲህ ይላል. . . "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡፡"

ይህ ማለት እኛ ሁላችን ኃጥያትን ሰርተናል፡፡ ሁላችንም ስህተትን ፈፅመናል፡፡ ስለዚህም  በከበረው በእግዚአብሔር መገኛ ውስጥ መሆን አይገባንም፡፡ ማናችንም እኔም ሆንን እናንተ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት አይገባንም፡፡ ማናችንም አይገባንም፡፡ ምክንያቱም ሁላችንም በህይወታችን እግዚአብሔርን አልታዘዝንምና ነው፡፡

በሮሜ መፅሐፍ እንዲህ ተፅፏል፡፡ "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው፡፡"ሮሜ 6፡23

የኃጢያት ደሞዝ ማለት ኃጢያት የሚያስከትለው ወይንም በኃጥያታችን ምክንያት የሚከፈለን ወይም የሚጠብቀን ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሞት መንፈሳዊ ሞት ሲሆን ይህም ወደ ገሃነም መግባትን የሚያመለክት ነው፡፡ በራዕይ መፅሐፍ እንደተገለፀው የእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው፡፡ ማንም በህይወት መፅሐፍ ውስጥ ተፅፎ ያልተገኘ ሰው በዚህ እሳት ባህር ውስጥ እንደሚጣል ቃሉ ይናገራል(ራዕይ 20፡14-15)፡፡

ስለዚህ እነዚህ ሦስት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊሰመርባቸው የሚገቡ ናቸው፡-

1. ሁላችንም ኃጢያት ሰርተናል
2. የኃጢያት ደሞዝ ደግሞ ሞት ነው
3. ሞት ደግሞ የእሳት ባህር ወይንም ገሃነም ነው

ይህንን በጥልቅ ስናገናዝበው እግዚአብሔር በህይወታችን ጣልቃ እንዲገባ እስካልፈቀድን በስተቀር ሁላችንም መጨረሻችን ገሃነም ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ማናችንም ብንሆን ወደ ገሃነም እንድንገባ አይፈልግም፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስ ለኃጢያታችን ሁሉ በመስቀል ላይ እንዲሞት ወደ ምድር የላከው፡፡ እናም የዘላለም ህይወት የምናገኘው በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ አለ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዩሐንስ 14፡6

ስለዚህም መዳን የምንችለው በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ሌላ ምንም መንገድ የለም፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ኃጢያት ክፍያ የሚቀበለው የክርስቶስን ደም ብቻ ነው፡፡ ለዛም ነው ለኃጢያታችን እንዲሞት ኢየሱስን ወደ ምድር የላከው፡፡ ይህንንም ያደረገው ስለሚወደን እንጂ ስለሚገባን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ማናችንም ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የማይገባን ስለሆነ ነው፡፡

ማወቅ ያለብን አንድ ትልቅ ነገር የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ብቻ ናቸው ሲሞቱ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ እርሱ የሚሄዱት፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አባታችን እግዚአብሔር እንዴት የእርሱ ልጆች መሆን እንደምንችል አሳይቶናል፡፡ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" ዩሐንስ 1፡12 ፡፡

በክርስቶስ ማመን ማለት የክርስቶስን መኖር ማመን ብቻ ሳይሆን ሙሉ እምነታችንን በእርሱ ላይ መጣልና እርሱን ሙሉ ለሙሉ መታዘዝ ማለት ነው፡፡ ይህ ነው በእርሱ ጌትነት ማመን ማለት፡፡ " ጌታ" የሚለው ቃል "ንጉሥ" ወይም "አለቃ" ማለት ሲሆን ይህም የምታምኑትና የምትታዘዙት የሚለውን የሚገልፅ ነው፡፡

የሮሜ መፅሐፍ ደግሞ እንዲህ ይላል "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፡፡" ሮሜ 10፡9

"ብትመሰክር" የሚለው ቃል "መስማማት" የሚለውን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በእውነት ኢየሱስ ጌታ ነው ስትል እርሱ የአንተ ጌታ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም የምትገዛለት፣ የምታምነውና የምትታዘዘው ማለት ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ክርስቶስን በእምነት ከተቀበላችሁት እርሱን ያገኛችሁት በማመን ነው እንጂ በመልካም ሥራችሁ አይደለም፡፡

"በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፡፡" ፊሊጲስዩስ 2፡8-9

ስለዚህም መዳንን በራስህ አታገኘውም፡፡ መዳን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ ይህም ልክ የልደት ስጦታ እንደመቀበል ልታየው ትችላለህ፡፡ ለልደት ስጦታ አትከፍልም ነገር ግን ስጦታውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የራስህ ውሳኔ ነው፡፡

የመዳንህን ዋጋ ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ ከፍሎታል፡፡ እናም ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ አስቃቂ ነው፡፡ ይህ እኔ ልናገረው ከምችለው በላይ ነው፡፡ እኛ ሁላችን ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት እንድንችል ኢየሱስ ብዙ ስቃይ ተቀብሏል፡፡ እኛ የሚጠበቅብን አንድ ነገር ኢየሱስ ዋጋ የከፈለበትን ይህንን ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ በነፃ መቀበል ነው፡፡

ነገር ግን ምንም እንኳን እያንዳንዳችን የዘላለም ህይወት እንዲኖረን ኢየሱስ ትልቅ ፍላጎት ቢኖረውም ጌታ አድርገን እንድንቀበለው ማንንም አያስገድድም፡፡ ለሁሉም ነፃ ምርጫ ሰጥቶአል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው እንዲቀበለውና የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እያንዳንዱን ሰው ይጋብዛል፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ይላል. . ."እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።" ራዕይ 3፡20

ስለዚህም በዚህ ጥሪ ላይ ሁላችንም መወሰን ያለብን ውሳኔ አለ፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ተለይተን ራሳችንን የምንመራው ህይወትን መምረጥ ወይም ክርስቶስ የሚመራውና ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር የሚያስችል ህይወትን መምረጥ፡፡

ራስን በመምራት የምንኖረውን ህይወት ስንመርጥ ራሳችንን በራሳችን የምናስተዳድረው ህይወት ሲሆን ይህም ምርጫ የዘላለም ምርጫ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ሆነን ከሞትን ምርጫችን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይቶ በገሃነም ውስጥ መጥፋት ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል " . . .ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁም እንዲሁ ትጠፉላችሁ (ሉቃስ 13፡3)፡፡ እግዚአብሔር ግን ይህንን ለማንም አይመኝም፡፡ ነገር ግን ደግሞ በግድ እንዲቀበሉት ማንንም አያስገድድም፡፡ በክርስቶስ የሚመራው ህይወት ራስን ለክርስቶስ ማስገዛትና ህይወትን ለእርሱ መስጠትን ይጠይቃል፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፈጠረን ደግሞም እጅግ ስለሚወደን ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ ሞተልን፡፡ በእውነቱ ከሆነ ለእግዚአብሔር መልሰን ልንሰጠው የማንችለውን ቁጥር ሥፍር የሌለውን ነገር ሰጥቶናል፡፡

ህይወታችንን ለኢየሱስ ከሰጠን የዘላለም ህይወት ሊሰጠን ቃል ገብቶልናል፡፡ በዩሐንስ 6፡40 እንዲህ ተፅፏል፡፡ "ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"

ኢየሱስን ጌታ አድርገን በህይወታችን ስንቀበል እስከዛች ሰአትና ደቂቃ ድረስ በራሳችን መንገድ በሜዳችን በተመሳሳይ መልኩ ንስሐ መግባት አለብን፡፡ ምክንያቱም ይህ አካሄድ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር የምንርቅበት መንገድ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ "ንስሐ መግባት" የሚለው ቃል ወደኋላ መመለስ ማለት ነው፡፡ ይህም ራሳችንን ስንመራ ከነበርንበት ህይወት መመለስና እግዚአብሔርን በመከተል መሄድን ያመለክታል፡፡ ንስሐ መግባት በሌላ ትርጉሙ ደግሞ ከኃጢያት መመለስን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም ኢየሱስን በመከተል ከኃጢያት እንመለሳለን ፡፡

ኢየሱስን ተቀብለን ህይወታችንን ለእርሱ ስንሰጥ ምህረትን በመጠየቅና ኃጢያትን ሁሉ በመቃወም ነው፡፡ ከጌታ ርቀን ሄደን ከሆነ ወይም ወደ ኃጢያት ተመልሰን ከሆነና አሁን ደግሞ ንስሐ መግባትና ወደ ጌታ ለመመለስ ከፈለግን እንዲህ ብለን መፀለይ እንችላለን፡-

ይህን ፀሎት ለእግዚአብሔር መፀለይ ትፈልጋለህ? ይህ ፀሎት ለእኔ ወይ ለቤተክርስቲያን ወይም ለሆነ የሃይማኖት ወገን አይደለም፡፡ ይህንን ውሳኔና ፀሎት የምታደርገው ለሚወድህና ለፈጠረህ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ነው፡፡ ይህንን ፀሎት ህይወትህን ለኢየሱስ ለመስጠት ወስነህ ትፀልያለህ? እያንዳንዱን መስመር ለእግዚአብሔር እንደሚከተለው በለው፡-

**ጌታን ለመቀበል የሚደረግ ፀሎት**

"ውድ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እኔ ኃጥያተኛ ነኝ፡፡ ደግሞም በራሴ መልካም ሥራና በራሴ መንገድ መዳን እንደማልችል ተረድቻለሁ፡፡ እንዲሁም እንደምትወደኝና ለእኔ ኃጥያት በመስቀል ለመሞት እንደተላክህም አምናለሁ፡፡ አሁን በዚህ ጊዜ ስለ ሁሉም ኃጥያቴ ንስሐ እገባለሁ፡፡ ስለዚህም ምህረት እንድታደርግልኝና የዘላለምን ህይወትን እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ፡፡ ኢየሱስ ህይወቴን ሁሉ ለአንተ ሰጥቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር ሆይ ፀሎቴን ስለሰማህኝና ስለመለስክልኝ እንዲሁም የዘላለምን ህይወት ልትሰጠኝ ቃል ስለገባህልኝ አመሰግናለሁ አሜን፡፡"

ይህንን ፀሎት ከልባችሁ ነው የፀለያችሁት? የፀለያችሁት ከልብ ከሆነ እግዚአብሔር የዘላለም ህይወትን ሊሰጥህ ቃል ገብቶልሃል፡፡ "የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡" 1ኛ ዩሐንስ 5፡13

ዛሬ ብትሞቱ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ወደ መንግስተ ሰማያት ትሄዳላችሁ፡፡ይህንን እርግጠኞች መሆን የምንችለው እግዚአብሔር ሁልጊዜ በቃሉ ታማኝ አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን በመግዛት አዲስ ኪዳንን ማንበብ ጀምሩ፡፡ እንዲሁም መፅሐፍ ቅዱስን በትክክል ከሚቀበሉና እንደ ቃሉ ከሚኖሩ ጋር ህብረት አድርጉ፡፡

ይህንን ፅሑፍ ምንም ፈቃድ ሳያስፈልገው በመገልበጥ ወይም በሌላ መንገድ ለምትፈልጉት ሁሉ ማሰራጨት ትችላላችሁ፡፡